# የእናት ጓዳ

## የባህላዊና የውጭ አገር ምግቦች አዘገጃጀት

ሁለተኛ መጽሐፍ




ከጽጌ ሩቁባሚካኤል

# የእናት ጓዳ

## ባህላዊና ዘመናዊ ምግቦችና አዘገጃጀታቸው

### ሁለተኛ መጽሐፍ

ከጽጌ ሁቁባሚካኤል

አዲስ አበባ ፲፱፻፹፬ ዓ. ም.
ADDIS ABABA, 1991

# መግቢያ

የሰው ልጅ ለመኖር ከሚያስችሉትና መሠረታዊ ከሆኑት ፍላጎቶቹ አንዱ ምግብ ነው ። ከእፅዋትና ከእንስሳት የሚገኙ የምግብ ዓይነቶች መጠናቸው ተጠብቆ እጥቅም ላይ ከዋሉ የሚሰጡት ጥቅም ከፍተኛ ነው ።

እንደ አገሩ ባህል የዓለም ሕዝብ የሚመገባቸው የምግብ ዓይነቶችና የዝግጅታቸው ሁናቴ ብዙ ነው ። በአገራችንም እያንዳንዱ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ የምግብ ምርጫና የአሠራር ስልት አለው ። የማደራጃና የማብሰያ ቁሳቁሶችም በየቦታው ይለያያሉ ፤ ዝግጅቱም ሆነ በማብቃቂያነትና በማጣፈጫነት የሚጠቀሙባቸው መቀላቀሎች መጠንና ዓይነት እንደዚሁ የተለያዩ ናቸው ።

አብዛኛው የአገራችን ሕዝብ የጤፍ ፥ የስንዴ ፥ የገብስ ፥ አልፎ አልፎም የበቆሎ እንጀራ ከመባያው (ወጥ) ጋር ይመገባል ። ዳቦ ፥ ቂጣ ፥ አምባሻ ፥ ቆሎ እንዲሁም ሌሎች የምግብ ዓይነቶች እንደ አካባቢው የአሠራር ዘዴ እየተዘጋጁ ለምግብነት ያገለግላሉ ። የተክልና የሥጋ ነክ ምግቦች የመመገብ ባህል በአገራችን የዳበረ ነው ። በመሆኑም አትክልትና ፍራፍሬ ከመመገብ ይልቅ ሥጋና ወተት መመገብ በልጦ ይገኛል ።

ዓይነቱና አሠራሩ ብዙ ይሁን እንጂ የአገራችን የባህል ምግብ አዘገጃጀት በተለምዶ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ከመሆኑ በስተቀር በምግብነት ደረጃው የተመጣጠነ ባለ መሆኑ በሰውነት ግንባታና በኃይል ምንጭነቱ እምብዛም ብቃት እንደሌለው በአመጋገብ ጠበብት ይነገራል ።

ይህ የባልትና መጽሐፍ ዋና ዓላማው ለምግብነት ከሚጠቅሙ የእርሻና የፋብሪካ ውጤቶች እንዲሁም ለአዘገጃጀታቸው አስፈላጊ ከሆነት የተለያዩ ቅመማቅመሞች ጋር ተጠቃሚውን ማስተዋወቅ ነው ። እነዚህ የምግብ አሠራር ዘዴዎች ለድርጅትም ሆነ ለቤተሰብ ጥቅም እንዲውሉ ተደርገው የተዘጋጁ ናቸው ።



የምግብ አሠራር ዘዴዎቹ በአመጋገብ ሳይንስ ላይ የተመሠረቱ ከመሆናቸውም በላይ መጽሐፉ የምግብን አሠራር ዘዴ ደረጃ በደረጃ ለማወቅና ለመረዳት እንዲቻል ተደርጎ የተዘጋጀ ሲሆን ፥ ዕድሜያቸው ምግብን ለማዘጋጀት የደረሰ ወንድ ወይም ሴት በግልም ሆነ በጋራ ተፈላጊውን የምግብ ዓይነት አዘጋጅተው ለመጠቀም ይረዳቸዋል ።

የመጽሐፉ ልዩ ባሕርይ ከሆኑት ነጥቦች ዋነኛው ፥ በምግብ አሠራር ዘዴ ዕውቀትን ከማዳበሩም ሌላ እያንዳንዱ የመጽሐፉ ተጠቃሚ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱትን ሳይንሳዊ የምግብ አሠራር ዘዴዎች መሠረት በማድረግ የፈጠራ ችሎታውን እንዲያዳብር ይረዳዋል ።

በምግብ አሠራር ሂደት ቤቶች የሚመኙትን ውጤት እውን እንዲያደርጉ እንዲረዳቸው መጽሐፉ በሁለት ተከፍሏል ። አንደኛው መጽሐፍ ባህላዊና ዘመናዊ ምግቦችን ፤ ይህም ማለት ልዩ ልዩ የእንጀራና የዳቦ ፥ የቅመማቅመምና የወጥ ዓይነቶችን ፤ የኮክቴል መጠጦችና ሾርባ ፤ የፓስታ ላዛኛ ፥ የማር ጥቅምና በማር የሚሠሩ ልዩ ልዩ ምግቦችና መጠጦችን ወዘተ. ያጠቃልላል ።

ሁለተኛው መጽሐፍ በአብዛኛው የአውሮፓውያንን የምግብ አሠራር ያካተተ ሲሆን ፥ የተለያዩ ማዮኔዝ ፥የሰላጣ ማጣፈጫ ሶስ ፥የምግብ ማጣፈጫ ፥ ሰላጣ ፥ ልዩ ልዩ የአትክልት ምግቦችን ፥ የዶሮ ፥ የሥጋና የዓሣ አሮስቶ ፥ ልዩ ልዩ የዳቦ ፥ የኬክ የኩኪስ የሳንድዊችና የአይስክሬም ወዘተ. ዓይነቶችን የያዘ ነው ። በአጠቃላይ ሁለቱም መጻሕፍት በያዙት የምግብ አዘገጃጀት ዘዴ ማንኛውም ሰው እንደ ኑሮው ደረጃና የገቢ መጠን ሊጠቀምበት የሚያስችለው ሆኖ የቀረበ ነው ። የመጻሕፍቱ ዋና ቁም ነገር ምግብ ሠርቶ ራስን መመገብን ማስተማር ብቻ ሳይሆን የተመጣጠነ ምግብ አዘጋጅቶ በመመገብ ጤናማ ዕድገት ፥ ጤናማ ሰውነት ፥ ጤናማ ሕይወት ፥ እንደሚገኝ በሰፊትና በተግባር ማስረዳት ነው ።

አስፈላጊና ጠቃሚ የሆኑ ምግቦች (የተመጣጠነ ምግብ) ባለመመገብ በውስጣዊ ረሃብ የሚጠቁ ሰዎች በርካታ ናቸው ። እነኝህ ሰዎች ይህ ስውር ረሃብ የሚያሠቃያቸው መሆኑ ባይታወቃቸውም በሰውነታቸው ላይ የሚከተሉት ምልክቶች ይታይባቸዋል ። የማያስደስት የሰውነት ቀለም ፤ የከንፈር መድረቅ ፤ የሰውነት እንደፈለጉት አለመታዘዝ ፤ የቆዳ መጠውለግ ፤ የዓይን መፍዘዝ ፤ የጸጉር

መጕሳቆል ፤ የጥርስ መውለቅና መድከም ። ይህ ሁኔታ የሚታይ ባቸው ሰዎች የዕለት ሥራቸውን በሚገባ ለማከናወን እንደሚያዳግ ታቸው ግልጽ ነው ።

ጤናማና ጠንካራ ሕዝብ ማፍራት የሚቻለው ከጤናማ ዜጋ በመሆኑ ማንኛውም የሕብረተሰብ አባል በዚህ ዓይነት የምግብ አዘ ገጃጀትና አመጋገብ ሰውሩን ረሃብ ከቤቱና ከአካባቢው ለማስወ ገድ ጥረት ማድረግ አለበት ።

የተመጣጠነ ምግብ ማለት ለሰውነት አስፈላጊ የሆኑና ሰው ነት ያለ ችግር የዕለት ተዕለት ተግባሩን እንዲያከናውን የሚረዱ ንጥረ ምግቦች ማለት ነው ። እነሱም ፥ ፕሮቲን ፥ ካርቦሃይድሬት ፥ ቅባት ፥ ማዕድን ፥ ቫይታሚንና ውኃ ናቸው ። እነዚህ ንጥረ ምግቦች በሰውነት ውስጥ የሚያከናወኑት ተግባር እንደሚከተለው ይሆናል ።

---

ማንኛወም ምግብ ብቻውን ሁሉንም ንጥረ ምግቦች አሟልቶ ሊይዝ አይችልም ፤ የምንመገበውም ለመጥገብ ብቻ ሳይሆን እያን ዳንዱ የሰውነት ክፍል ጥንካሬና ጤንነት እንዲያገኝ መሆን አለበት ። ስለዚህ ከተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ተደባልቆና ተዋሕዶ የሚሠራ ምግብ :—

አንድ እጅ

በካርቦሃይድሬትና በቅባት የበለጸጉ ምግቦች (ሙቀትና ኃይል ሰጪ)

ቅቤ ፥ ዘይት ፥ ማር ፥ እንጀራ ፥ ዳቦና የመሳሰሉት ፤ ድንች ፥ ሙዝ ፥ እንሰት ፥ ሸንኮራ አገዳ ፥ በቆሎ እሸት ወዘተ.

አንድ እጅ

በፕሮቲን የበለጸጉ ምግቦች (ገንቢ ምግቦች)

የከብት ሥጋ ፥ ቅቤ ፥ ወተት ፥ አይብ ፥ ዶሮ ፤ ጥራጥሬ ፥ አደንጓሬ ፥ ምስር ፥ አተር ባቄላ ፥ ሽንኮራ ፥ እንቍላል ፥ ዓሣ ወዘተ.



አንድ እጅ

በቫይታሚንና በማዕድን የበለጸጉ ምግቦች (በሽታ ተከላካይ ምግቦች)

ቆስጣ ፥ ሎሚ ፥ ካሮት ፥ ዘይቱን ፥ ፓፓያ ፥ ዱባ ፥ ብርቱካን ፥ቃሪያ ፥ ጥቅል ጎመን ፥ ቲማቲም ፥ ጎመን ፥ ሸንኩርት ወዘተ.

ያለበት ከሆነ የተመጣጠነ ምግብነት ደረጃ ይኖረዋል ማለት ነው ።

«የእናት ጓዳ» አንደኛ መጽሐፍ ተከታይ የሆነው ይህ የባልትና መመሪያ የያዛቸው የባልትና ዘዴዎች ከትምህርትና ከብዙ ዓመት ልምድ ባገኘሁት ዕውቀት በመታገዝ የብዙ ጊዜ ጥረትና ሙከራ ውጤት ነው።ይህ «የእናት ጓዳ» የተሰኘው ሁለተኛ የባልትና መጽ ሐፌ እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ያበረታቱኝን ሁሉ ከልብ አመሰግና ለሁ ። ለወደፊቱም የማሻሻያና የማስተካከያ አስተያየታቸውንና ምክ ራቸውን ለሚለግሱኝ ሁሉ በቅድሚያ ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ ።

ጽጌ ዑቁባሚካኤል ።

# ም ስ ጋ ና ።

ይህ መጽሐፍ እዚህ ደረጃ ለደርስ የቻለው በርካታ የሆኑ የተለያየ ሙያ ባለቤቶች የመጽሐፉን ዓላማ በመረዳት ከፍተኛ የሆነ ድጋፍና ትብብር ስላደረጉልኝ መሆኑን መግለጽ እወዳለሁ ።

አቶ አያሌው ካሣዬ ፣ ማር ነክ የሆኑ የምግብ አቀማመምን በተመለከተ በዚሁ የጥበብ ዘርፍ ያላቸውን ከፍተኛ ዕውቀት ሳይቆጥቡ አጋዥ መረጃዎችን በመስጠት ፣ ለሥራው መቃናት ገንቢ ሐሳቦችንና የሞራል ድጋፍ ስለ ለገሱኝ ፡—

ወይዘሮ አሥራት ወንድሙ ፣ በተማሩት ሰፊ የሆነ የባልትና ሙያ አማካይነት የውጭ አገር የምግብ ቅመማቅመሞች ተስማሚ በሆኑ የአገር ውስጥ ቅመማቅመሞች እንዲተኩ በማድረግ ፤ ለውጭ አገር ምግቦች አዘገጃጀትና አሠራር ጠቃሚ ምክሮችና ሐሳቦች በማበርከት ከፍተኛ ድጋፍ ስላደረጉልኝ ከልብ አመሰግናቸዋለሁ ።

በተጨማሪም የመጽሐፉን ረቂቅ በማንበብ ፣ የቋንቋውን ቅንብር ፣ የሐሳቡን ቅደም ተከተልና አጠቃላይ አቀራረቡን በማቃናት የተባበሩኝን ደራሲ አማረ ማሞን ፣ የመጽሐፉ ኅትመት ሥራ በጥራትና በቅልጥፍና እንዲከናወን ከፍተኛ ድጋፋቸውን ለሰጡኝ ለአቶ ጌታቸው ድጋፌ ፣ ለአቶ ጫኔ ወልደ ሩፋኤልና ለአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ሠራተኞች ፤ እንዲሁም የመጽሐፉን ሽፋን ሥዕል ቅንብር ላዘጋጀልን ለአርቲስት ቦጋለ በላቸው ፣ በተለያዩ መንገድ በሐሳብና በሞራል ላበረታቱኝ ሁሉ ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

ጽጌ ዑቁባሚካኤል ።



## የዕለት ምግብ

**ወተት ፤**

በቀን አራት ኩባያ ፣ ለልጆች ።
በቀን ግማሽ ኩባያ ፣ ለአዋቂዎች ።

**አትክልትና ፍራፍሬ ፤**

አንድ ሰው ከአንድ ወይም ከአንድ የበለጠ የቅጠላቅጠል ዓይነት መመገብ ያሻዋል ፤ ድንች ፣ ቲማቲም ፣ ብርቱካን ፣ ፓፓያ ፣ መንደሪን… እንዲሁም የተለያዩ ፍራፍሬዎች አረንጓዴና ቢጫ አትክልቶችን በቀን አንድ ጊዜ መመገብ አለበት ።

**እንቁላል ፤**

ከሁለት እስከ ሦስት እንቁላል ለአዋቂዎች ፤ ላደጉ ሕፃናት በየሳምንቱ ። ወጥ በሚሠራበት ጊዜ ትንሽ እንቁላል ወጡ ውስጥ መጨመር ያስፈልጋል ።

**ሥጋ ፣ ዓሣና ዶሮ ፤**

ከአትክልትና ከሥጋ ጋር የተዘጋጀ ከሆነ ፣ በአምስት ቀናት ውስጥ በቀን አንድ ባይቻል በሳምንት ሦስት ጊዜ ሥጋ ፣ ዓሣና ዶሮ መመገብ ያስፈልጋል ።

**ከእህል የተዘጋጁ ምግቦች ፤**

በየቀኑ ከእህል የተዘጋጁ ምግቦች መበላት አለበት ። ከተለያዩ የእህል ዓይነቶች የተዘጋጀ ምግብ ጠቃሚነት አለው ።

**ዳቦና ቅቤ ፤**

በቁርስ ፣ በምሳና በእራት ላይ ዳቦና ቅቤ መመገብ ያሻል ።

**ማር ፤**

በቀን ሁለት የሾርባ ማንኪያ ማር መመገብ ያስፈልጋል ።

ድፍን ምስር ፤

2½ ትልቅ ጭልፋ ድፍን ምስር = 450 ግራም

የተከካ ምስር ፤

2½ ትልቅ ጭልፋ የተከካ ምስር = 500 ግራም

ጎመን ፤

7½ ትልቅ ጭልፋ ጎመን = 450 ግራም
9 ትልቅ ጭልፋ ጎመን = 600 ግራም

ጥቅል ጎመን ፤

1 መሃከለኛ ጥቅል ጎመን = 600 ግራም

ዓሣ ፥ የዓሣ ቋንጣ ፤

1½ መሃከለኛ የዓሣ ብልት = 200 ግራም
3½ መሃከለኛ የዓሣ ብልት = 500 ግራም
6 መሃከለኛ የዓሣ ብልት = 850 ግራም
4 ትልቅ ጭልፋ የዓሣ ቋንጣ = 300 ግራም

ካሮት ፤

4 መሃከለኛ እራስ ካሮት = 200 ግራም

ፋሶሊያ ፤

3 ትልቅ ጭልፋ የተቈራረጠ ፋሶሊያ = 300 ግራም

ድንች ፤

3 መሃከለኛ ድንች (በቊጥር) = 200 ግራም
5 ትልልቅ ድንች (በቊጥር) = 500 ግራም

ምላስ ፤

2½ ትልቅ ጭልፋ የተከተፈ ምላስ = 150 ግራም



ጨጓራ ፤

4 ትልቅ ጭልፋ ተቀቅሎ የተከተፈ ጨጓራ = 150 ግራም
3 መሃከለኛ ጭልፋ የተከተፈ ጨጓራ = 190 ግራም

ጉበት ፥ ሳንባ ፥ የሽንጥ ሥጋ ፥ ወተት አንጀት ፤

2 ትልቅ ጭልፋ (ከእያንዳንዱ) የተከተፈ ጉበት ፥ ሳንባ ፥ የሽንጥ ሥጋ ፥ ወተት አንጀት = 100 ግራም

ጨው ፤

1 የሾርባ ማንኪያ ጨው = 15 ግራም
1 የሻይ ማንኪያ ጨው = 5 ግራም

ሱፍ ፤

2 ትልቅ ጭልፋ ሱፍ = 300 ግራም

ተልባ ፤

4 ትልቅ የቡና ሲኒ የተወቀጠ ተልባ = 250 ግራም

ጠጅ ፤

1 ትልቅ የቡና ሲኒ ጠጅ = 60 ሚሊ ሊትር
1 መሃከለኛ የቡና ሲኒ ጠጅ = 45 ሚሊ ሊትር
2½ ትልቅ የቡና ሲኒ ጠጅ = 100 ሚሊ ሊትር

ዶሮ ፤

1 መሃከለኛ ክብደት ያለው ዶሮ = 400 ግራም ተገንጥሎ የተከተፈ የዶሮ ሥጋ ይወጣዋል ።

ቀይ ሥር ፤

5 መሃከለኛ ራስ ቀይ ሥር = 1000 ግራም (1 ኪሎ)

## ለምግብ አሠራር የሚረዱ መሠረታዊ ነጥቦች ፡፡

1. ምግብን ለማዘጋጀት የሚውሉ ዕቃዎችን ወይም መቀላቀሎችን በንጽሕናና በሥርዓት ማዘጋጀት ።

2. ለማዘጋጀት የሚፈለገውን የምግብ ዓይነት የአዘገጃጀት መመሪያ በቅድሚያ አንብቦ የሚያስፈልጉትን መቀላቀሎች ማቅረብ።

3. በመደጋገም የሚዘጋጅ የምግብ ዓይነት አዘገጃጀት በልምድ የሚታወቅ ቢሆንም አልፎ አልፎ አንዳንድ አስፈላጊ የሆኑ የቅመም ዓይነቶች ሊረሱ ስለሚችል ይህን የባልትና መጽሐፍ ከአቅራቢያ አለማራቅ ።

4. የምግብ ዝግጅት ልክ መድኃኒት እንደ መቀመም በመሆኑ በዚህ የባልትና መጽሐፍ ውስጥ የሰፈሩትን የቅመሞች ዝርዝርና የአጠቃቀም ዘዴ በየጊዜው መመልከት ።

5. በመጽሐፉ ውስጥ የተገለጹትን ዝርዝር መመሪያዎች በመመልከት በተሰጠው መመሪያ መሠረት የሚደባለቀውን በሥርዓት አደባልቆ ማዋሐድና ለማብሰያ የተወሰነውን ጊዜ መጠበቅ።

6. ዱቄት ተለክቶ እጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በሚገባ በወንፊት መንፋት ።

7. ምድጃ ከመለኮሱ በፊት እውስጡ የቆየው አየር እንዲወጣ ለጥቂት ጊዜ ከፍቶ ማናፈስ ።

8. ለኬክ የሚሆን ዱቄት ለአሠራሩ አስፈላጊ ከሆኑ ከሌሎች መቀላቀሎች ጋር ከመደባለቁ በፊት የሚሠራው ኬክ እንዳይከብድ ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ብቻውን አሳምሮ መንፋት ።



9. የእርሾን አሠራር በተመለከተ ፤ ትንሽ የስንዴ ዱቄት ለብ ባለ ውኃ በጥብጦ በተላጠ ነጭ ሽንኩርት ውስጥ ቀጭን ስንጥር ሻጥ ሻጥ አድርጎ መጨመርና ከድኖ ማሳደር ። በማግሥቱ ጠዋት ነጭ ሽንኩርቱን አውጥቶ እርሾውን ለዳቦና ለእምፃሻ መጋገሪያ መጠቀም ።

10. ትኩስ ዳቦ በቀላሉ ለመቁረስ ሙቀት በሚሰማው ቢላዋ መቍረጥ ።

11. ዳቦን በቀጭኑ በቅቤ መቀባት ሲፈለግ ፥ መጀመሪያ የዳቦውን አንዱን ጫፍ በቅቤ መቀባትና ከዚያ በኋላ ዳቦውን መቍረጥ ።

12. የተጋገረ ዳቦ ፈርፍሮ ዱቄት ማዘጋጀት ሲፈለግ ፥ የዳቦ መፍጫ መሣሪያ መጠቀም ፤ ወይም ደግሞ የዳቦ ፍርፋሪውን ከረጢት ውስጥ ጨምሮ ክብደት ባለው ብረት መደመጥ ።

13. ዳቦ ላይ ቅርጽ ለማውጣት የተለያዩ ክፍተት (ቅርጽ) ያላቸውን ቱቦዎች በመጠቀም ሊጡ የቱቦዎቹን ቅርጽ እንዲያንፃ ማድረግ ።

14. ድንች ሳይላጥ እንዳለ መቀቀል አለበት ። ተልጦ የተቀቀለ ድንች በውስጡ ያለው ጨው ይባክናል ።

15. ወጥ ሲሠራ (መረቅ) ድንገት ጨው በዝቶበት ከተገኘ ድንች ልጦ ሁለት ቦታ ክፍሎ ለአጭር ጊዜ ወጡ (መረቁ) ውስጥ ጨምሮ ማቆየት ድንቹ ጨውን ስለሚመጠው የጨውን ብዛት ይቀንሰዋል ።

16. ሽንኩርት ሲከተፍ እንዳያስለቅስ ሽንኩርቱን ሁለት ወይም ሦስት ቦታ ቈርጦ በላዩ ላይ ውኃ አፍስሶ ለጥቂት ጊዜ ማቆየትና መክተፍ ።

17. አንድ ብርጭቆ ሩዝ ከተቀቀለ በኋላ ሦስት ብርጭቆ ሩዝ ይወጣዋል ።

18. ወይንና ብርቱካን በቀላሉ ለመላጥ ለስምንት ደቂቃ ሙቅ ውኃ ውስጥ ዘፍዝፎ ማቆየት ።

ለስላሳ አበሳሰል ፤

እንቍላሎቹን ከ12 — 15 ደቂቃ ማብሰል ።

ጠንካራ አበሳሰል ፤

እንቍላሎቹን ከ25—30 ደቂቃ ማብሰል ።

ዓሣ የሚበስልበት የሙቀት ደረጃ ፤

ዓሣ ከመጠበሱ በፊት የጀርባ አጥንቱን (ደንደሱን) ማውጣት ። የውስጥ አካሉን አውጥቶ በደንብ አድርጎ መቀመም ፤ በመጨረሻም በ350 ድግሪ ፋራንሃይት ከ45—50 ደቂቃ መጥበስ ።



## ማዮኔዝ፣የሰላጣ ሶስ፣የምግብ ማጣፈጫ ሰላጣ አቀማመም።

001. ማዮኔዝ ፣ ቍጥር 1 ።

½ የሻይ ማንኪያ የተፈጨ ሰናፍጭ
¼ የሻይ ማንኪያ ስኳር
2 ኩባያ የሰላጣ ዘይት
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
3 የእንቍላል አስኳል
1 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
የጣት ቁንጣሪ ፓፕሪካ
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ሰናፍጭ ፣ ስኳር ፣ ፓፕሪካ ፣ ጨውና ቁንዶ በርበሬ አንድ ላይ ማቀላቀል ።
2. እንቍላል ጨምሮ በማንኪያ ወደ አንድ በኩል ብቻ መምታት ።
3. ከዘይቱ ግማሽ ኩባያ ቀንሶ ትንሽ ጠብ እያደረጉ ወደ አንድ በኩል መምታት ።
4. የቀረውን ዘይት ትንሽ በትንሽ ጠብ እያደረጉ ወፈር እስኪል ድረስ መምታት ።
5. የሎሚ ጭማቂውን ጨምሮ በደንብ ማደባለቅ ።
6. ሰፊ አፍና መክደኛ ባለው ጠርሙስ ውስጥ ጨምሮ ማቀዝቀዣ ውስጥ ማስቀመጥ ። ማዮኔዙ ማቀዝቀዣ ውስጥ ባይገባም መጠቀም ይቻላል ። ለሰላጣና ለሳንድዊች ፣ ለመሳሰሉት ምግቦች ማጣፈጫነት ያገለግላል ።

002. ማዮኔዝ ቍጥር ፣ 2 ።

2 እንቍላል
4 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ

2. እንደ ተዘጋጀ ወዲያው ማቅረብ ።
3. ከሃምበርገር ሰላጣ ፣ ከሳንድዊችና ከመሳሰሉት ምግቦች ጋር መቅረብ ይችላል ።

አንድ ኩባያ ተኩል ማዮኔዝ ይወጣዋል ።

006. የቀዝቃዛ ቲማቲም ማዮኔዝ ።

4 ቲማቲም ፣ ተልጦ የተከተፈ
2 የሻይ ማንኪያ ቀይ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
1 ኩባያ ማዮኔዝ
ትንሽ ጨው
ትንሽ ሚጥሚጣ
አቮካዶ
የሰዲኖ ቅጠል

አሠራር

1. ቲማቲም ፣ ሽንኩርት ፣ ማዮኔዝ ፣ ጨውና ሚጥሚጣ አደባልቆ ማቀዝቀዣ ውስጥ ማቀዝቀዝ ።
2. አቮካዶውን ልጦ ሁለት ቦታ ከትፎ ፍሬውን አውጥቶ የቀዘቀዘውን የታማቲም ማዮኔዝ መሙላት ።
3. የተሞላውን አቮካዶ በሰዲኖ ቅጠል አስጊጦ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

007. የእርጎ ሰላጣ ሶስ ።

1 ኩባያ እርጎ
½ ኩባያ የሎሚ ጭማቂ

አሠራር

መቀላቅሎቹን አንድ ላይ ደባልቆ ለጎመን ሰላጣ ማጣፈጫ መጠቀም ።



008. የማር ሰላጣ ሶስ ፣ ቊጥር 1 ።

1 ሎሚ ጭማቂ
¼ ኩባያ ውኃ
1 የሾርባ ማንኪያ ማር
1 የሾርባ ማንኪያ ዘይት
2 የሾርባ ማንኪያ ፐርሰሜሎ ፣ በደቃቁ የተከተፈ
ትንሽ ቀይ ሽንኩርት ፣ በደቃቁ የተከተፈ

አሠራር

ከላይ የተጠቀሱትን በሙሉ አንድ ላይ ደባልቆ ማቅረብ ።

009. የፎርማጆ ሶስ ።

2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
1 የሾርባ ማንኪያ የፋርኖ ዱቄት
1 ኩባያ ወተት
¾ ኩባያ ፎርማጆ
ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. የቀለጠውን ቅቤና ዱቄት አደባልቆ ወተቱን ጨምሮ እስኪ ወፍር ድረስ እያማሰሉ ማብሰል ።
2. ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬና ፎርማጆ ጨምሮ እያማሰሉ ፎርማጆው እስኪቀልጥ ድረስ እሳቱ ላይ ማቆየት ።
3. ከተለያየ የምግብ ዓይነት ጋር ትኩሱን መቅረብ ይችላል ።

አንድ ኩባያ ተሩብ ሶስ ይወጣዋል ።

010. የእንቁላል ሶስ ።

6 እንቁላል ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
1 ኩባያ ክሬም
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
¼ ኩባያ ፐርሰሜሎ ፣ የተከተፈ
ጨው ፣ ሚጥሚጣ

**አሠራር**

1. የተከተፈውን እንቊላል ፣ ክሬም ፣ ጨው ፣ ቅቤና ሚጥሚጣ በብረት ድስት የፈላ ውኃ ላይ ጥዶ በእንፋሎት ማሞቅ ።
2. ፐርስሜሎ ጨምሮ ከተዋሐደ በኋላ ማውጣት ።
3. ከአትክልት ምግቦች ጋር ትኩሱን ማቅረብ ።

ሁለት ኩባያ ተኩል ሶስ ይወጣዋል ።

## 011. የአሳማ ሥጋና የቲማቲም ሶስ ።

1 ፍንካች ነጭ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
1 ቀይ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ዘይት
$\frac{3}{4}$ ኩባያ የአሳማ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
$1\frac{1}{2}$ ኩባያ የቲማቲም ሾርባ
1 የሻይ ማንኪያ ስኳር

**አሠራር**

1. ቀይና ነጭ ሽንኩርት በዘይት ማቁላላት ።
2. የአሳማ ሥጋ ፣ የቲማቲም ሾርባና ስኳሩን ጨምሮ ለአሥር ደቂቃ ማብሰል ።
3. ከተለያየ የምግብ ዓይነቶች ጋር ትኩሱን መቅረብ ይችላል ።

ሁለት ኩባያ ተሩብ ሶስ ይወጣዋል ።

## 012. የሆላንድ ሶስ ።

$\frac{1}{2}$ ኩባያ ቅቤ
2 የእንቊላል አስኳል ፣ በደንብ የተመታ
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
ትንሽ ሚጥሚጣ

**አሠራር**

1. ቅቤውን ሦስት ቦታ መክፈል ።
2. የተመታውን የእንቊላል አስኳል ከአንደኛው ቅቤ ጋር አደባልቆ የሞቀ ውኃ ላይ ጥዶ በእንቊላል መምቻ ወይም በማንኪያ መምታት



3. ቀሪውን ቅቤ በየተራ በመጨመር ቅቤው እስኪቀልጥ ድረስ የፈላ ውኃ ላይ ጥዶ መምታት ።
4. የቅቤና የእንቊላል ድብልቁ ከወፈረ በኋላ ከተጣደበት ውኃ ላይ አውጥቶ ሚጥሚጣና የሎሚ ጭማቂውን ጨምሮ ማዋሐድ ።
5. ከተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ጋር መቅረብ ይችላል ።

ሦስት አራተኛ ኩባያ ሶስ ይወጣዋል ።

## 013. የቲማቲም ሰላጣ ሶስ ።

$\frac{1}{2}$ ኩባያ የሰላጣ ዘይት
$\frac{1}{4}$ ኩባያ የሎሚ ጭማቂ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ የተፈላ ቲማቲም

**አሠራር**

ዘይት ፣ የሎሚ ጭማቂና ቲማቲም አንድ ላይ ደባልቆ ማቅረብ ።

## 014. የቫኒላ ሶስ ።

1 የሾርባ ማንኪያ ቫኒላ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ስኳር
1 የሾርባ ማንኪያ የበቆሎ ስታርች—ኮርን ስታርች
1 ኩባያ የፈላ ውኃ
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
ትንሽ ጨው

**አሠራር**

1. ስኳርና የበቆሎ ስታርቹን አደባልቆ በፈላ ውኃ መበጥበጥ ።
2. የተበጠበጠውን ስኳርና የበቆሎ ስታርች እያማሰሉ ለአምስት ደቂቃ ማፍላት ።
3. ቅቤ ፣ ቫኒላና ጨው ጨምሮ ማደባለቅ ።
4. ሶሱ ከተዘጋጀ በኋላ ትኩሱን ማቅረብ ።

አንድ ኩባያ የቫኒላ ሶስ ይወጣዋል ።

አሠራር

1. አቮካዶውን አጥቦና ልጦ ፍሬውን ማውጣት ።
2. የተላጠውን አቮካዶ በደንብ አድቅቆ መፍጨት ።
3. የተፈጨውን አቮካዶ ማዮኔዝ ፣ ጨውና የበርበሬ ሶስ ወይም የቲማቲም ካችአፕ አንድ ላይ ማደባለቅ ።
4. የተዘጋጀውን የአቮካዶ ሶስ ታጥቦ በተቀቀለ ጠርሙስ ውስጥ ጨምሮ ክድኖ ማስቀመጥና ሲያስፈልግ መጠቀም ።

ሁለት ኩባያ ሶስ ይወጣዋል ።

032. ከአቮካዶ ጋር የሚቀርብ ኮክቴል ሶስ ።

½ ኩባያ ወፍራም ክሬም
½ ኩባያ የበርበሬ ሶስ
½ ኩባያ ማዮኔዝ
3 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
አቮካዶ

አሠራር

1. ክሬሙን በእንቁላል መምቻ በደንብ መምታት ።
2. የበርበሬ ሶስ ፣ ማዮኔዙንና የሎሚ ጭማቂውን ከተመታው ክሬም ጋር አደባልቆ ታጥቦ የተቀቀለ ጠርሙስ ውስጥ ጨምሮ መክደን ።
3. የተዘጋጀውን ሶስ ከአቮካዶ ጋር ማቅረብ ።

033. ከግሬፕ ፍሩት ጋር የሚቀርብ ሶስ ።

½ ኩባያ ወፍራም ክሬም
1 ኩባያ የቲማቲም ሶስ
1 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
ግሬፕ ፍሩት



አሠራር

1. ክሬሙን በእንቁላል መምቻ በደንብ መምታት ።
2. የቲማቲም ሶስና የሎሚ ጭማቂውን ከክሬሙ ጋር አደባልቆ በደንብ መምታት ።
3. ሶሱን ታጥቦ በተቀቀለ ጠርሙስ ውስጥ ጨምሮ መክደን ።
4. ተልጦ ከተከተፈ ግሬፕ ፍሩት ጋር ይቀርባል ።

አንድ ኩባያ ተኩል ሶስ ይወጣዋል ።

034. የዱባ ሶስ ።

1 ዱባ ፣ ተልጦ የተከተፈ
½ ኩባያ የበርበሬ ሶስ
1 የሻይ ማንኪያ ሽንኩርት ፣ በደቃቁ የተከተፈ
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ
ትንሽ ታባስኮ ሶስ

አሠራር

1. ዱባውን አጥቦና ልጦ በደቃቁ መከተፍ ።
2. የተከተፈውን ዱባ ከበርበሬ ሶስ ፣ ከሽንኩርት ፣ ከቁንዶ በርበሬና ከታባስኮ ሶስ ጋር በደንብ ማደባለቅ ።
3. ሶሱን ታጥቦ በተቀቀለ ጠርሙስ ውስጥ ጨምሮ መክደን ።
4. ከዓሣና ከመሳሰሉት ምግቦች ጋር ይቀርባል ።

አንድ ኩባያ ተሩብ ሶስ ይወጣዋል ።

035. የፍራፍሬ ሶስ ።

1 ኩባያ የእንጆሪ ማርማላት (የእንጆሪ ጃም)
½ ኩባያ የፈላ ውኃ
1 የሾርባ ማንኪያ የብርቱካን ልጣጭ ፣ (ፍቅፋቂ)

አሠራር

1. የእንጆሪ ጃም ፣ የፈላ ውኃና የብርቱካን ልጣጭ አደባልቆ በደንብ መምታት ።
2. የተዘጋጀውን ሶስ ትኩሱን ማቅረብ ።

አንድ ኩባያ ተሩብ ሶስ ይወጣዋል ።

2. የቀዘቀዘውን የኮክቴል ሶስ ከተለያዩ ምግቦች ጋር ማቅረብ ይቻላል ።

ግማሽ ኩባያ ሶስ ይወጣዋል ።

041. ራዲሽ የኮክቴል ሶስ ።

1 የሾርባ ማንኪያ ራዲሽ ፥ በደቃቁ የተከተፈ
½ ኩባያ የቲማቲም ካችአፕ
¼ ኩባያ የበርበሬ ሶስ
1 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
ትንሽ ታባስኮ ሶስ ፥ ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. የቲማቲም ካችአፕ ፥ የበርበሬ ሶስ ፥ የሎሚ ጭማቂ ፥ ታባስኮ ሶስ ፥ ራዲሽ ፥ ጨውና ቁንዶ በርበሬ በደንብ ማደባለቅ ።
2. የተዘጋጀውን የራዲሽ ሶስ ንጹሕ ጠርሙስ ውስጥ ጨምሮ መክደን ።
3. ከብዙ ዓይነት ምግቦች ጋር መቅረብ ይችላል ።

አንድ ኩባያ ተሩብ ሶስ ይወጣዋል ።

042. የዳቦ ሶስ ።

4 ፍሬ ቅርንፉድ
1 ትንሽ ሽንኩርት ፥ ተልጦ ሁለት ቦታ የተከተፈ
⅓ ኩባያ ወተት ፥ የሞቀ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
1½ የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ቅርንፉድ ፥ ሽንኩትር ፥ የተፈጨ ዳቦና የሞቀ ወተት ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ የፈላ ውኃ ላይ ጥዶ ለሃያ ደቂቃ በእን ፋሎት ማብሰል ።



2. ቅርንፉድና ሽንኩርቱን ከዳቦና ከወተት ድብልቁ ውስጥ ማውጣት።
3. ጨው ፥ ቁንዶ በርበሬና ቅቤውን ከዳቦ ድብልቁ ጋር አዋሕዶ ቅቤው እስኪቀልጥ ድረስ እያማሰሉ የፈላ ውኃ እንፋሎት ላይ አቆይቶ ማውጣት ።
4. ከብዙ ዓይነት ምግቦች ጋር ይቀርባል ።

አንድ ኩባያ ሶስ ይወጣዋል ።

043. የቲማቲም ስላጣ ሶስ ፥ ቊጥር 2 ።

2 ትልቅ ሽንኩርት ፥ የተከተፈ
2 ቃሪያ ፥ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ የስላጣ ዘይት
1 ኩባያ ቲማቲም ፥ ተከትፎ የተቀቀለ
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
½ የሻይ ማንኪያ ሚጥሚጣ

አሠራር

1. ሽንኩርትና ቃሪያውን በዘይት ማቁላላት ።
2. ቲማቲም ጨውና ሚጥሚጣ ከተቁላላው ሽንኩርትና ቃሪያ ጋር አደባልቆ ቲማቲሙ እስኪበስል ድረስ እያማሰሉ እንደ ተጣደ ማቆየት ።
3. ሶሱ ከበሰለ በኋላ ከተጠበሰ እንቊላል ወይም ከተቀቀለ ሩዝ ጋር መቅረብ ይችላል ።

አንድ ኩባያ ተኩል ሶስ ይወጣዋል ።

044. ነጭ ሶስ ።

2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
2 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
1 ኩባያ ወተት
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ቅቤውን ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ በእሳት ማቅለጥ ።

2. ዱቄቱን ከቀለጠው ቅቤ ጋር ጨው ጨምሮ ማደባቅለ ።
3. በመጠኑ ወተት በመጨመር እያማሰሉ ማዋሐድ ።
4. ወተትና ዱቄቱ ከተዋሐደ በኋላ ለሦስት ደቂቃ ያህል በመጠነኛ እሳት ላይ አንተክትኮ ማውጣት ።

አንድ ኩባያ ሶስ ይወጣዋል ።

### 045. የቪኖ ሶስ—ለዶሮ ።

2 ትንሽ ሽንኩርት ፡ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ቅቤ
2 ፍሬ ቅርንፉድ ፡ ድፍን
1 የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
2 ፍንካች ነጭ ሽንኩርት ፡ የተከተፈ
2 ኩባያ ነጭ ቪኖ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሻይ ማንኪያ ፐርሰሜሎ ፡ የተከተፈ
2 ኩባያ ክሬም
$\frac{1}{2}$ ዶሮ ፡ ተገነጣጥሎ የተዘጋጀ
ትንሽ ሚጥሚጣ

#### አሠራር

1. ሽንኩርቱን በቅቤ ማቁላላት ።
2. ቅርንፉድ ፡ ቁንዶ በርበሬና ነጭ ሽንኩርት ከተቁላላው ሽንኩርት ጋር ማደባለቅ ። የዶሮ ሥጋውን ጨምሮ አጋም እስኪመስል ማቁላላት ።
3. ቪኖ ፡ ጨው ፡ ሚጥሚጣና ፐርሰሜሎ ጨምሮ ለአሥር ደቂቃ በመጠነኛ እሳት ላይ ጥዶ ማንተክተክ ።
4. የበሰለውን የዶሮ ሥጋ አውጥቶ ማቅረቢያ ሣህን ላይ ማድረግ ። የቀረውን ሶስ አጥልሎ ከክሬሙ ጋር አደባልቆ ሲፈላ ማውጣት ።
5. ከክሬሙ ጋር የተዘጋጀውን ሶስና የዶሮ ሥጋ ትኩሱን ማቅረብ ።

ሁለት ሰው ይመገባል ።

### 046. የቪኖ ሶስ—ለሥጋ ።

3 መካከለኛ ሽንኩርት ፡ በስሱ የተቈረጠ
1 ቃሪያ ፡ የተከተፈ



1 ኩባያ ሰዲኖ ፡ የተከተፈ
$1\frac{1}{2}$ ኪሎ ኩባያ ቀይ ቪኖ
1 ኩባያ የቲማቲም ጭማቂ
$1\frac{1}{2}$ ቀይ ሥጋ
ቅቤ ፡ ለመጥበሻ ፡ የፉርኖ ዱቄት

#### አሠራር

1. ሥጋውን ቈርጦ እንዲሳሳ መቀጥቀጥ ።
2. የተቀጠቀጠውን ሥጋ ዱቄት ነስንሶ በመጥበሻ ላይ እፈላው ቅቤ ውስጥ ጨምሮ አጋም እስኪመስል አገላብጦ መጥበስ ።
3. ሽንኩርት ፡ ቃሪያ ፡ ሰዲኖና ግማሹን ቪኖ ከተጠበሰው የእስቴክ ሥጋ ጋር መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ። ሙቀቱ 400 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአንድ ሰዓት ተኩል ማቆየት ።
4. የቀረውን ቪኖ ፡ የቲማቲሙን ጭማቂ ጨምሮ ለአንድ ተጨማሪ ሰዓት ምድጃ ውስጥ ማብሰል ።

ስምንት ሰው ይመገባል ።

### 047. የቪኖ ሶስ—ለምላስ ።

1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 ኩባያ የእንጆሪ ጃም (ማርማላት)
1 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ውኃ
3 ፍሬ ቅርንፉድ—ድፍን
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ቪኖ
3 የሾርባ ማንኪያ መረቅ
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

#### አሠራር

1. ቅቤ ፡ የእንጆሪ ጃም ፡ የሎሚ ጭማቂ ፡ ቁንዶ በርበሬ ፡ ውኃ ፡ ቅርንፉድና ጨው ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ ለአምስት ደቂቃ ማንተክተክ ።
2. በተራ ቊጥር 1 የተዘጋጀውን በማጥለያ አጥልሎ ቪኖና መረቁን ጨምሮ ሲፈላ ማውጣት ።

2. የሚፈለገው ያህል የእሳማ ሥጋ በስሱ ከተቈረጠ በኋላ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ሙቀቱ 400 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ማብሰል ።
3. ሥጋው በሚበስልበት ወቅት በተራ ቍጥር 1 የተዘጋጀውን የፍራፍሬ ጭማቂና የቪኖ ድብልቅ ሥጋው ላይ መጨመር ።
4. ሥጋው በስሎ ከወጣ በኋላ ቀሪውን መረቅ ወይም ግሬቪ ከመጋገሪያው ላይ ወደ ብረት ድስት ገልብጦ እሳት ላይ መጣድ ። ዱቄትና ውኃውን አደባልቆ የሚፈላው ግሬቪ ውስጥ ጨምሮ እስኪወፍር ድረስ እያማሰሉ ማንተክተክ ።
5. ጨውና ቁንዶ በርበሬውን ጨምሮ አዋሕዶ ማውጣት ።
6. ከበሰለው ሥጋ ጋር ትኩሱን ማቅረብ ።

ሁለት ኩባያ ተኩብ ግሬቪ—መረቅ—ይወጣዋል ።

052. የቲማቲም ሾርባና የቅመማቅመም ሶስ ።

$\frac{1}{2}$ የሾርባ ማንኪያ ቀይ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
1 የሾርባ ማንኪያ ሴዲኖ ፣ የተከተፈ
1 ፍንካች ነጭ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
1 ቃሪያ ፣ የተከተፈ
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
1 ኩባያ የቲማቲም ሾርባ
ትንሽ ጨውና ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ቀይ ሽንኩርት፣ሰዲኖ፣ነጭ ሽንኩርትና ቃሪያ በቅቤ ማቁላላት ።
2. የቲማቲም ሾርባ ፣ ቁንዶ በርበሬና ጨው ከተቁላላው የሽንኩርት ድብልቅ ጋር አዋሕዶ ሲፈላ ማውጣት ።
3. ከተቀቀለ ጥቅል ጎመን ጋር ትኩሱን ማቅረብ ።

አንድ ኩባያ ተኩብ ሶስ ይወጣዋል ።

053. የቲማቲምና የፎርማጆ ሶስ ፣ ቍጥር 1 ።

300 ግራም የቲማቲም ሾርባ
$\frac{3}{4}$ ኩባያ ወተት
2 የሾርባ ማንኪያ ፎርማጆ
2 በስሱ የተቈረጠ ቤከን ፣ በደቃቁ የተከተፈ



አሠራር

1. የቲማቲም ሾርባውንና ወተቱን እደባልቆ ማፍላት ።
2. ፎርማጆውን ጨምሮ እያማሰሉ እስኪቀልጥ ድረስ ማብሰል ።
3. በደቃቁ የተከተፈውን ቤከን ጨምሮ ወዲያው ማውጣት ።
4. ከፒሳ ጋር ትኩሱን ማቅረብ ።

ሁለት ኩባያ ሶስ ይወጣዋል ።

054. የስፓጌቲ ሶስ ።

$\frac{1}{2}$ ኪሎ ስፓጌቲ
2 ቀይ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
2 ፍንካች ነጭ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ዘይት
700 ግራም ቀይ ሥጋ ፣ የተፈጨ
$2\frac{1}{2}$ ኩባያ የቲማቲም ጭማቂ
$3\frac{1}{2}$ ኩባያ የቲማቲም ሳልሳ
4 ቃሪያ ፣ ፍሬው የወጣ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
1 የሻይ ማንኪያ ስኳር
12 የወይራ ፍሬ ፣ የተከተፈ
ፎርማጆ

አሠራር

1. ቀይና ነጭ ሽንኩርት በዘይት ማቁላላት ።
2. ሥጋውን ጨምሮ እያማሰሉ ማቁላላት ።
3. የቲማቲም ሳልሳ ፣ የቲማቲም ጭማቂ ፣ ቃሪያ ፣ ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬና ስኳር ከተቁላላው ሥጋ ጋር አደባልቆ ከሁለት ተኩል እስከ ሦስት ሰዓት መጠነኛ በሆነ እሳት ላይ ማንተክተክ ።
4. ቃሪያውን አውጥቶ የወይራ ፍሬውን ጨምሮ ለአሥር ደቂቃ ያህል ማንተክተክ ።
5. የተቀቀለ ስፓጌቲ ላይ ፎርማጆ ነስንሶ ከተዘጋጀው ትኩስ ሶስ ጋር ማቅረብ ።

ለግማሽ ኪሎ ስፓጌቲ ይበቃል ።

055. የአሳማ ሥጋ ሶስ ።

6 በስሱ የተቈረጠ የአሳማ ሥጋ ፥ በደቃቁ የተከተፈ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
$2\frac{1}{2}$ ኩባያ ወተት
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው

አሠራር

1. የአሳማ ሥጋውን ብቻውን መጥበስ ።
2. ዱቄቱን ከተጠበሰው ሥጋ ጋር ማደባለቅ ።
3. ወተትና ጨው ጨምሮ እስኪወፍር ድረስ እያማሰሉ ማብሰል ።
4. ከተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ጋር ትኵሱን መቅረብ ይችላል ።

ሁለት ኩባያ ተኩል ሶስ ይወጣዋል ።

056. የቲማቲምና የፎርማጆ ሶስ ፥ ቍጥር 2 ።

2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ።
2 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ በሶቢላ
2 ኩባያ የቲማቲም ጭማቂ
$\frac{3}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
1 ኩባያ ፎርማጆ

አሠራር

1. ቅቤውን አቅልጦ ዱቄትና በሶቢላውን ጨምሮ ማደባለቅ ።
2. የቲማቲም ጭማቂውን በመጠኑ በመጨመር እያማሰሉ እስኪ ወፍር ድረስ ማማሰል ።
3. ጨው ፥ ቁንዶ በርበሬና ፎርማጆ ጨምሮ እያማሰሉ ፎርማጆው እስኪቀልጥ ድረስ እሳቱ ላይ ማቆየት ።
4. ከተለያየ የምግብ ዓይነት ጋር ትኵሱን ማቅረብ ይቻላል ።

ሦስት ኩባያ ሶስ ይወጣዋል ።

057. የፈረንሳይ የሰላጣ ማጣፈጫ—ፍሬንች ድሬሲንግ ።

1 ኩባያ የሰላጣ ዘይት
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ኮምጣጤ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ነጭ ቁንዶ በርበሬ



2 የሾርባ ማንኪያ ፐርሰሜሎ ፥ የተከተፈ
ትንሽ ሚጥሚጣ

አሠራር

1. ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ በአንድ ጠርሙስ ውስጥ ጨምሮ ጠርሙሱን በጣም በመናጥ ቅመሙ ከዘይቱ ጋር እንዲዋሐድ ማድረግ ።
2. የተዘጋጀው የሰላጣ ማጣፈጫ ከተለያዩ የሰላጣ ዓይነቶች ጋር መቅረብ ይችላል ።

አንድ ኩባያ ተሩብ የሰላጣ ማጣፈጫ ይወጣዋል ።

058. የፈረንሳይ የሎሚ የሰላጣ ማጣፈጫ ።

$\frac{1}{2}$ ኩባያ የሰላጣ ዘይት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ የሎሚ ጭማቂ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
2 የሾርባ ማንኪያ ስኳር ወይም ማር
ትንሽ ሚጥሚጣ

አሠራር

1. ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ በአንድ ጠርሙስ ውስጥ ጨምሮ ጠርሙሱን በጣም በመናጥ ቅመሙ ከዘይቱ ጋር እንዲዋሐድ ማድረግ ።
2. የተዘጋጀው የሰላጣ ማጣፈጫ ከተለያዩ የሰላጣ ዓይነቶች ጋር መቅረብ ይችላል ።

አንድ ኩባያ የሰላጣ ማጣፈጫ ይወጣዋል ።

059. የሩስያ የሰላጣ ማጣፈጫ—ራሺያን ድሬሲንግ ።

1 ኩባያ የሰላጣ ዘይት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ የቲማቲም ካቾፕ
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ኮምጣጤ
2 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ የሰላጣ ሽንኩርት ፥ የተከተፈ

3. የእንቍላሉን አስኳል አድቅቆ ከኮምጣጤ ክሬም ፥ ከማዮኔዝ፥ ከኮምጣጤና ሰናፍጭ ጋር አደባልቆ ማሞቅ ።
4. የሞቀውን የክሬም ድብልቅ በተራ ቍጥር 2 ከተዘጋጀው መቀላቅል ጋር አደባልቆ ማቅረብ ።

122. ትኩስ የድንች ሰላጣ ።

6 መካከለኛ ድንች ፥ የተቀቀለና የተከፈተ
2 የተቀቀለ እንቍላል ፥ የተከተፈ
4 በስሱ የተቈራረጠ የአሳማ ሥጋ—ቤከን
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ፥ የተከተፈ ሽንኩርት
1 እንቍላል ፥ የተመታ
4 የሾርባ ማንኪያ ኮምጣጤ
$1\frac{3}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
ሰላጣ ቅጠል

አሠራር

1. የተከተፈውን ድንችና እንቍላል ማደባለቅ ።
2. ቤከኑን በደቃቁ ከትፎ ከሽንኩርት ጋር ማብሰል ።
3. የበሰለውን ቤከን ከድንችና ከእንቍላል ጋር ማደባለቅ ።
4. የተመታውን እንቍላል ፥ ኮምጣጤና ጨው አደባልቆ በተራ ቍጥር 3 ከተዘጋጀው መቀላቅል ጋር መዋሐድ ።
5. ውኃ በብረት ድስት ጥዶ ሲፈላ ድብልቁን የፈላው ውኃ ላይ ከነዕቃው አስቀምጦ በቀስታ በእንፋሎት ማብሰል ።
6. በቅጠል ሰላጣ አጊጦ ትኩሱን ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

123. የቲማቲም ሰላጣ ።

8 ቲማቲም
$1\frac{1}{2}$ ኩባያ ክሬም ቺዝ—የሰላጣ አይብ
2 የእንቍላል አስኳል ፥ የተቀቀለ
ሰላጣ ቅጠል
የሰላጣ ማጣፈጫ
ወተት



አሠራር

1. ቲማቲሙን ልጦ ማቀዝቀዝ ።
2. የሰላጣውን አይብ ከወተት ጋር ማደባለቅ ።
3. የሰላጣውን ቅጠል አጥቦ ሣህን ላይ ማዘጋጀት ።
4. የቀዘቀዘውን ቲማቲም ሁለት ቦታ ከፍሎ ሰላጣው ላይ መደርደር ።
5. ክሬም ቺዙን ከቲማቲሙ ዳር በከቡ መደርደር ።
6. የእንቍላሉን አስኳል ቲማቲሙ ላይ ማድረግ ።
7. የሰላጣ ማጣፈጫ ጨምሮ ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

124. ከሣቴ ከርስ ሰላጣ ።

$1\frac{1}{2}$ ኩባያ የተከተፈ ካሮት
1 ትንሽ ዱባ—የፈረንጅ ዱባ
1 እንቍላል ፥ የተቀቀለ
ሽንኩርት
የሰላጣ ማጣፈጫ

አሠራር

1. ካሮቱን በማቀዝቀዣ ውስጥ ለአንድ ሰዓት ማቆየት ።
2. ዱባውን ልጦ በቁመቱ በስሱ መቍረጥና ማቀዝቀዝ ።
3. ሰላጣውን አጥቦ ሣህን ላይ ማዘጋጀት ።
4. ካሮቱንና ዱባውን ሰላጣው ላይ መደርደር ።
5. የእንቍላሉን አስኳልና ነጩን ክፍል (ዞፉን) መለየት ።
6. ነጩን እንቍላል በስሱ ቈርጦ ካሮትና ዱባው ላይ ማኖር ።
7. የእንቍላሉን አስኳል ፥ አድቅቆ አላዩ ላይ መነስነስ ።
8. የሰላጣውን ማጣፈጫ ጨምሮ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

125. የድብልቅ አትክልት ሰላጣ ፥ ቍጥር 4 ።

$\frac{1}{2}$ ኩባያ የወይራ ፍሬ ፡ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ካሮት ፥ ተቀቅሎ የተከተፈ
1 ኩባያ የሰዲኖ ቅጠል ፥ የተከተፈ
1 ኩባያ አተር ፥ የተቀቀለ

3. የተደባለቁትን መቀላቀሎች ማቀዝቀዝ ።
4. ክሬም ፣ ማዮኔዝና የወይራ ፍሬ መጨመር ።
5. ቅርጽ ማውጫ ዕቃ ላይ ጨምሮ በረዶ ቤት ውስጥ ማቀዝቀዝ ።
6. ሰላጣ ቅጠሉን አጥቦ በማህን ላይ ማዘጋጀት ።
7. የቀዘቀዘውን ሰላጣ የተዘጋጀው ሰላጣ ቅጠል ላይ መገልበጥ ።
8. በወይራ ፍሬ ማስጌጥ ።
9. ማዮኔዝና ትንሽ ሚጥሚጣ እላዩ ላይ ነስንሶ ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 138. የዶሮና የአሳማ ሥጋ ሰላጣ በሰናፍጭ ።

1½ ኩባያ ዶሮ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
1½ ኩባያ የአሳማ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
½ የሻይ ማንኪያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
6 ቲማቲም
1 ኩባያ ማዮኔዝ
2 የሾርባ ማንኪያ ሰናፍጭ
¼ ኩባያ የሰላጣ ማጣፈጫ
ጨውና ትንሽ ሚጥሚጣ
ሰላጣ ቅጠል
ፐርሰሜሎ

### አሠራር

1. ዶሮ ፣ የአሳማ ሥጋና ሽንኩርቱን ከሰላጣ ማጣፈጫ ጋር አደባልቆ ለአንድ ሰዓት ማስቀመጥ ።
2. ቲማቲሙን ልጦ ከጨው ጋር አደባልቆ ማቀዝቀዝ ።
3. ማዮኔዙን ከሰናፍጭ ጋር አደባልቆ ከዶሮ ድብልቁ ጋር መዋሐድ ።
4. ሰላጣውን አጥቦ ማህን ላይ ማዘጋጀት ።
5. እንዱን ቲማቲም ስድስት ቦታ ቈርጦ ቅጠል ሰላጣው ላይ መደርደር ።
6. ሰላጣው መካከል ላይ የዶሮ ሰላጣ ማስቀመጥ ።
7. ፐርሰሜሎ ቅጠልና ሚጥሚጣ ነስንሶ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።



## 139. የሥጋ ሰላጣ ።

1 ኩባያ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
2 እንቊላል ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
2 ቲማቲም ፣ አራት ቦታ የተከተፈ
4 እንቾቪ ወይም በጣም ትንሽ ዓሣ—የቆርቆሮ ወይም የተቀቀለ
1 ትንሽ ጥቅል ሰላጣ
የሰላጣ ማጣፈጫ

### አሠራር

1. ሥጋ ፣ እንቊላል ፣ ቲማቲምና እንቾቪ ወይም ዓሣ አንድ ላይ ማደባለቅ ።
2. ሰላጣውን አጥቦ ማህን ላይ ማዘጋጀት ።
3. በተራ ቊጥር 1 የተዘጋጀውን የሥጋ ሰላጣ ማህን ላይ ባለው ሰላጣ ቅጠል ላይ መገልበጥ ።
4. ከሰላጣ ማጣፈጫ ጋር ማደባለቅና ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 140. በዓሣ የተሞላ የአቮካዶ ሰላጣ ።

2 አቮካዶ
1 ኩባያ የሰሊሪ ቅጠል ፣ የተከተፈ
1 ኩባያ ዓሣ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
½ ኩባያ ማዮኔዝ
የሎሚ ጭማቂ
ጨው
የሰላጣ ማጣፈጫ

### አሠራር

1. አቮካዶውን በቁመቱ ሰንጥቆ ፍሬውን ማውጣት ።
2. አቮካዶው ውስጥ የሎሚ ጭማቂና ጨው መነስነስ ።
3. ዓሣ ፣ የሰሊሪ ቅጠልና ማዮኔዝ በአንድ ማህን ውስጥ ማደባለቅ ።
4. አቮካዶውን በተደባለቀው ዓሣ መሙላት ።
5. ከሰላጣ ማጣፈጫ ጋር ማቅረብ ።

አምስት ሰው ይመግባል ።

8. ሰላጣ ሣህን ላይ መገልበጥ ።
9. በቅጠል ሰላጣና አናናስ ቅጠል አጊጦ ማቅረብ ።

አራት ሰው ይመግባል ።

148. ቀዝቃዛ የቲማቲም ሰላጣ ።

6 ትናንሽ ቲማቲም
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
በጣም ትንሽ በርበሬ
ሰላጣ ቅጠል ፥ ማዮኔዝ
የሰላጣ ማጣፈጫ

አሠራር

1. ቲማቲሙን አጥቦ ትንሽ ከማፉ በኩል መቦርቦር ።
2. ጨውና በርበሬ ነስንሶ በረዶ ቤት ውስጥ ማቀዝቀዝ ።
3. ሰላጣ ቅጠሉን አጥቦ ሣህን ላይ ማዘጋጀት ።
4. የተዘጋጀው ሰላጣ ላይ የቀዘቀዘውን ቲማቲም ማስቀመጥ ።
5. የተቦረቦረውን ቲማቲም ማዮኔዝ መሙላት ።
6. ከሰላጣ ማጣፈጫ ጋር ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

149. ቀዝቃዛ የወይራ ፍሬና የፎርማጅ ሰላጣ ።

10 የበሰለ የወይራ ፍሬ ፥ የተከተፈ
3 ኩባያ ፎርማጅ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ክሬም
6 ቲማቲም
ሰላጣ ቅጠል
ማዮኔዝ

አሠራር

1. ፎርማጅ ፥ የወይራ ፍሬና ክሬሙን በደንብ ማደባለቅ ።
2. በስድስት የወረቀት ወይም የፕላስቲክ ኩባያ ውስጥ ሞልቶ በረዶ ቤት ውስጥ ማቀዝቀዝ ።



3. ቲማቲሙን አጥቦ መቦርቦርና የቀዘቀዘውን ሰላጣ መሙላት ።
4. ሰላጣ ቅጠሉን አጥቦ ሣህን ላይ ማዘጋጀት ።
5. የተሞላውን ቲማቲም ሰላጣ ቅጠሉ ላይ ደርድሮ ከማዮኔዝ ጋር ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

150. ቀዝቃዛ የኮክና የፎርማጅ ሰላጣ ።

$\frac{1}{2}$ ኩባያ ፎርማጅ
1 ቆርቆሮ ኮክ
3 የሾርባ ማንኪያ የሰላጣ ማጣፈጫ
ሰላጣ ቅጠል
የተፈጨ ዝንጅብል

አሠራር

1. የኮኩን ውኃ አጥልሎ ከፎርማጅና ከተፈጨ ዝንጅብል ጋር በደንብ እስኪዋሐድ ድረስ መምታት ።
2. ኮኩን ቈርጦ በሰላጣ ሣህን ላይ አድርጎ ማቀዝቀዝ ።
3. የተደባለቀውን ፎርማጅ ኮኩ ላይ አፍስሶ እንደገና ማቀዝቀዝ ።
4. ሰላጣ ቅጠሉን አጥቦ ሣህን ላይ ማዘጋጀት ።
5. የቀዘቀዘውን ሰላጣ ከበረዶ ቤት አውጥቶ በአራት ማዕዘን በትንሹ ቈራርጦ ሰላጣ ቅጠሉ ላይ መደርደር ።
6. ከሰላጣ ማጣፈጫ ጋር ማቅረብ ።

አራት ሰው ይመግባል ።

151. ቀዝቃዛ የበጋ የፍራፍሬ ሰላጣ ።

$\frac{1}{2}$ ኩባያ እንጆሪ ፥ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ አናናስ ፥ ተልጦ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ብርቱካን ፥ ተልጦ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ሙዝ ፥ ተልጦ የተከተፈ
2 የሻይ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
1 የሻይ ማንኪያ ጀላቲኒ
1 የሾርባ ማንኪያ ቀዝቃዛ ውኃ
4 የሻይ ማንኪያ ማር
$\frac{2}{3}$ ኩባያ ክሬም ፥ የተመታ
ሰላጣ ቅጠል

አሠራር

1. ቲማቲሙን አጥቦ ከጫፉ በኩል ቈርጦ ፍሬውን በማንኪያ ቦርቡሮ ማውጣት ።
2. ቲማቲሙ ውስጥ አንድ የሻይ ማንኪያ ቅቤና ትንሽ ጨው ጨምሮ አንድ እንቍላል ሰብሮ ቲማቲሙ ውስጥ መሙላት ። በዚህ ዓይነት ስድስቱንም ቲማቲም መሙላት ።
3. የተሞላውን ቲማቲም መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

154. በእንቍላል የተጠበሰ ዳቦ ።

3 እንቍላል
2 ኩባያ ወተት
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
12 ቦታ የተቈረጠ ዳቦ
ዘይት—ቅቤ ፤ ለመጥበሻ

አሠራር

1. እንቍላል ፥ ወተትና ጨው አደባልቆ መምታት ።
2. ዳቦውን የተመታው እንቍላል ውስጥ ነክሮ በዘይት ወይም በቅቤ መጥበስ ።
3. እያገላበጡ አጋም እስኪመስል ድረስ ጠብሶ ማውጣት ።
4. ትኩሱን ከማርማላት ጋር ማቅረብ ።

155. ተሰብሮ በውኃ የተቀቀለ እንቍላል ።

1 እንቍላል
1 በቅቤ የተጠበሰ ዳቦ
2 ኩባያ ውኃ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
½ የሻይ ማንኪያ ኮምጣጤ

አሠራር

1. ውኃ በብረት ድስት ማፍላት ።
2. ጨውና ኮምጣጤ የፈላ ውኃ ውስጥ መጨመር ።



3. እንቍላሉን ሰብሮ የፈላው ውኃ ውስጥ ጨምሮ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።
4. የበሰለውን እንቍላል በቅቤ ከተጠበሰ ዳቦ ጋር ማቅረብ ።

156. እንቍላል በሶስ ።

1½ ኩባያ ነጭ ሶስ ወይም ቲማቲም ሶስ
6 የተቀቀለ እንቍላል
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
¼ የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
4 የሾርባ ማንኪያ ወተት
1 ሽንኩርት ፥ የተከተፈ

አሠራር

1. የተቀቀለውን እንቍላል ልጦ በቁመቱ ሁለት ቦታ መክፈል ።
2. ከተቈረጠው እንቍላል ውስጥ አስኳሉን በጥንቃቄ ማውጣት ።
3. አስኳሉን ከጨው ፥ ከቁንዶ በርበሬ ፥ ከቅቤ ፥ ከወተትና ከሽንኩርት ጋር በደንብ አደባልቆ ነጩ እንቍላል ውስጥ መሙላት ።
4. የተሞላውን እንቍላል መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
5. ሙቀቱ 325 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ አስገብቶ ለአምስት ደቂቃ ማብሰል ።
6. የተዘጋጀው እንቍላል ላይ ነጭ ሶስ ወይም የቲማቲም ሶስ ጨምሮ ማቅረብ ።
7. ከተፈለገ ፥ ግማሽ ኩባያ ተቀቅሎ የተከተፈ የአሳማ ሥጋና ሁለት የሾርባ ማንኪያ የተከተፈ ፕርሰሜሎ ከእንቍላሉ አስኳል ጋር አደባልቆ ማቅረብ ይቻላል ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

157. የእንቍላል ሱጎ ።

6 እንቍላል ፥ የተቀቀለ
3 ኩባያ መረቅ
¼ ኩባያ ክሬም
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
3 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት

አሠራር

1. ድንቹን ልጦ ማጠብ ።
2. የተላጠውን ድንች መጋገሪያው ዕቃ ላይ አድርጎ ሙቀቱ ከ425—450 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአርባ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።
3. የበሰለውን ድንች በጥንቃቄ ውስጡን መቦርቦር ።
4. ተቦርቡሮ የወጣውን ድንች ፣ ቅቤ ፣ ጨው ፣ በርበሬና ወተት በጐድጓዳ ሣህን ውስጥ አደባልቆ የተቦረቦረው ድንች ውስጥ እንቍላል መጨመሪያ ያህል ቦታ ትቶ መሙላት ።
5. በእያንዳንዱ የተሞላ ድንች ውስጥ እንቍላል ሰብሮ መጨመር ።
6. እላዩ ላይ ትንሽ ጨውና በርበሬ መነስነስ ።
7. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ በተፈለገው ዓይነት አብስሎ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 165. እንቍላልና ሩዝ ።

6 እንቍላል
1 ኩባያ ሩዝ
½ ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
2½ ኩባያ ቲማቲም ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
½ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
¾ የሻይ ማንኪያ ጨው
2 ቅርንፉድ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
2 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
2 የሾርባ ማንኪያ ፎርማጆ

አሠራር

1. ሩዙን ጨው በገባበት ውኃ መቀቀል ።
2. ቲማቲም ፣ ሽንኩርት ፣ ጨውና ቅርንፉድ በአንድ ላይ ለአሥር ደቂቃ አብስሎ ማጥለል ።
3. ዱቄቱንና ቅቤውን በጐድጓዳ ብረት ድስት ውስጥ ማደባለቅ ።
4. የቲማቲሙን ጥላይ ከዱቄትና ከቅቤ ጋር አደባልቆ እያማሰሉ እስኪወፍር ድረስ ማማሰል ።



5. መጋገሪያ ዕቃውን (ካሴሮል) ቅቤ ወይም ዘይት መቀባት ።
6. ሩዙን የተቀባው መጋገሪያ ዕቃ ላይ ጨምሮ ስድስት ቦታ ሩዙን መሃሉን ከፈት ከፈት ማድረግ ።
7. እንቍላሉን እየሰበሩ ከፍት ቦታ ውስጥ መሙላት ።
8. በተራ ቍጥር4 የተዘጋጀውን የቲማቲም ሶስ ሩዙና እንቍላሉ ላይ መጨመር ።
9. የተፈጨ ዳቦና ፎርማጆ ነስንሶ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

## 166. እንቍላል በቲማቲም ።

6 እንቍላል ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
2 ቲማቲም ፣ የተላጠ
6 በስሱ የተቈረጠ ዳቦ
2 ኩባያ ቺዝ ሶስ
12 በስሎ የተቈረጠ የአሳማ ሥጋ—ቤከን ፐርስሜሎ

አሠራር

1. ቲማቲሙን በስሱ መቍረጥ ።
2. ዳቦውን በዳቦ መጥበሻ ወይም በምጣድ ላይ በመጠኑ ማድረቅ ።
3. ዳቦው ላይ የተከተፈውን እንቍላል ማድረግ ። እንቍላሉ ላይ የተከተፈውን ቲማቲም መደረብ ።
4. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ከበሰለ በኋላ ትኵስ ቺዝ ሶስ እላዩ ላይ ጨምሮ እንደ ገና ምድጃ ውስጥ መመለስ ።
5. የተጨመረው የቺዝ ሶስ መፍላት ሲጀምር አውጥቶ በፐርስ ሜሎ አጊጦ ከአሳማ ሥጋ (ቤከን) ጋር ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 167. እንቍላል የተሞላ ቲማቲም ።

6 እንቍላል
2 ኩባያ ቲማቲም ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
1 ሽንኩርት ፣ የተከተፈ

1 የሻይ ማንኪያ ጨው
6 በስሱ የተቆረጠ ደረቅ ዳቦ፣ ቅቤ የተቀባ
ትንሽ በርበሬ

አሠራር

1. ሽንኩርትና ቲማቲሙን አደባልቆ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
2. የቲማቲሙንና የሽንኩርቱን ድብልቅ ሙቀት 350 ድግሪ ፋራን ሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአሥር ደቂቃ አቆይቶ ጨውና በርበሬ መጨመር ።
3. እንቁላሉን ሰብሮ በተራ ቊጥር 2 የተዘጋጀው የቲማቲም ድብልቅ ላይ ማፍሰስና እንደገና ምድጃ ውስጥ ጨምሮ እንቁላሉ እስኪ በስል ማቆየት ።
4. ትኩሱን ከደረቅ ዳቦ ጋር ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

168. እንቁላል በደረቅ ዳቦ ።

6 እንቁላል ፤ አስኳሉና ዞፉ (ነጨ) የተሰየ
6 በስሱ የተቈረጠ የደረቀ ዳቦ
ቅቤ
ጨው
በርበሬ

አሠራር

1. ደረቁን ዳቦ ቅቤ ቀብቶ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
2. ውኃ በጨው በብረት ድስት አፍልቶ የእንቁላሉን አስኳል መቀቀል ።
3. የተቀቀለውን አስኳል የተቀባው ደረቅ ዳቦ ላይ ማድረግ ።
4. የእንቁላሉን ዞፍ በወፍራሙ መትቶ ከአስኳሉ ዙሪያ በማፍሰስ ጨውና በርበሬ እላዩ ላይ መነስነስ ።
5. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ አብስሎ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።



169. እንቁላል በቅቤ ።

2 እንቁላል
1 የሾርባ ማንኪያ ኮምጣጤ
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 የሻይ ማንኪያ ፐርሰሜሎ፣ የተከተፈ

አሠራር

1. ትንሽ ኮምጣጤ ውኃ ውስጥ ጨምሮ ማፍላት ።
2. እንቁላሉን ሰብሮ የፈላው ውኃ ውስጥ ጨምሮ በመጠኑ ማብሰል ።
3. የበሰለውን እንቁላል ሣህን ላይ አድርጎ ኮምጣጤውን አፍልቶ መጨመር ።
4. ቅቤና ፐርሰሜሎውን በብረት ድስት ጥዶ በደንብ ማቁላላት ።
5. የተቁላላውን ቅቤና ፐርሰሜሎ እንቁላሉ ላይ ጨምሮ ማቅረብ ።

አንድ ሰው ይመግባል ።

170. የዶሮ ሳንድዊች ።

1 ኩባያ የዶሮ ሥጋ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
½ ኩባያ የሰዲኖ ቅጠል፣ የተከተፈ
1 የሾርባ ማንኪያ ቃሪያ፣ የተከተፈ
¼ ኩባያ ማዮኔዝ
ለስላሳ ወይም ደረቅ ዳቦ
የሰላጣ ወይም የሰዲኖ ቅጠል

አሠራር

1. የዶሮ ሥጋ ፣ የሰዲኖ ቅጠል ፣ ቃሪያና ማዮኔዝ ማደባለቅ ።
2. ለስላሳ ወይም ደረቅ ዳቦ ላይ የዶሮውን ድብልቅ ማድረግ ።
3. ከላይ በሌላ ዳቦ ሸፍኖ በአራት ወይም በሦስት ማዕዘን መቊረጥ ።
4. በሰላጣ ወይም በሰዲኖ ቅጠል አጊጦ ማቅረብ ።

171. የፈረንሳይ እንቁላል ጥብስ ።

6 እንቁላል፣ የተቀቀለ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ

## 175. የእንቁላል አምሌት በዱቄት ።

4 እንቁላል ፤ አስኳሉና ዞፉ የተለየ
2 የሾርባ ማንኪያ የፋርኖ ዱቄት
1 ኩባያ ወተት
½ የሻይ ማንኪያ ጨው

**አሠራር**

1. ዱቄቱን በሩብ ኩባያ ወተት ማቡካት ።
2. የቀረውን ወተት ከእንቁላል አስኳሉ ጋር መምታት ።
3. የእንቁላሉን ዞፍ በወፍራሙ መትቶ በተራ ቁጥር 2 ከተዘጋጀው እንቁላልና ዱቄት ጋር ማዋሐድ ።
4. ቅቤ ወይም ዘይት መጥበሻ ላይ አፍልቶ የእንቁላሉንና የዱቄቱን ድብልቅ መጥበስ ።

አራት ሰው ይመግባል ።

## 176. የእንቁላል አምሌት በድንች ።

3 እንቁላል ፤ አስኳሉና ዞፉ የተለየ
3 የሾርባ ማንኪያ ወተት
1 ኩባያ ድንች ፤ ተቀቅሎ የተፈጨ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
¼ የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
ሽንኩርት ፤ በደቃቁ የተከተፈ
ፐርሰሜሎ ፤ በደቃቁ የተከተፈ
ቅቤ

**አሠራር**

1. የእንቁላሉን አስኳል ከድንቹ ጋር አደባልቆ መምታት ።
2. ጨው ፤ ቁንዶ በርበሬ ፤ ሽንኩርትና ፐርሰሜሎ ጨምሮ ማዋሐድ ።
3. የእንቁላሉን ዞፍ በወፍራሙ መምታት ።
4. በተራ ቁጥር 2 የተዘጋጀውን መቀላቅል ከተመታው ዞፍ ጋር ማደባለቅ ።



5. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ እያገላበጡ ማብሰል ።

ከአራት እስከ ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 177. የእንቁላል አምሌት በአሳማ ሥጋ ።

8 እንቁላል
8 ቁራጭ በስሎ የተከተፈ የአሳማ ሥጋ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው

**አሠራር**

1. የአሳማ ሥጋውን ቅቤ ወይም ዘይት ሳይጨመርበት መጥበስ ።
2. እንቁላሉንና ጨውን አደባልቆ መምታት ።
3. የተመታውን እንቁላል የአሳማ ሥጋው ላይ ጨምሮ በመጠነኛ ሙቀት ማብሰል ።
4. በዝርግ ሣህን ላይ አድርጎ ትኩሱን ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 178. ስፓንሽ አምሌት ።

1 የተዘጋጀ አምሌት
½ ቃሪያ ፤ የተከተፈ
1 የሾርባ ማንኪያ ሽንኩርት ፤ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
6 የወይራ ፍሬ ፤ የተከተፈ
1¾ ኩባያ ቲማቲም ፤ ተቀቅሎ የተከተፈ
1 የሾርባ ማንኪያ እንጉዳይ ፤ የተከተፈ
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
ሚጥሚጣ

**አሠራር**

1. ሽንኩርቱንና ቃሪያውን በሙጠኑ በቅቤ ማብሰል ።
2. ቲማቲሙንና የወይራ ፍሬውን ጨምሮ እስኪወፍር ድረስ እያማሰሉ ማብሰል ።
3. እንጉዳይ ፤ ጨውና ሚጥሚጣ መጨመር ።

185. የቻይና የእንቍላል ቅቅል—ፖችድ ኤግ ።

6 እንቍላል ፣ ተሰብሮ በውኃ የተቀቀለ
1 ኩባያ ሩዝ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
2 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
1 ኩባያ ወተት
1 የሻይ ማንኪያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
1 የሾርባ ማንኪያ ሰዴኖ ፣ የተከተፈ
ጨው
በርበሬ
የፓርስሜሎ ቅጠል
ሚጥሚጣ

አሠራር

1. ውኃ በጨው አፍልቶ ሩዙን መቀቀል ።
2. ቅቤውን አቅልጠ ዱቄትና ጨው ጨምሮ ማደባለቅ ።
3. ወተት ፣ በርበሬ ፣ ሽንኩርትና ሰዴኖ ጨምሮ እያማሰሉ እስ ኪወፍር ማብሰል ።
4. የተቀቀለውን ሩዝ ሣህን ላይ አድርጎ እንቍላሉን እላዩ ላይ ማድረግ ።
5. በተራ ቍጥር 3 የተዘጋጀውን ሶስ ሩዝና እንቍላሉ ላይ መጨመር።
6. በፓርስሜሎ ቅጠልና በሚጥሚጣ አጊጦ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

186. የእንቍላልና የካሮት ፍርፍር ።

6 እንቍላል ፣ ተቀቅሎ የተቈራረጠ
6 ካሮት ፣ ተቀቅሎ የተቈራረጠ
4 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
4 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
$2\frac{1}{2}$ ኩባያ ወተት
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ በርበሬ
6 ቦታ የተቈራረጠ ደረቅ ዳቦ
ፓርስሜሎ



አሠራር

1. ቅቤውን ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ ማቅለጥ ።
2. ዱቄቱንና ወተቱን ከቅቤው ጋር አዋሕዶ እስኪወፍር ድረስ አለማቋረጥ እያማሰሉ ማብሰል ።
3. ጨው ፣ በርበሬ ፣ እንቍላልና ካሮቱን ጨምሮ ሲፈላ ማውጣት ።
4. የእንቍላልና የካሮቱን ድብልቅ የደረቀው ዳቦ ላይ መጨመር ።
5. በፓርስሜሎ ቅጠል አጊጦ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

187. ቲማቲምና እንቍላል በደረቅ ዳቦ ።

9 እንቍላል ፣ ተቀቅሎ የተቈራረጠ
6 ደረቅ ዳቦ ፣ ቅቤ የተቀባ
4 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
6 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
4 ኩባያ ቲማቲም ፤ ተቀቅሎ የተከተፈ
ፓርስሜሎ

አሠራር

1. ቅቤውን አቅልጦ ዱቄትና ጨው መጨመር ።
2. ቲማቲሙን ጨምሮ እስኪወፍር ማብሰል ።
3. እንቍላሉን ከበሰለው ሶስ ጋር አደባልቆ የደረቀው ዳቦ ላይ መጨመር ።
4. በፓርስሜሎ አጊጦ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

188. እንቍላል በዓሣ ።

6 እንቍላሉን ፣ የተቀቀለ
3 የእንቍላል አስኳል ፣ ያልተቀቀለ
1 ኩባያ የዓሣ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
1 የሻይ ማንኪያ ፓርስሜሎ ፣ የተከተፈ

አሠራር

1. የእንቁላሉን አስኳል መፍጨት ።
2. ጨው ፣ በርበሬና የእንቁላሉን ዞፍ ከተፈጨው የእንቁላል አስኳል ጋር ማደባለቅ ።
3. በተራ ቁጥር 2 የተዘጋጀውን በእጅ በክቡ ማድቦልቦልና ዱቄት እላዩ ላይ መነስነስ ።
4. የተድቦለቦለውን የእንቁላል ድብልቅ በቅቤ መጥበስ ።
5. የተጠበሰውን ድቡልቡል እንቁላል ሾርባ ውስጥ ጨምሮ ማቅረብ።

196. የካሮት ካስታርድ ።

3 እንቁላል
1½ ኩባያ ካሮት ፣ ጥሬ ወይት ተቀቅሎ የተከተፈ
3 ኩባያ ወተት
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ

አሠራር

1. እንቁላሉን በመጠኑ መምታት ።
2. ካሮት ፣ ወተት ፣ ጨውና ቅቤውን ከእንቁላል ጋር ማደባለቅ ።
3. መጋገሪያውን ዕቃ ቅባት ቀብቶ ማዘጋጀት ።
4. በተራ ቁጥር 2 የተዘጋጀውን የእንቁላልና የካሮት ድብልቅ የተቀባው መጋገሪያ ዕቃ ላይ መጨመር ።
5. የሞቀ ውኃ ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ መጋገሪያውን ዕቃ ሙቅ ውኃው ላይ አድርጎ ሙቀቱ 325 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአንድ ሰዓት በእንፋሎት ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

197. የፎርማጆ ካስታርድ ።

4 እንቁላል
½ ኩባያ ፎርማጆ
1½ ኩባያ ወተት
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
ትንሽ በርበሬ



አሠራር

1. እንቁላሉን በመጠኑ መምታት ።
2. ወተት ፣ ጨው ፣ በርበሬ ፣ ፎርማጆ ከእንቁላል ጋር ማደባለቅ ።
3. መጋገሪያ ዕቃውን ቅባት መቀባት ።
4. በተራ ቁጥር 2 የተዘጋጀውን መጋገሪያ ዕቃ ላይ ገልብጦ በፈላ ውኃ ላይ አስቀምጦ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ከሃያ አምስት እስከ ሠላሳ ደቂቃ ማብሰል ።
5. ከበሰለ በኋላ ከምድጃ አውጥቶ ለሦስት ደቂቃ ማስቀመጥ ።
6. ከቲማቲም ሶስ ጋር ማቅረብ ።

አራት ሰው ይመግባል ።

198. የበቆሎ ካስታርድ ።

3 እንቁላል
2 ኩባያ በቆሎ ፣ በቆርቆሮ የታሸገ ወይም ተፈልፍሎ የተቀቀለ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
2 ኩባያ ወተት
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
በርበሬ
ስኳር
የተፈጨ ዳቦ
ቅቤ

አሠራር

1. እንቁላሉን በደንብ መምታት ።
2. በቆሎ ፣ የቀለጠ ቅቤና ወተት ከእንቁላል ጋር ማዋሐድ ።
3. ጨው ፣ በርበሬና ስኳር መጨመር ።
4. የመጋገሪያ ዕቃውን (ካሴሮል) ቅባት መቀባት ።
5. የበቆሎውን ድብልቅ የመጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
6. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለ40 ደቂቃ ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 199. የሸንኩርት ካስታርድ ።

6 እንቁላል ፣ የተመታ
2 ኩባያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
½ ኩባያ ወተት
ፐርሰሜሎ ፣ የተከተፈ
ጨው

### አሠራር

1. ሽንኩርቱን በቅቤ ማቁላላት ።
2. እንቁላል ፣ ጨው ፣ ወተትና ሽንኩርት ማደባለቅ ።
3. የመጋገሪያውን ዕቃ ቅባት ቀብቶ ማዘጋጀት ።
4. የእንቁላሉን ድብልቅ መጋገሪያው ላይ መገልበጥ ።
5. መጋገሪያውን የፈላው ውኃ ላይ አድርጎ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ከአርባ አምስት እስከ ስድሳ ደቂቃ በእንፋሎት ማብሰል ።
6. በፐርሰሜሎ ቅጠል አጊጦ ማቅረብ ።

አምስት ሰው ይመግባል ።

## 200. የአሳማ ሥጋና የእንቁላል ሱፍሌ ።

5 እቁንላል ፣ አስኳሉና ዞፉ የተለየ
1 ኩባያ የአሳማ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
1 ኩባያ ወተት
ጨው
በርበሬ

### አሠራር

1. የእንቁላል አስኳሉን በደንብ መምታት ።
2. ቅቤ ፣ ጨው ፣ በርበሬ ፣ ወተትና የአሳማ ሥጋ ከእንቁላል አስኳል ጋር ማደባለቅ ።
3. የእንቁላሉን ዞፍ በወፍራሙ መምታት ።



4. በተራ ቁጥር 2 እና 3 የተዘጋጀውን ድብልቅ አዋሕዶ ሱፍሌ መጋገሪያ ላይ ማድረግ ።
5. መጋገሪያ ዕቃውን የፈላ ውኃ ላይ አስቀምጦ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ከሃያ እስከ ሠላሳ ደቂቃ በእንፋሎት ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 201. የእንቁላል ሰላጣ ።

6 እንቁላል ፣ የተቀቀለ
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 የሾርባ ማንኪያ ክሬም
½ የሻይ ማንኪያ ሰናፍጭ
ሚጥሚጣ
ጨው
ቅጠል ሰላጣ
ሽንኩርት

### አሠራር

1. የተቀቀለውን እንቁላል ሁለት ቦታ ቈርጦ አስኳሉን ማውጣት ።
2. አስኳሉን ከቅቤ ፣ ከጨው ፣ ከሰናፍጭ ፣ ከክሬም ፣ ከሚጥሚጣ ጋር ማዋሐድ ።
3. የእንቁላሉን ዞፍ በተደባለቀው አስኳል መሙላት ።
4. ቅጠል ሰላጣውን አጥቦ ዝርግ ሣህን ላይ ማስቀመጥ ።
5. የተሞላውን እንቁላል የተዘጋጀው ሰላጣ ላይ አድርጎ በሽንኩርት አጊጦ ማቅረብ ።

ከአራት እስከ ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 202. ፋሶሊያ በፎርማጆ ።

4 ኩባያ ፋሶሊያ ፣ የተቀቀለ
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
¾ ኩባያ ፎርማጆ

አሠራር

1. ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ በአንድ ላይ ማደባለቅ ።
2. ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ እስኪበስል ድረስ መቀቀል ።
3. በስሎ ሲወጣ ትኩሱን ማቅረብ ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመግባል ።

210. በምድጃ የበሰለ ጥቅል ጎመን ።

4 ኩባያ ጥቅል ጎመን ፣ የተቀቀለ
2 እንቁላል ፣ የተመታ
2 ኩባያ ወተት
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
ሚጥሚጣ

አሠራር

1. ጥቅል ጎመኑን ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ሚጥሚጣ እላዩ ላይ መነስነስ ።
2. እንቁላል ፣ ወተትና ጨው አደባልቆ ጎመኑ ላይ መጨመር ።
3. በብረት ድስት ውስጥ የፈላ ውኃ ጨምሮ እላዩ ላይ ጎመን ያለበትን መጋገሪያ ዕቃ ማስቀመጥ ።
4. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ አስገብቶ ለአርባ ደቂቃ በእንፋሎት ማብሰል ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

211. የተቀቀለ ጥቅል ጎመን ።

$\frac{1}{3}$ ኪሎ ጥቅል ጎመን
4 የሻይ ማንኪያ ጨው
4 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ

አሠራር

1. ጎመኑን አጥቦ መቁረጥ ።
2. የተቈረጠውን ጎመን ብረት ድስት ውስጥ ከውኃና ከጨው ጋር ጨምሮ ብረት ድስቱን ሳይከድኑ መቀቀል ።



3. ከአሥራ አምስት እስከ ሃያ ደቂቃ አብስሎ ፣ ውኃውን አጠንፍፎ ፣ ጎመኑ ላይ የሎሚ ጭማቂ ጨምሮ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

212. በምድጃ የበሰለ ካሮት ።

18 ትንንሽ ካሮት
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ቅቤ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ስኳር
1 የሻይ ማንኪያ ቀርንፉድ
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ውኃ
ጨው

አሠራር

1. ካሮቱን ልጦ ማጠብ ።
2. የተላጠውን ካሮት መጋገሪያ ዕቃ (ካሴሮል) ውስጥ መጨመር ።
3. ቅቤ ፣ ስኳር ፣ ጨውና ቀርንፉድ በደንብ አደባልቆ ውኃ ጨምሮ ማዋሐድ ።
4. በተራ ቊጥር 3 የተዘጋጀውን መቀላቅል ካሮቱ ላይ መጨመር ።
5. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአንድ ሰዓት ተኩል ማብሰል ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመግባል ።

213. ካሮትና አተር ።

2 ኩባያ ካሮት ፣ ተልጦ የተቀቀለ
2 ኩባያ አተር ፣ የተቀቀለ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
ፐርሰሜሎ
ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. የተቀቀለውን ካሮትና አተር ማደባለቅ ።
2. ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬና ቅቤ መጨመር ።
3. በፐርሰሜሎ አጊጦ ማቅረብ ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 214. የካሮትና የስዴኖ ሱፍሌ ።

1 ኩባያ ካሮት ፥ ተቀቅሎ የተፈጨ
½ ኩባያ ስዴኖ ፥ የተከተፈ
1 ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
¼ ኩባያ ወተት
2 የሾርባ ማንኪያ ሽንኩርት ፥ የተከተፈ
2 እንቍላል ፥ ዞፉና አስኳሉ የተለየ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
ቁንዶ በርበሬ

### አሠራር

1. የተፈጨውን ዳቦ በወተት ማራስ ።
2. ካሮት ፥ ሰዴኖ ፥ ሽንኩርትና አስኳሉን አደባልቆ በወተት ከራሰው ዳቦ ጋር ማዋሐድ ።
3. የእንቍላሉን ዞፍ እስኪወፍር ድረስ መምታት ፤ ጨውና ቁንዶ በርበሬ ጨምሮ ማደባለቅ ።
4. የተመታውን የእንቍላል ዞፍ በተራ ቍጥር2 ከተዘጋጀው የካሮት ድብልቅ ጋር አዋሕዶ የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
5. ሙቀቱ 350 ፋራንሃይት ድግሪ በሆነ ምድጃ ከሠላሳ እስከ አርባ ደቂቃ ማብሰል ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 215. ካሮት በፎርማጆ ።

3½ ኩባያ ካሮት ፥ ተቀቅሎ የተከተፈ
¾ ኩባያ ፎርማጆ
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፥ የቀለጠ
3 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
1½ ኩባያ ወተት
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
ትንሽ ሚጥሚጣ

### አሠራር

1. ቅቤና ዱቄቱን ማደባለቅ ።
2. ወተት ጨምሮ ማዋሐድ ።



3. እያማሰሉ እስኪወፍር ድረስ ማብሰል ።
4. ጨው ፥ ሚጥሚጣ ፥ ግማሽ ኩባያ ፎርማጆ መጨመር ።
5. ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ላይ ካሮቱን ማድረግ ።
6. ካሮቱ ላይ የተዘጋጀውን ሶስ መጨመር ።
7. ቀሪውን ፎርማጆ እላዩ ላይ ነስንሶ ሙቀቱ350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 216. የተቀቀለ የአበባ ጎመን ።

1½ ኪሎ የአባበ ጎመን
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
ቁንዶ በርበሬ ፥ ቅቤ ፥ የፈላ ውኃ

### አሠራር

1. የአበባ ጎመኑን ጨው የገባበት ቀዝቃዛ ውኃ ውስጥ ለሠላሳ ደቂቃ መዘፍዘፍ ።
2. የተዘፈዘፈውን የአበባ ጎመን በውኃ አለቅልቆ ብረት ድስት ውስጥ መጨመር ።
3. ጨውና የፈላ ውኃ ጨምሮ ከሃያ እስከ ሠላሳ ደቂቃ ማብሰል ።
4. ቁንዶ በርበሬና ቅቤ ጨምሮ ማቅረብ ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 217. የአበባ ጎመን ፍሪተር—ኮተሌት ።

1 ኩባያ የአበባ ጎመን ፥ ተቀቅሎ የተከተፈ
1 እንቍላል ፥ የተመታ
1 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት ፥ የተነፋ
1 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
½ ኩባያ ወተት
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፥ የቀለጠ
ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. እክራውን አጥቦ መክተፍ ።
2. ሽንኩርቱን ከቅቤው ጋር ማቁላላት ።
3. እክራውን ጨምሮ ለአምስት ደቂቃ ማብሰል ።
4. ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ውስጥ እክራውን መጨመር ።
5. የቲማቲም ሶስ ፣ ጨው ቁንዶ በርበሬና ፐርሰሜሎ አደባልቆ እክራው ላይ መጨመር ።
6. ሙቀቱ ድግሪ 350 ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለሠላሳ ደቂቃ ማብሰል ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመገባል ።

225. አተርና ሽንኩርት ።

3 ኩባያ አተር ፣ የተቀቀለ
1 ኩባያ ደቃቅ ሽንኩርት ፣ የተቀቀለ
3 የሾርባ ማንኪያ ክሬም
½ የሻይ ማንኪያ ስኳር

አሠራር

1. አተር ፣ ሽንኩርት ፣ ክሬምና ስኳር ማደባለቅ ።
2. ድብልቁን ብረት ድስት ውስጥ እያማሰሉ በደንብ ማፍላት ።
3. ክሬሙ ከአተርና ከሽንኩርት ጋር በደንብ ከተዋሐደ በኋላ አውጥቶ ትኩሱን ማቅረብ ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመገባል ።

226. አተር በፎርማጆ ።

4 ኩባያ አተር ፣ የተቀቀለ
1 ኩባያ ፎርማጆ
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 ኩባያ ወተት
2 የሾርባ ማንኪያ ቲማቲም ፣ የተከተፈ
ቁንዶ በርበሬ



አሠራር

1. አተሩን ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
2. ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬና ወተት አደባልቆ መጨመር ።
3. ፎርማጆና ቲማቲሙን እላዩ ላይ መነስነስ ።
4. ሙቀቱ 400 ድግሪ ፈራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሃያ ደቂቃ ወይም ፎርማጆው እስኪቀልጥ ድረስ ማብሰል ።

ስምንት ሰው ይመገባል ።

227. አተር በሽንኩርትና በቅቤ ።

3½ ኩባያ አተር ፣ የተቀቀለ
1 ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
5 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
¼ የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
½ የሻይ ማንኪያ ነጭ ሽንኩርት ፣ የተፈጨ

አሠራር

1. ሽንኩርቱን በመጠኑ በቅቤ እያቁላሉ ማብሰል ።
2. ቁንዶ በርበሬ ፣ ጨው ፣ ነጭ ሽንኩርትና አተር ጨምሮ ከድኖ በመጠኑ ማንተክተክ ።
3. በደንብ ከተዋሐደ በኋላ ትኩሱን ማቅረብ ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመገባል ።

228. በቆሎ የተሞላ ቃሪያ ።

6—8 የፈረንጅ ቃሪያ
2 ኩባያ በቆሎ፣የተቀቀለ
¾ የሻይ ማንኪያ ጨው
½ ኩባያ ፎርማጆ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
¼ ኩባያ የወይራ ፍሬ፣የተከተፈ
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

3. ወተት ፣ ቅቤ ፣ ጨውና ቁንዶ በርበሬ ከተፈጨ ድንችና ካሮት ጋር በደንብ ማዋሐድ ።
4. መጋገሪያ ዕቃውን (ካሴሮል) ቅቤ ቀብቶ ማዘጋጀት ።
5. የተቀቀለውን ድንችና ካሮት መጋገሪያ ዕቃው ላይ ማድረግ ።
6. ሙቀቱ 300 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሃያ ደቂቃ ማብሰል።
7. ከቲማቲም ሶስ ጋር ማቅረብ ።

አራት ሰው ይመግባል ።

## 235. የተቀቀለ ድንች ።

700 ግራም ድንች
¼ ኩባያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
250 ግራም ፋሶሊያ
2 የሻይ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
ቁንዶ በርበሬ ፣ ፐርሰሜሎ ፣ ጨው

አሠራር

1. ድንቹን ልጦ በስሱ መክተፍ ።
2. የተከተፈውን ድንች ጨው በገባበት ውኃ መቀቀል ።
3. ፋሶሊያውን በአጭሩ ቀንጥሶ ማጠብ ።
4. የታጠበውን ፋሶሊያ ጨው በገባበት ውኃ መቀቀል ።
5. የተቀቀለውን ድንችና ፋሶሊያ ማደባለቅ ።
6. ቅቤ ፣ የሎሚ ጭማቂ ፣ ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬና ፐርሰሜሎ ከድንችና ከፋሶሊያው ጋር አደባልቆ የመቀቀያውን ውኃ እስኪመጥ ድረስ ከድኖ ማብሰል ።

ለድስት ሰው ይመግባል ።

## 236. ድንችና ፎርማጆ ።

8 ድንች ፣ የተቀቀለ
½ ኩባያ ፎርማጆ
¼ ኩባያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ



አሠራር

1. ድንቹን አጥቦ መቀቀል ።
2. የተቀቀለውን ድንች መላጥ ።
3. ቅቤ ፣ ፎርማጆ ፣ ጨውና ቁንዶ በርበሬ ከድንቹ ጋር ማደባለቅ ።
4. የተደባለቀውን ድንችና ፎርማጆ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ሙቀቱ 400 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 237. ድንች በፉርኖ ዱቄትና በቅቤ ።

6 ድንች ፣ ተቀቅሎ የተቈረጠ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
2 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
¼ የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
2 ኩባያ ወተት
የሎሚ ጭማቂ

አሠራር

1. ቅቤውን ማቅለጥ ።
2. ዱቄት ፣ ጨውና ቁንዶ በርበሬ ከቀለጠው ቅቤ ጋር ማደባለቅ ።
3. ወተቱን የተደባለቀው ዱቄት ውስጥ ጨምሮ እያማሰሉ እስኪወፍር ድረስ ማብሰል ።
4. የሎሚ ጭማቂውንና ድንቹን ጨምሮ እስኪወፍር ማንተክተክ ።
5. ሲበስል አውርዶ ትኩሱን ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 238. ድንች በነጭ ሶስ ።

6 ራስ ድንች
1½ ኩባያ መካከለኛ ነጭ ሶስ
2 የሻይ ማንኪያ ጨው

1 ኩባያ ውኃ
ዘይት ወይም የቀለጠ ቅቤ
ፐርስሜሎ

አሠራር

1. ድንቹን አጥቦ መላጥ ።
2. የተላጠውን ድንች ዘይት ወይም ቅቤ መቀባት ።
3. የተቀባውን ድንች መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
4. ድንች ያለበት መጋገሪያ ዕቃ ውስጥ ውኃና ጨው ጨምሮ መክደን ።
5. ሙቀቱ 300 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለግማሽ ሰዓት ማብሰል።
6. የበሰለው ድንች ላይ ትኩስ ነጭ ሰስ መጨመር ።
7. በፐርስሜሎ አጊጦ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

239. ድንችና ፐርስሜሎ ።

ከ8—10 ራስ ድንች
½ ኩባያ ወተት
1 የሾርባ ማንኪያ ፐርስሜሎ ፡ የተከተፈ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ድንቹን ቀቅሎ መላጥ ።
2. የተላጠውን ድንችና ወተት ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ ድንቹ ወተቱን እስኪመጥ ድረስ ከድኖ ማብሰል ።
3. ቁንዶ በርበሬ ፡ ጨው ፡ ቅቤና ፐርስሜሎ ጨምሮ ለጥቂት ደቂቃ ዎች ማብሰል ።

አራት ሰው ይመግባል ።



240. ዶል ሞኒከ ድንች ።

2 ኩባያ ድንች ፡ ተቀቅሎ የተከተፈ
2 ኩባያ መካከለኛ ነጭ ሰስ
¼ የሻይ ማንኪያ በሶብላ
ጨው
ቁንዶ በርበሬ
የተፈጨ ዳቦ

አሠራር

1. ድንቹን ቀቅሎ መላጥ ።
2. የተላጠውን ድንች መከተፍ ።
3. የተከተፈውን ድንች ፡ ከነጭ ሰስ ፡ ከበሶብላ ፡ ከጨውና ከቁንዶ በር በሬ ጋር ማደባለቅ ።
4. የድንቹን ድብልቅ የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
5. የተፈጨውን ዳቦ ድንቹ ላይ ነስንሶ ሙቀቱ 450 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

አራት ሰው ይመግባል ።

241. የሩስያ ድንች ።

4 መካከለኛ ድንች
1 ትንሽ ሽንኩርት ፡ የተከፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
3 የሾርባ ማንኪያ ክሬም
የፈላ ውኃ
ቁንዶ በርበሬ
ጨው

አሠራር

1. ድንቹን ልጦ መከተፍ ።
2. የተከተፈውን ድንች ፡ ሽንኩርት ፡ ጨው ፡ ቁንዶ በርበሬና ውኃ ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ ከድኖ ማብሰል ።

## አሠራር

1. ድንቹን ልጦ ማጠብ ።
2. የተላጠውን ድንች ከሽንኩርትና ከቃሪያ ጋር አድርጎ በሥጋ መፍጫ መፍጨት ።
3. ጨው፡ቁንዶ በርበሬ፡እንቍላል ከተፈጨው ድንች ጋር ማደባለቅ ።
4. ቅቤውን በመጥበሻ ላይ አሙቆ የድንቹን ድብልቅ ጨምሮ እያገላበጡ እስኪበስል መጥበስ ።

ከሦስት እስከ አራት ሰው ይመግባል ።

## 252. የዳች የድንች ዳምፕሊንግ ።

9 መካከለኛ ድንች
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
3 እንቍላል ፡ በደንብ የተመታ
1 ኩባያ የፋርኖ ዱቄት ፡ የተነፋ
$\frac{2}{3}$ ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ገውዝ
1 ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
2 የሾርባ ማንኪያ ሽንኩርት

### አሠራር

1. ድንቹን ቀቅሎ ከተላጠ በኋላ መፍጨት ።
2. የተፈጨውን ድንች ፡ ጨው ፡ እንቍላል ፡ የተፈጨ ዳቦ ፡ ዱቄትና ገውዙን ማደባለቅ ። ድብልቁ የላላ ከሆነ ተጨማሪ የተፈጨ ዳቦ መጨመር ።
3. የድንቹን ድብልቅ በመጠኑ እየቆነጠሩ በእጅ ማድቦልቦል ።
4. የተድቦለቦለውን የድንች ድብልቅ ጨው በገባበት ውኃ ውስጥ ለአምስት ደቂቃ ቀቅሎ ከውኃ ውስጥ ማውጣት ።
5. የተፈጨውን ዳቦና ሽንኩርት በቅቤ አቁላልቶ አጋም ሲመስል ማውጣት ።
6. የተቀቀለው የድንች ድብልቅ ላይ የበሰለውን ሽንኩርትና የተፈጨ ዳቦ ድብልቅ ጨምሮ ማቅረብ ።

አሥራ ሁለት ሰው ይመግባል ።



## 253. አይሪሽ ዳምፕሊንግ ።

5 ኩባያ ድንች ፡ ተቀቅሎ የተፈጨ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ድንች ፡ ያልተቀቀለና በደቃቁ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ዘይት
1 የሾርባ ማንኪያ ሽንኩርት ፡ የተከተፈ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{3}{4}$ ኩባያ የፋርኖ ዱቄት
2 እንቍላል ፡ በመጠኑ የተመታ

### አሠራር

1. ዘይቱ መጥበሻ ላይ ሲሞቅ ሽንኩርት ጨምሮ ማቁላላት ።
2. በደቃቁ የተከተፈውን ድንች ጨምሮ ከሽንኩርቱ ጋር ማብሰል ። ሲቀዘቅዝ የተፈጨውን ድንች ፡ ጨው ፡ ዱቄትና እንቍላል ጨምሮ ማዋሐድ ።
3. የተደባለቀውን ድንች በመጠኑ እየቆነጠሩ በእጅ በስሱ ማድቦልቦል ።
4. የተድቦለቦለውን ድንች ጨው በገባበት የፈላ ውኃ ውስጥ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።
5. ከበሰለ በኋላ ከመቀቀያው ውኃ ውስጥ ወዲያው ማውጣት ።

አምስት ሰው ይመግባል ።

## 254. የተፈጨ ድንች ።

6 ድንች
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ወተት የፈላ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

### አሠራር

1. ድንቹን ቀቅሎ መላጥ ።
2. የተላጠውን ቅቅል ድንች ጐድጓዳ ሣህን ውስጥ ጨምሮ በጭልፋ እየተጫኑ ወይም በመፍጫ መሣሪያ ማላም ።

3. ቅቤ ፥ ወተት ፥ ጨውና ቁንዶ በርበሬ ጨምሮ እስኪበስል ድረስ በማንኪያ እያማሰሉ ማዋሐድ ።
4. ትኩሱን ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

255. ድንች በሽንኩርት ፥ ቍጥር 2 ።

8 ድንች
6 ሽንኩርት
6 ካሮት
½ ኩባያ ወተት
2—4 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
ጨው ፥ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ሽንኩርት ፥ ካሮትና ድንቹን ልጦ መክተፍ ።
2. የተከተፈውን ሽንኩርት ፥ ድንችና ካሮት ጨው በገባበት ውኃ መቀቀል ።
3. የበሰለውን ሽንኩርት ፥ ከካሮትና ከድንች ጋር አደባልቆ መፍጨት ።
4. ጨው ፥ ቁንዶ በርበሬ ፥ ወተትና ቅቤ ጨምሮ በደንብ ከተደባለቀ በኋላ በብረት ድስት መጣድ ።
5. በደንብ እስኪዋሐድ ድረስ እያማሰሉ ለአሥራ አምስት ደቂቃ እሳት ላይ ማቆየት ።
6. ትኩሱን ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

256. የተፈጨ ድንች በፎርማጆና በተፈጨ ዳቦ ።

6 ድንች ፥ ተቀቅሎ የተፈጨ
½ ኩባያ ፎርማጆ
½ ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
½ የሻይ ማንኪያ ሚጥሚጣ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
2 እንቍላል ፥ በደንብ የተመታ



አሠራር

1. ቅቤ፥ጨው፥ሚጥሚጣና እንቍላል ከተፈጨ ድንች ጋር ማደባለቅ ።
2. የድንቹን ድብልቅ ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ላይ ማድረግ ።
3. ድንቹ ላይ ፎርማጆውን ከዚያም የተፈጨውን ዳቦ መጨመር ።
4. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ወይም አጋም እስኪመስል ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

257. የተፈጨ ድንች በዓሣ ።

2 ኩባያ የተፈጨ ድንች
2 ኩባያ የከራብ ወይም የዓሣ ሥጋ፥የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
2 የሾርባ ማንኪያ የፋርኖ ዱቄት
1 ኩባያ ወተት ፥ ለብ ያለ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
½ ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. የተፈጨውን ድንች ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ (ካሴሮል) ላይ ማድረግ ።
2. ቅቤውን አቅልጦ ከዱቄቱ ጋር ማደባለቅና ቀስ በቀስ ወተቱን ጨምሮ እያማሰሉ ማሞቅ ።
3. ጨው ፥ ቁንዶ በርበሬና የከራብ ወይም የዓሣ ሥጋ ጨምሮ ለሦስት ደቂቃ አብስሎ የተፈጨው ድንች ላይ መጨመር ።
4. የተፈጨውን ዳቦ እላዩ ላይ መነስነስ ።
5. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ከሃያ እስከ ሠላሳ ደቂቃ ማብሰል ።

አራት ሰው ይመግባል ።

258. ድንች በእንቍላልና በቤከን ።

4 ኩባያ ድንች ፥ ተቀቅሎ የተፈጨ
12 በስሱ የተቈረጠ ቤከን

አሠራር

1. ስኳር ድንቹን ልጦ በስሱ በቁመቱ መቁረጥ ።
2. የተቈረጠውን ስኳር ድንች ለአሥራ አምስት ደቂቃ መቀቀል ።
3. የተቀቀለውን ስኳር ድንች ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ (ካሴሮል) ላይ ማድረግ ።
4. ማር ፥ የብርቱካን ጭማቂና ጨው አደባልቆ ስኳር ድንቹ ላይ መጨመር ።
5. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሠላሳ ደቂቃ ማብሰል።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

265. ስኳር ድንች በሙዝ ።

6 መካከለኛ ስኳር ድንች
3 ሙዝ
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 ኩባያ የፈላ ውኃ
ዝንጅብል

አሠራር

1. ስኳር ድንቹን ቀቅሎ መላጥ ።
2. የተላጠውን ስኳር ድንች በስሱ መክተፍ ።
3. ሙዙን ልጦ በስሱ መክተፍ ።
4. ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ላይ ስኳር ድንቹንና ሙዙን በየተራ መጨመር ።
5. ቅቤ ፥ ትንሽ ዝንጅብልና ውኃ ጨምሮ መክደን ።
6. ሙቀቱ 400 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሃያ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።
7. ክዳኑን ክፍቶ አጋም እስኪመስል ምድጃው ውስጥ ማቆየት ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

266. ስኳር ድንች በአሳማ ሥጋ ።

3 ስኳር ድንች
1 በስሱ የተቈረጠ የአሳማ ሥጋ



2 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
1 ኩባያ የፈላ ውኃ

አሠራር

1. ስኳር ድንቹን ቀቅሎ መላጥ ።
2. የተላጠውን ስኳር ድንች በስሱ መቁረጥ ።
3. የአሳማ ሥጋውን አጋም እስኪመስል መጥበስ ።
4. የተጠበሰውን የአሳማ ሥጋ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
5. የአሳማ ሥጋው ላይ ስኳር ድንቹን ጨምሮ በስኳር ድንቹ ላይ ስኳር መነስነስ ።
6. ውኃ ጨምሮ መክደን ።
7. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ማብሰል ፤ ውኃውን ሲመጥ ትንሽ ውኃ መጨመር ።
8. የአሳማ ሥጋው ወደ መብሰሉ ሲቃረብ የመጋገሪያውን ዕቃ ክዳን ከፍቶ አጋም እስኪመስል ምድጃው ውስጥ ማቆየት ።

ከሦስት እስከ አራት ሰው ይመግባል ።

267. ስኳር ድንች በቤከንና በፎርማጆ ።

$1\frac{1}{2}$ ኪሎ ስኳር ድንች ፥ የተቀቀለ
120 ግራም ቤከን ፥ የተከተፈ
1 ትንሽ ሽንኩርት ፥ የተከተፈ
6 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 ኩባያ መረቅ
1 ኩባያ የቲማቲም ሳልሳ
ፎርማጆ

አሠራር

1. ቤከኑንና ሽንኩርቱን በቅቤ ማቁላላት ።
2. የተቀቀለውን ስኳር ድንች ልጦ በወፍራሙ በቁመቱ መቁረጥ ።
3. ስኳር ድንቹን ከተቁላላው ቤከንና ሽንኩርት ጋር አደባልቆ አሥር ደቂቃ ማብሰል ።
4. መረቁንና ሳልሳውን ጨምሮ ለተጨማሪ ሃያ ደቂቃ ማብሰል ።
5. ፎርማጆውን እላዩ ላይ ነስንሶ ማቅረብ ።

አሥር ሰው ይመግባል ።

4. መረቁን አፍልቶ ዱቄቱንና ውኃውን አደባልቆ መጨመርና እያማሰሉ ለአምስት ደቂቃ ከበሰለ በኋላ የዶሮ ሥጋው ላይ መጨመር ።
5. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሠላሳ ደቂቃ ማብሰል።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 275. የተፈጨ ስኳር ድንች ።

6 መካከለኛ ስኳር ድንች ፣ የተቀቀለ
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ትኩስ ወተት
ትንሽ ገውዝ

### አሠራር

1. ስኳር ድንቹን ቀቅሎ መላጥ ።
2. የተላጠውን ስኳር ድንች ከቅቤና ከወተት ጋር መፍጨት ።
3. ደረቅ የሚል ከሆነ ወተት መጨመር ።
4. ከተፈለገም ትንሽ ገውዝ ጨምሮ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 276. ስኳር ድንች በብርቱካን ።

2 ኩባያ ስኳር ድንች ፣ ተቀቅሎ የተፈጨ
3 ብርቱካን
$\frac{1}{2}$ ኩባያ የብርቱካን ጭማቂ
6 በስሎ የተቈረጠ እናናስ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው

### አሠራር

1. ስኳር ድንች ፣ ቅቤ ፣ ጨውና የብርቱካን ጭማቂውን ማደባለቅ ።
2. ብርቱካኑን በክቡ ሁለት ቦታ መቍረጥና ውስጡን ቦርቡሮ ማውጣት ።
3. የብርቱካኑን ቀፎ በስኳር ድንች ድብልቅ መሙላት ።



4. የተቈረጠውን እናናስ ስኳር ድንቹ ላይ መሰካት ።
5. የተሞላውን ብርቱካን መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ሙቀቱ 400 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 277. የስኳር ድንች ፓፍ ።

2 ኩባያ የስኳር ድንች ፣ ተቀቅሎ የተፈጨ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ወተት ወይም ክሬም
1 እንቍላል ፣ አስኳሉና ዞፉ የተለየ
ጨው
ቁንዶ በርበሬ

### አሠራር

1. የተፈጨ ስኳር ድንች ፣ ቅቤ ፣ ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬና ወተት ማደባለቅ
2. አስኳሉን በደንብ መምታትና በተራ ቍጥር 1 ከተዘጋጀው የስኳር ድንች ድብልቅ ጋር ማዋሐድ ።
3. የእንቍላሉን ዞፍ እስኪወፍር ድረስ መምታት ።
4. የተመታውን የእንቍላል ዞፍና የስኳር ድንቹን ድብልቅ አዋሕዶ ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ (ካሴሮል) ላይ ማድረግ ።
5. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሠላሳ ደቂቃ ወይም እጋም እስኪመስል ድረስ ማብሰል ።

አራት ሰው ይመግባል ።

## 278. በምድጃ የበሰለ የቆስጣና—እስፒናች—የፋርኖ ዱቄት ድብልቅ።

1 ኪሎ ቆስጣ—እስፒናች
6 የሾርባ ማንኪያ የፋርኖ ዱቄት
5 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ የቀለጠ
1 ኩባያ ወተት
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
4 የሾርባ ማንኪያ ፎርማጆ
$\frac{3}{4}$ ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. የአሳማ ሥጋ ፣ ማዮኔዝና ሽንኩርት ማደባለቅ ።
2. ቲማቲሙ ከታጠበ በኋላ ውስጡን ቦርቡሮ ፍሬውን ማውጣት ።
3. እያንዳንዱን ቲማቲም አራት ቦታ በስሱ መቁረጥ ።
4. የተደባለቀውን የአሳማ ሥጋ ግማሹ ቲማቲም ላይ ማድረግ ።
5. በቀሪው ግማሽ ቲማቲም ደግሞ የአሳማ ሥጋውን መሸፈን ።
6. በማዮኔዝና በፐርሰሜሎ ቅጠል ማጌጥ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 282. የተሞላ እንቁላል ።

8 እንቁላል ፣ የተቀቀለ
1 ኩባያ የአሳማ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ የሰዴኖ ቅጠል ፣ በደቃቁ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ አቻሎኒ ፣ ተፈልፍሎ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ቃሪያ ፣ ተከትፈ
1 የሻይ ማንኪያ ሰናፍጭ
ማዮኔዝ ፣ ጨው
ቅጠል ሰላጣ

አሠራር

1. የተቀቀለውን እንቁላል ልጦ ሁለት ቦታ በቁመቱ መቁረጥ ።
2. አስኳሉን ለብቻ አውጥቶ ማድቀቅ ።
3. የአሳማሥጋ ፣ የሰዴኖ ቅጠል ፣ አቻሎኒ ፣ ቃሪያ ፣ ሰናፍጭ ፣ ጨውና ማዮኔዝን ከእንቁላል አስኳሉ ጋር በደንብ ማደባለቅ ።
4. የእንቁላሉን ዞፍ በተራ ቁጥር 3 የተዘጋጀውን የአሳማ ሥጋ ድብልቅ መሙላት ።
5. ሰላጣ ቅጠሉን አጥቦ ሣሀን ላይ ከተዘጋጀ በኋላ የተሞላውን እንቁላል ለዓይን በሚስብ ሁኔታ መደርደር ።
6. የተሞላው እንቁላል ላይ ትንሽ በርበሬ ነስንሶ ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።



## 283. አይብና ካሮት ።

75 ግራም አይብ
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ካሮት ፣ የተከተፈ
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሾርባ ማንኪያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
ትንሽ ሚጥሚጣ
የፐርሰሜሎ ቅጠል

አሠራር

1. አብይብና ካሮት ማደባለቅ ።
2. ጨው ፣ ሚጥሚጣና ሽንኩርት ድብልቁ ውስጥ መጨመር ።
3. በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተዘጋጀውን ድብልቅ በደንብ አዋሕዶ የካሮት ቅርጽ እንዲይዝ አድርጎ ማድቦልቦል ።
4. ቅርጹን እንዲጠብቅ በረዶ ቤት ውስጥ ማቀዝቀዝ ።
5. የፐርሰሜሎውን ቅጠል ከጫፉ በኩል በመሰካት ካሮት አስ መስሎ ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 284. ጣፋጭና ጉምዛዛ መከሰስ ።

1 ኩባያ መረቅ ፣ የዶሮ ወይም የሥጋ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ኮምጣጤ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ስኳር
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኪሎ ዓሣ ፣ የተጠበሰ
ጨው ፣ በርበሬ

አሠራር

1. መረቅ ፣ ኮምጣጤ ፣ ስኳር ፣ ጨው ፣ በርበሬና ሽንኩርት ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ ማደባለቅ ።
2. የተደባለቀውን እሳት ላይ ጥዶ አለማቋረጥ እያማሰሉ እስኪ ወፍር ድረስ ማብሰል ።
3. የበሰለውን ስስ የተጠበሰው ዓሣ ላይ ጨምሮ ማቅረብ ።

285. ጥቅል የአሳማ ሥጋ—ቤከን ።

8 ቍራጭ በስሱ የተቈረጠ የአሳማ ሥጋ—ቤከን
4 የሾርባ ማንኪያ አቾሎኒ ፣ የተፈጨ

አሠራር

1. የተቈረጠውን የአሳማ ሥጋ አቾሎኒ መቀባት ።
2. አቾሎኒ የተቀባውን የአሳማ ሥጋ ጠበቅ አድርጎ መጠቅለልና በክር ማሰር ።
3. ምድጃ ውስጥ ጨምሮ ማብሰል ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

286. የሙዝ ስካሎፕ በእንቍላል—የተጠበሰ ሙዝ ።

1 እንቍላል
1½ የሻይ ማንኪያ ጨው
6 ሙዝ ፣ በመጠኑ የበሰለ
¾ ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
ዘይት ፣ ለመጥበሻ የሚሆን

አሠራር

1. እንቍላሉ በመጠኑ ከተመታ በኋላ ጨው ጨምሮ ማደባለቅ ።
2. ሙዙን ልጦ በቁመቱ መሰንጠቅ ።
3. ሙዙን የተመታው እንቍላል ውስጥ መንከር ።
4. እንቍላል ውስጥ የተነከረው ሙዝ ላይ የተፈጨ ዳቦ ነስንሶ በፈላ ዘይት መጥበስ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

287. የቤከንና የአይብ መከሰስ ።

¼ ኪሎ አይብ
4 ቍራጭ በስሱ የተቈራረጠ ቤከን—የአሳማ ሥጋ
8 ቍራጭ በስሱ የተቈረጠ በእሳት የደረቀ ዳቦ ።



አሠራር

1. ቤከኑን በጣም አድቅቆ መክተፍ ።
2. አይቡንና የተከተፈውን ቤከን ማደባለቅ ።
3. የአይቡንና የቤከኑን ድብልቅ በዳቦ ላይ መቀባት ።
4. የተቀባውን ዳቦ ሙቀቱ መጠነኛ በሆነ ምድጃ ማብሰል ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

288. የስዊድሽ እንቍላል ።

8 እንቍላል ፣ የተቀቀለ
1 የእንቍላል ዘፍ ፣ በመጠኑ የተመታ
½ ኪሎ ሶሴጅ
የተፈጨ ዳቦ

አሠራር

1. የተቀቀለውን እንቍላል መላጥ ።
2. የእንቍላሉን ዘፍ በመጠኑ ከተመታ በኋላ የተላጠውን እንቍላል መቀባት ፣
3. እንቍላሉን በሶሴጅ መጠቅለል ።
4. የተፈጨውን ዳቦ የተጠቀለለው እንቍላል ላይ ነስንሶ በፈላ ዘይት መጥበስ ።
5. የተጠበሰውን እንቍላል በቁመቱ ሁለት ቦታ ቈርጦ ትኩሱን ማቅረብ ።

289. በአሳማ ሥጋ የተጠቀለለ ሙዝ ።

6 በስሎ የተከተፈ የአሳማ ሥጋ
6 ሙዝ ፣ በመጠኑ የበሰለ
ሰናፍጭ
ፎርማጆ

አሠራር

1. ሰናፍጩን የአሳማ ሥጋው ላይ መነስነስ ።
2. ሙዙን ሰናፍጭ በተነሰነሰበት የአሳማ ሥጋ መጠቅለል ።

አሠራር

1. ቅቤና ዱቄቱን አደባልቆ ወተት፣ ጨው፣ ቁንዶ በርበሬና ፎርማጆ መጨመር ።
2 እያማሰሉ እስኪወፍር ማብሰል ።
3 ከበሰለ በኋላ አውጥቶ ሲቀዘቅዝ በደንብ ከተመታ የእንቁላል አስኳል ጋር ማደባለቅ ።
4. የእንቁላሉን ዞፎ እስኪወፍር ድረስ መትቶ በተራ ቁጥር 3 ከተ ዘጋጀው ድብልቅ ጋር በዝግታ ማዋሐድ ።
5. ሱፍሌውን ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ውስጥ ገልብጦ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ከሃምሳ እስከ ስድሳ ደቂቃ ማብሰል ።
6. ከበሰለ በኋላ አውጥቶ ትኩሱን ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

294. አቾሎኒ በአትክልት ።

½ ኩባያ አቾሎኒ ፣ ተፈልፍሎ የተከተፈ
1 ኩባያ ቲማቲም ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
1 ኩባያ አተር ፣ የተቀቀለ
1 ኩባያ ካሮት ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
3 የሾርባ ማንኪያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
1 ኩባያ ዳቦ ፣ የተፈጨ
½ ኩባያ ወተት
2 እንቁላል ፣ የተመታ
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ከላይ የተዘረዘሩትን መቀላቅሎች በሙሉ ማደባለቅ ።
2. መጋገሪያ ዕቃውን ዘይት ወይም ቅቤ መቀባት ።
3. መጋገሪያው ላይ ድብልቁን በሙሉ ግልብጦ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሠላሳ ደቂቃ አብስሎ ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።



295. ዳቦ ላይ የሚቀባ ሶስ ።

1 ኪሎ ፎርማጆ
8 የደረቀ ዳቦ
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
½ የሻይ ማንኪያ ሚጥሚጣ
1 የሻይ ማንኪያ ሰናፍጭ
1 ኩባያ ቢራ
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ፎርማጆውንና ቅቤውን ብረት ድስት ውስጥ አድርጎ የፈላ ውኃ ላይ በእንፋሎት ማቅለጥ ።
2. ጨው ፣ ሚጥሚጣ ፣ ሰናፍጭ ፣ ቁንዶ በርበሬና ቢራ ጨምሮ እስኪለደልድ እያማሰሉ ማብሰል ።
3. ዳቦውን በስሱ ቈርጦ ምጣድ ላይ ወይም በዳቦ መጥበሻ ላይ ማድረቅ ።
4. የተዘጋጀውን ሶስ የደረቀውን ዳቦ ቀብቶ ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

296. የእንጉዳይ ሶስ ።

¼ ኩባያ እንጉዳይ ፣ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
2 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
1 ኩባያ የዶሮ መረቅ
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ቅቤውን ማቅለጥ ።
2. እንጉዳዩን ጨምሮ ለአምስት ደቂቃ ማብሰል ።
3. ዱቄቱን ጨምሮ ማዋሐድ ።
4. የዶሮውን መረቅ ጨምሮ እስኪለደልድ እያማሰሉ ማንተክተክ ።
5. ጨውና ቁንዶ በርበሬ ጨምሮ ትኩሱን ማቅረብ ።
6. በዶሮ መረቅ ፈንታ ወተት ወይም ክሬም መጠቀም ይቻላል ።

## 297. ፎርማጆ የተቀባ ደረቅ ዳቦ ።

8 የተቈረጠ ዳቦ
2 ኩባያ ፎርማጆ
2 እንቍላል ፤ የተመታ
3 የሾርባ ማንኪያና ክሬም
3 የሾርባ ማንኪያ የፋርኖ ዱቄት
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

### አሠራር

1. እንቍላል ፤ ክሬም ፤ ዱቄት ፤ ፎርማጆ ፤ ጨውና ቁንዶ በርበሬ ማደባለቅ ።
2. የተቈረጠውን ዳቦ የተዘጋጀው ድብልቅ ውስጥ መንከር ።
3. የተነከረውን ዳቦ በዘይት እያገላበጡ መጥበስ ።

## 298. በፎርማጆ የተጠቀሰለ ዳቦ ።

2 ዳቦ ፤ የተቈረጠ
½ ኩባያ ፎርማጆ
1 እንቍላል
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 ማንኪያ ቅቤ ፤ የቀለጠ

### እሠራር

1. ዳቦውን በአራት ማዕዘን በትንሹ መቍረጥ ።
2. እንቍላል ፤ ጨውና ቅቤ ማደባለቅ ።
3. የተቈረጠውን ዳቦ በተራ ቍጥር 2 በተዘጋጀው የእንቍላል ድብልቅ ውስጥ መንከር ።
4. ፎርማጆውን የተነከረው ዳቦ ላይ መነስነስ ።
5. ዳቦውን መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራን ሃይት በሆነ ምድጃ ፎርማጆው እስኪቀልጥ ድረስ ማብሰል ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።



## 299. ቺዝ ፓፍ ።

1 ዳቦ
100 ግራም ፎርማጆ
¼ የሻይ ማንኪያ ቤክንግ ፓውደር
1 እንቍላል ፤ አስኳልና ዞፉ የተለየ
ቅቤ

### እሠራር

1. ዳቦውን በክቡ ቈርጦ በአንድ ወገን ብቻ ማድረቅ ።
2. እሳት ያልነካውን ሌላውን ወገን ቅቤ መቀባት ።
3. ፎርማጆ ፤ ቤኪንግ ፓውደርና የእንቍላሉን አኳስል በደንብ ማደባለቅ ።
4. የእንቍላሉን ዞፍ እስኪወፍር ድረስ በደንብ መምታት ።
5. በተራ ቍጥር 3 የተዘጋጀውን ድብልቅ ከእንቍላል ዞፉ ጋር ማደባለቅ ።
6. የእንቍላሉን ድብልቅ ቅቤ የተቀባው ዳቦ ላይ መርጎ መጋገሪያው ዕቃ ላይ ማኖር ።
7. የተዘጋጀውን ዳቦ ሙቀቱ መጠነኛ በሆነ ምድጃ ውስጥ ማብሰል ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 300. የዳቦና የቺዝ ሽሽክባብ ።

1 ዳቦ ፤ የተቈረጠ
½ ኪሎ ቺዝ ፤ በስሎ የተቈረጠ
1½ ኩባያ ወተት
⅓ ኩባያ የፋርኖ ዱቄት
2 እንቍላል ፤ እስኳሉ
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሾርባ ማንኪያ ውኃ
የቲማቲም ሶስ

$\frac{1}{2}$ ኩባያ ክሬም
$1\frac{1}{2}$ የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው

### አሠራር

1. ወተት ፥ ክሬምና ቅቤ አደባልቆ ትንሽ ሞቅ ማድረግ ።
2. ጨውና ዳቦ ጨምሮ ለአምስት ደቂቃ ማስቀመጥ ።
3. በመጠነኛ እሳት ላይ ጥዶ ወተቱን እስከሚመጥ ድረስ ማን ተክተክ ።
4. በትኩሱ ማቅረብ ።

አራት ሰው ይመግባል ።

## 305. አፕል—ፖም—በዳቦ ።

3 ኩባያ የተከተፈ አፕል—ፖም
$1\frac{1}{2}$ ኩባያ ዳቦ ፥ የተፈጨ
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ስኳር
1 የሻይ ማንኪያ ቀረፋ ፥ የተፈጨ
4 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፥ የቀለጠ
$\frac{3}{4}$ ኩባያ ውኃ

### አሠራር

1. አፕል ፥ አንድ ኩባያ የተፈጨ ዳቦ ፥ ስኳርና ቀረፋ ማደባለቅ ።
2. ድብልቁን ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
3. ቅቤና ውኃ አደባልቆ መጨመር ።
4. ቀሪውን ዳቦ እላዩ ላይ መነስነስ ።
5. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ከሠላሳ እስከ አርባ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።
6. ትኩሱን ወይም ቀዝቅዞ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።



## 306. ሊቨር ሎፍ—ከጉበት የተዘጋጀ ።

$\frac{1}{2}$ ኪሎ ጉበት
2 ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
2 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
$1\frac{1}{2}$ ኩባያ የፈላ ውኃ
2 የተቁረጠ የእሳማ ሥጋ ፥ ጨው ያለው
1 ራስ ሽንኩርት
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ፐርሰሜሎ ፥ የተከተፈ
2 እንቁላል ፥ በመጠኑ የተመታ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
$1\frac{1}{2}$ ኩባያ ውኃ
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

### አሠራር

1. ጉበቱን እጥቦ የሞቀ ውኃ ውስጥ ለአሥር ደቂቃ ማስቀመጥ ።
2. ጉበት ፥ የእሳማ ሥጋ ፥ ሽንኩርት ፥ ፐርሰሜሎ ፥ የተፈጨ ዳቦ እንቁላል ፥ ጨውና ፥ ቁንዶ በርበሬ አደባልቆ መፍጨት ።
3. በተራ ቁጥር 2 የተዘጋጀውን ድብልቅ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ገል ብጦ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአንድ ሰዓት ማብሰል ።
4. የተጋገረውን ሎፍ ማውጣት ።
5. ዱቄቱን ከሎፉ በወጣው መረቅ በጥብጦ እሳት ላይ መጣድ ።
6. ዱቄቱ በሚንተከተከበት ጊዜ ስለሚወፍር ውኃ ጨምሮ እስኪ በስል ድረስ እሳቱ ላይ ማቆየት ።
7. ከበሰለ በኋላ ሎፉ ላይ ጨምሮ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 307. ስካሎፕ ድ ችክን ።

3 ኩባያ የዶሮ ሥጋ ፥ ተቀቅሎ የተከተፈ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ቅቤ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
4 ኩባያ የዶሮ መረቅ ወይም ወተት

### አሠራር

1. የአሳማ ሥጋውን እድቅቆ መክተፍ ።
2. የተከተፈውን የአሳማ ሥጋ ያለ ዘይት ወይም ቅቤ መጥበስ ።
3. ሽንኩርት ፥ ጨው ፥ ቁንዶ በርበሬ ፥ ሩዝ ፥ ዱቄት ፥ ቤኪንግ ፓውደርና ቲማቲሙን ከተጠበሰው ሥጋ ጋር ማደባለቅ ።
4. ከአሳማው ሥጋ የወጣውን ቅባት በመጥበሻ ላይ ማፍላት ።
5. በተራ ቁጥር 3 የተዘጋጀውን የሩዝና የአሳማ ሥጋ ድብልቅ በማንኪያ እየቆነጠሩ የፈላው ቅባት ውስጥ ጨምሮ መጥበስ ።

## 311. የሩዝ ፥ ጥብስ ።

1 ኩባያ ሩዝ የተቀቀለ
የተፈጨ ዳቦ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ወተት
1 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
2 እንቁላል
2 የሾርባ ማንኪያ ውኃ
የሎሚ ልጣጭ ፥ የደቀቀ

### አሠራር

1. ሩዝ ፥ ወተት ፥ ስኳር ፥ ጨው ፥ የሎሚ ልጣጭና አንዱን እንቁላል በጐድጓዳ ሣህን ውስጥ አደባልቆ ማቀዝቀዝ ።
2. በተፈለገው ዓይነት ቅርጽ በእጅ ማድቦልቦል ።
3. የቀረውን አንድ እንቁላል ከውኃው ጋር ማደባለቅ ።
4. በተራ ቁጥር 2 የተዘጋጀውን ድብልቅ እንቁላሉ ውስጥ ነክሮ የተፈጨውን ዳቦ መነስነስ ።
5. በመጥበሻው ላይ ዘይት ማፍላት ።
6. በተራ ቁጥር 4 የተዘጋጀውን የሩዝ ድቡልቡል በፈላው ዘይት ውስጥ ጨምሮ እያገላበጡ መጥበስ ።

## 312. የሩዝ ወፍል ።

1 ኩባያ ሩዝ ፥ የተቀቀለ
1 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት



3 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
2 እንቁላል
1 ኩባያ ወተት
4 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፥ የቀለጠ

### አሠራር

1. ዱቄት ፥ ቤኪንግ ፓውደርና ጨው አደባልቆ መንፋት ።
2. የእንቁላሉን አስኳልና ወተቱን በተራ ቁጥር 1 ከተዘጋጀው ድብልቅ ጋር መምታት ።
3. ቅቤውንና ሩዙን ጨምሮ ማዋሐድ ።
4. የእንቁላሉን ዞፍ በወፍራሙ መምታትና በተራ ቁጥር 3 ከተዘጋጀው ድብልቅ ጋር በዝግታ ማዋሐድ ።
5. ወፍል መጋገሪያ ዕቃ ላይ ገልብጦ ምድጃ ውስጥ ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 313. የሩዝ መፊን ።

$1\frac{1}{2}$ ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
3 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
1 ኩባያ ሩዝ
1 ኩባያ ወተት
2 እንቁላል ፥ የተመታ
5 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፥ የቀለጠ
2 የሻይ ማንኪያ ስኳር
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው

### አሠራር

1. ሩዝ ፥ ወተት ፥ እንቁላልና ቅቤ አደባልቆ መምታት ።
2. ዱቄት ፥ ስኳር ፥ ጨውና ቤኪንግ ፓውደር በደንብ እስኪያያዝ ድረስ ማደባለቅ ።
3. የመፊን መጋገሪያውን ቅቤ ወይም ዘይት ቀብቶ በተራ ቁጥር 1 የተዘጋጀውን የሩዝ ድብልቅ ግማሹን መጨመር ። እላዩ ላይ በተራ ቁጥር 2 የተዘጋጀውን መጨመር ።
4. ሙቀቱ 400 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሃምሳ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

ሁለት ሰው ይመግባል ።

## 314. የአጃ መፊን ፡፡

$\frac{2}{3}$ ኩባያ አጃ ፣ የተቀቀለ
2 ኩባያ የፋርኖ ዱቄት ፣ የተነፋ
3 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
2 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 እንቁላል ፣ በደንብ የተመታ
1 ኩባያ ወተት
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ

### አሠራር

1. ዱቄት፣ ቤኪንግ ፓውደር ፣ ስኳርና ጨው ማደባለቅ ፡፡
2. እንቁላል ፣ አጃ ፣ ወተትና ቅቤ የተደባለቀው ዱቄት ላይ ጨምሮ ማዋሐድ ፡፡
3. የመፊን መጋገሪያውን ቅቤ ወይም ዘይት ቀብቶ በተራ ቁጥር 2 የተዘጋጀውን የአጃ ድብልቅ ግማሽ ድረስ መጨመር ፡፡
4. ሙቀቱ 425 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሃያ አምስት ደቂቃ ማብሰል ፡፡

## 315. ቺዝ ፎንዱ ፡፡

1 ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
3 እንቁላል ፣ አስኳሉና ዞፉ የተለየ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ፎርማጆ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 ኩባያ ወተት
ትንሽ በርበሬ

### አሠራር

1. ወተቱን ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ የፈላ ውኃ ላይ በእንፋሎት ሞቅ ማድረግ ፡፡
2. የተፈጨ ዳቦ ፣ ፎርማጆ ፣ ቅቤ ፣ ጨውና በርበሬ ማደባለቅ ፡፡
3. የእንቁላሉን አስኳል ከዞፉ ለይቶ አስኳሉን ጨምሮ ማደባለቅ ፡፡
4. የእንቁላሉን ዞፍ እስኪወፍር መምታት ፡፡



5. የእንቁላሉን ዞፍ ከዳቦና ከእንቁላል አስኳል ድብልቁ ጋር ማዋሐድ ፡፡
6. የመጋገሪያ ዕቃውን ቅቤ ወይም ዘይት መቀባት ፡፡
7. በተራ ቁጥር3 የተዘጋጀውን ድብልቅ መጋገሪያ ዕቃ ላይ መገልበጥ፡፡
8. የፈላ ውኃ ዕቃ ላይ አድርጎ የተሞላውን መጋገሪያ እላዩ ላይ ማስቀመጥ ፡፡
9. ሙቀቱ 325 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ከሠላሳ እስከ አርባ አምስት ደቂቃ በእንፋሎት ማብሰል ፡፡

ስድስት ሰው ይመግባል ፡፡

## 316. ተፈጭቶ የተጋገረ ድንች ፡፡

6 ድንች ፣ ተቀቅሎ የተፈጨ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ፎርማጆ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
2 እንቁላል
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ሚጥሚጣ

### አሠራር

1. ቅቤ ፣ ጨው ፣ ሚጥሚጣ ፣ እንቁላልና የተፈጨውን ድንች ሣህን ውስጥ በደንብ ማደባለቅ ፡፡
2. የመጋገሪያ ዕቃውን ዘይት ወይም ቅቤ መቀባት ፡፡
3. በተራ ቁጥር 1 የተዘጋጀውን ድብልቅ የተቀባው መጋገሪያ ዕቃ ላይ መገልበጥ ፡፡
4. ፎርማጆና የተፈጨ ዳቦውን እላዩ ላይ መነስነስ ፡፡
5. ሙቀቱ 400 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአሥር ደቂቃ ማብሰል፡፡

ስድስት ሰው ይመግባል ፡፡

## 317. እንቁላልና ቆስጣ—እስፒናች ፡፡

2 ኩባያ ቆስጣ—እስፒናች—ተቀቅሎ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው

አሠራር

1. ቲማቲሙን አጥቦ ከጫፉ በኩል ቈርጦ ፍሬውን ቦርቡሮ ማውጣት ።
2. ከቲማቲሙ ውስጥ የወጣውን እድቅቆ መክተፍ ።
3. ሽንኩርቱ በቅቤ ከተቁላላ በኋላ ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬ ፣ የተፈጨ ዳቦ ፣ እንቍላል ፣ ቃሪያ ፣ ሰዲኖ ፣ ጥቅል ጎመንና የተከተፈውን ቲማቲም ጨምሮ ማዋሐድ ።
4. በተራ ቍጥር 3 የተዘጋጀውን ድብልቅ የተቦረቦረው ቲማቲም ውስጥ መሙላት ።
5. የተሞላውን ቲማቲም በቅባት በታሰሰ መጋገሪያ ዕቃ (ካሴሮል) ላይ ማድረግ ።
6. ሙቀቱ 375 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሃያ ደቂቃ ማብሰል ።
7. ከእንቍላል ሶስ ጋር ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

328. ዝኩኒ በቲማቲም ።

1 ኪሎ ዝኩኒ
2 ኩባያ ተከትፎ በመጠኑ የበሰለ ቲማቲም
3 የሾርባ ማንኪያ የተከተፈ ቀይ ሽንኩርት
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
¾ ኩባያ ፎርማጆ
ትንሽ በርበሬ

አሠራር

1. ዝኩኒውን አጥቦ በስሱና በክቡ መክተፍ ።
2. ሽንኩርቱን ከቅቤው ጋር ማቁላላት ።
3. ዝኩኒውን ጨምሮ ለአምስት ደቂቃ ማብሰል ።
4. ቲማቲም ፣ ጨው ፣ በርበሬ ጨምሮ በሌላ ድስት ለአምስት ደቂቃ አብስሎ ከዝኩኒው ጋር ማደባለቅ ።
5. በቅባት በታሰሰ መጋገሪያ ላይ ገልብጦ እላዩ ላይ ፎርማጆውን መነስነስ ።
6. ሙቀቱ 375 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሃያ ደቂቃ ማብሰል።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመግባል ።



329. እስፒናች—ቆስጣ—የተሞላ ቲማቲም ።

6 ቲማቲም
2 ኩባያ ቆስጣ—እስፒናች—የተቀቀለ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
½ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
የእንቍላል ሶስ

አሠራር

1. ቲማቲሙን አጥቦ ከጫፉ በኩል ቈርጦ ቦርቡሮ ማውጣት ።
2. ቆስጣ ፣ ቅቤ ፣ ጨው ፣ ሽንኩርትና ተቦርቡሮ የወጣውን ቲማቲም አደባልቆ የተቦረቦረው ቲማቲም ውስጥ መሙላት ።
3. የተሞላውን ቲማቲም በቅባት በታሰሰ መጋገሪያ ዕቃ (ካሴሮል) ላይ ማድረግ ።
4. ሙቀቱ 375 ድግሪ ፋራንሃይት ምድጃ ለሃያ ደቂቃ ማብሰል ።
5. ከበሰለ በኋላ ከእንቍላል ሶስ ጋር ማቅረብ

ስድስት ሰው ይመግባል ።

330. በምድጃ የበሰለ ቲማቲም በተፈጨ ዳቦ ።

4 ኩባያ ቲማቲም ፣ ተቈርጦ በመጠኑ የተቀቀለ
1 ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
1 የሾርባ ማንኪያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
ፓርሰሜሎ

አሠራር

1. ሽንኩርትና ቲማቲሙን ማደባለቅ ።
2. በቅባት በታሰሰ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ግማሹን የተፈጨ ዳቦ ማድረግ ።
3. በተፈጨው ዳቦ ላይ ቲማቲሙን መጨመር ።
4. እላዩ ላይ ቀሪውን የተፈጨ ዳቦ ጨምሮ ሙቀቱ 400 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሃያ ደቂቃ ወይም እጋም እስኪመስል ማብሰል።
5. በፓርሰሜሎ አጊጦ ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 331. የተጠበሰ ቲማቲም በፉርኖ ዱቄት ።

6 ቲማቲም ፣ በስሱ የተቈረጠ
1 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
2 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 እንቍላል ፣ የተመታ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ወተት
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
ዘይት ፣ ለመጥበሻ

### አሠራር

1. ዱቄት ፣ ቤኪንግ ፓውደር ፣ ጨው አደባልቆ መንፋት ።
2. የተነፋውን ዱቄት ከእንቍላል ጋር ማደባለቅ ።
3. በዝግታ እያማሰሉ ወተቱን መጨመር ።
4. በመጨረሻም ቅቤውን ጨምሮ በደንብ ማዋሐድ ።
5. በስሱ የተቈረጠውን ቲማቲም ከፍ ብሎ በተዘጋጀው የዱቄት፣የእንቍላልና የወተት ድብልቅ ውስጥ ነክሮ መጥበሻ ላይ በፈላ ዘይት ውስጥ እያገላበጡ እጋም እስኪመስል ማብሰል ።
6. ዘይቱን እንዲመጥ ጥብሱን ቲማቲም ወረቀቱ ላይ ማስቀመጥ ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመገባል ።

## 332. የቲማቲም ጥብስ ።

6—8 በጣም ያልበሰለ ቲማቲም
1 እንቍላል
1 የሾርባ ማንኪያ ቀዝቃዛ ውኃ
3 ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
1 የሻይ ማንኪያ ፐርሰሜሎ
ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬ
ማርገሪን

### አሠራር

1. ቲማቲሙን አጥቦ ቆሻሻውን አስወግዶ በክብ በስስ በስሱ መምተር።
2. እንቍላል መትቶ ከውኃው ጋር ማደባለቅ ።
3. የተፈጨ ዳቦ ፣ ጨውና ቁንዶ በርበሬ መጨመር ።



4. ቲማቲሙን እንቍላል ውስጥ እየነከሩ የተፈጨ ዳቦ እላዩ ላይ መነስነስ ።
5. በማርገሪን ጠብሶ ፐርሰሜሎ እላዩ ላይ ነስንሶ ማቅረብ ።

## 333. ደበርጃን በፔፐሮኒ ።

$\frac{1}{2}$ ኪሎ ደበርጃን
$\frac{1}{4}$ ኪሎ ፔፐሮኒ
1 በክብ ቅርጽ የተመተረ ቀይ ሽንኩርት
3 ፍሬ ነጭ ሽንኩርት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ የተከተፈ ፐርሰሜሎ
$\frac{1}{4}$ ኪሎ ቲማቲም
$\frac{1}{4}$ ኩባያ የሚነሰነስ ፐርሰሜሎ
ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬ
ዘይት ፣ ለመጥበሻ

### አሠራር

1. ደበርጃን በስሱ መትሮ ጨው በገባበት ውኃ ውስጥ ለግማሽ ሰዓት መዘፍዘፍ ።
2. በንጹሕ ጨርቅ አድርቆ በፈላ ዘይት ውስጥ መጥበስ ።
3. ፔፐሮኒውን በቁመት መትሮ ውኃውን አጥልሎ በጨርቅ ላይ ከደረቀ በኋላ በዘይት መጥበስ ።
4. ለመጥበሻ ከዋለው ግማሽ ኩባያ ዘይት ድስት ውስጥ ጨምሮ ነጭና ቀይ ሽንኩርት እንዲሁም ፐርሰሜሎ ቀላቅሎ መጥበስ ።
5. በሌላ ድስት ውስጥ ከደበርጃኑ ትንሽ ፣ ከፔፐሮኒው ትንሽ ከሥር እንጥፎ እላዩ ላይ የተጠበሰውን ሽንኩርት መጨመር ።አስፈላጊ ከሆነም በክቡ የተመተረ ወይም የተፈጨ ቲማቲም ማድረግ ። የቀረውን ደበርጃንና ፔፐሮኒ ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬና ፐርሰሜሎ እላዩ ላይ መነስነስ ። በክብ የተመተረ ቲማቲም እላዩ ላይ በመደርደር ትንሽ ዘይት እፍስሶ ምድጃ ውስጥ ወይም በፎርኔሎ ማብሰል ።

አራት ሰው ይመገባል ።

4 የሾርባ ማንኪያ የወይራ ዘይት—አሊቭ አይል
½ ኩባያ የተከተፈ ቀይ ሽንኩርት
1 ኩባያ ድንች ፣ በስሱ የተከተፈ
6 የሻይ ማንኪያ ቀዝቃዛ ውኃ
ጨው

እሠራር

1. ዘይቱን አሙቆ ሽንኩርት ጨምሮ እስኪበስል ማቁላላት ።
2. የተከተፈውን ድንችና ፔፐሮኒ መጨመር ።
3. አስፈላጊ ከሆነ ትንሽ ውኃ መከለስ ።
4. እንቁላሉን መትቶ መጨመር ። አስፈላጊ ከሆነ ግማሽ ኩባያ የተከተፈ የአሳማ ሥጋ መጨመር ።
5. ቀስ አድርጎ እያማሰሉ ከበሰለ በኋላ በሣህን ላይ አውጥቶ ማቅረብ ።

አራት ሰው ይመግባል ።

## 338. የእንቁላል ላዛኛ ።

12 እንቁላል
¼ ኪሎ ካሮት
1 ኪሎ ድንች
½ ዝኩኒ
2 የሾርባ ማንኪያ ፐርሰሜሎ
1 ራስ ነጭ ሽንኩርት ፣ ትንሽ
ጨው
ቁንዶ በርበሬ

እሠራር

1. ድንቹን ልጦ በከቡ መከተፍ ።
2. ዝኩኒው ሳይላጥ በስሱ መከተፍ ።
3. ካሮቱን ልጦ በከቡ መከተፍ ።
4. ከቁጥር 1 እስከ 3 የተዘጋጁትን አትክልቶች በሞቀ ዘይት ለየ ብቻቸው ጠብሶ አንድ ላይ ማደባለቅ ።
5. የተደባለቀውን ጎመን አንድ ሰፊ ድስት ውስጥ ጨምሮ አላዩ ላይ በደቃቁ የተፈጨውን ፐርሰሜሎና ነጭ ሽንኩርት መነስነስ ።
6. እንቁላሉን ትንሽ መትቶ ጨውና ቁንዶ በርበሬ ጨምሮ በሙሉ አን ዲያለብሰው አድርጎ አላዩ አፍስሶ በምድጃ ወይም በፎርኔሎ ማብሰል።



## 339. የአበባ ጎመን ጥብስ ።

½ ኪሎ አበባ ጎመን
4 ፍሬ ነጭ ሽንኩርት
1 የሻይ ማንኪያ ፐርሰሜሎ
4 እንቁላል ፣ አስኳሉ ብቻ
2 የሾርባ ማንኪያ ክሬም

እሠራር

1. ነጭ ሽንኩርትና ፐርሰሜሎ አንድ ላይ መፍጨት ።
2. እንቁላልና ክሬም በጎድጓዳ ሣህን መምታት ።
3. በቁጥር 1 የተዘጋጀውን ቅመም ከእንቁላሉና ከክሬሙ ድብልቅ ጋር መምታት ።
4. አበባ ጎመኑ ለብቻው ግማሽ ያህል ከበሰለ በኋላ ከውኃው ውስጥ አውጥቶ የተመታው እንቁላል ውስጥ እየነከሩ በዘይት መጥበስ ።

## 340. የአትክልት ሱፍሌ ።

2 ኩባያ በቀርቀሮ የታሸገ በቆሎ ፣ ወይም ተፈልፍሎ የተቀቀለ እሸት በቆሎ
½ ኩባያ ቲማቲም ፣ ተልጦ የተከተፈ
2 እንቁላል ፣ አስኳሉና ዞፉ የተለየ
1 ትንሽ ቀይ ሽንኩርት
1 የሾርባ ማንኪያ ዘይት ወይም ቅቤ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
¼ የሻይ ማንኪያ ሚጥሚጣ
1 ኩባያ ፎርማጆ

እሠራር

1. ሽንኩርቱን ልጦና አጥቦ በደቃቁ መከተፍ ።
2. ሽንኩርቱን በዘይት ወይም በቅቤ እስኪበስል ማቁላላት ።
3. የእንቁላሉን አስኳል ከዞፉ መለየትና አስኳሉን በመጠኑ መምታት።
4. በቆሎ ፣ ጨው ፣ ፎርማጆ ፣ ቲማቲምና የእንቁላል አስኳሉን በተራ ቁጥር 3 ከተዘጋጁት መቀላቀሎች ጋር ማደባለቅ ።

5. የእንቍላሉን ዞፍ በጣም እስኪ.ወፍር መምታትና ከተዋሐዱት መቀላቅሎች ጋር በዝግታ ማደባለቅ ።
6. የመጋገሪያውን ዕቃ ዘይት ወይም ቅቤ መቀባት ።
7. የተዘጋጀውን ሱፍሌ መጋገሪያ ዕቃው ላይ አስተካክሎ መገልበጥ ።
8. ሙቀቱ 250 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ከሠላሳ እስከ አርባ ደቂቃ ማብሰል ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 341. የአትክልት ካሴሮል ።

2 ትልቅ የዐላጣ ሽንኩርት
2 ትልቅ ቲማቲም
2 ኩባያ የተከተፈ ድንች
1 ኩባያ በደቃቁ የተከተፈ ሰለሪ—የሰዴኖ ቅጠል
1 ኩባያ የተከተፈ ካሮት
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
½ የሻይ ማንኪያ በርበሬ
1 የሻይ ማንኪያ ሚጥሚጣ
4 የሾርባ ማንኪያ ዘይት ወይም ቅቤ

አሠራር

1. ሽንኩርት ልጦና አጥቦ በስሱና በክቡ መክተፍ ።
2. ቲማቲሙን አጥቦ በስሱና በክቡ መክተፍ ።
3. የመጋገሪያውን ዕቃ ካሴሮል ዘይት ወይም ቅቤ መቀባት ።
4. ድንች ፡ ሽንኩርት ፡ ቲማቲም ፡ ሰለሪና ካሮት አንዱን በአንዱ ላይ ጨው እየነሰነሱ በመደራረብ ቅባት የተቀባው ካሴሮል ላይ ማድረግ ።
5. የተዘጋጀው ካሴሮል ላይ በርበሬና ሚጥሚጣ መነስነስ ።
6. ዘይት ወይም ቅቤ መጨመር ።
7. ሙቀቱ 375 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአንድ ሰዓት ወይም እስከሚበስል መጋገር ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመግባል ።



## 342. የተሞላ ዝኩኒ ።

1 ትልቅ ዝኩኒ
¼ ኪሎ የተፈጨ ሥጋ
½ ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
1 የሾርባ ማንኪያ የተከተፈ ሽንኩርት
2 የሾርባ ማንኪያ ቲማቲም
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
በጣም ትንሽ በርበሬ

አሠራር

1. ዝኩኒውን በቁመቱ መሰንጠቅ ።
2. ከተሰነጠቀው ዝኩኒ ውስጥ ፍሬውን ማውጣት ።
3. የተፈጨውን ሥጋ መቀቀልና አንድ ኩባያ ለክቶ ማንጣት ።
4. የተፈጨውን ዳቦ ፡ ሥጋ ፡ ሽንኩርት ፡ ቲማቲም ፡ ጨውና በርበሬ አንድ ላይ ማደባለቅ ።
5. ድብልቁን ዝኩኒው ውስጥ መሙላት ።
6. የተሞላውን ዝኩኒ አጋጥሞ በክር ማሰር ወይም በቀጫጭን ስንጥር ማያያዝ ።
7. መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ሙቀቱ 350 ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሠላሳ ደቂቃ ማብሰል ።

ሌላ አማራጭ ፤

የተሞላውን ዝኩኒ ከቲማቲም ሱጎ ጋር ማብሰል ይቻላል ።

## 343. በምድጃ የበሰለ አትክልት ።

8 ትንንሽ ካሮት
8 ትንንሽ ድንች
8 ትንንሽ ሽንኩርት
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
ነጭ ሶስ
ትንሽ በርበሬ
ትንሽ ጨው

## እሠራር

1. ቲማቲሙን ልጦ ፍሬውን ማውጣት ።
2. ቲማቲሙን ከትፎ ከቅቤ ጋር ማቁላላት ።
3. ጨውና በርበሬ ከቲማቲሙ ጋር ማዋሐድ ።
4. ዝኩኒውን አጥቦ በደቃቁ መክተፍ ።
5. የተከፈተውን ዝኩኒ ከተቁላላው ቲማቲም ጋር አዋሕዶ ማብሰል ።
6. ፐርስሜሎውን ጨምሮ ማውጣት ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመገባል ።

## 347. ዝኩኒ በቲማቲም ።

1 ኪሎ ዝኩኒ
3 የሾርባ ማንኪያ የተከተፈ ቀይ ሽንኩርት
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
2 ኩባያ ተከትፎ በመጠኑ የበሰለ ቲማቲም
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{3}{4}$ ኩባያ ፎርማጅ
ትንሽ በርበሬ

## አሠራር

1. ዝኩኒውን አጥቦ በስሱና በክቡ መክተፍ ።
2. ሽንኩርቱን ከቅቤው ጋር ማቁላላት ።
3. ዝኩኒውን ጨምሮ ለአምስት ደቂቃ ማብሰል ።
4. ቲማቲም ፣ ጨውና በርበሬ በሌላ ድስት ጨምሮ ለአምስት ደቂቃ ማብሰል ።
5. ቅባት በተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ በተራ ቁጥር 3 ና 4 የተዘጋጀውን ገልብጦ እላዩ ላይ ፎርማጅ መነስነስ ።
6. ሙቀቱ 375 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሃያ ደቂቃ ማብሰል።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመገባል ።



## 348. ሚኒኮታ በቲማቲም ።

$\frac{1}{2}$ ኪሎ ስፒናች
$\frac{1}{4}$ ኪሎ የተፈጨ ሥጋ
2 ቀይ ሽንኩርት ፣ በደቃቁ የተከተፈ
1 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
$\frac{3}{4}$ ኩባያ ውኃ
5 እንቁላል
50 ግራም ፎርማጅ ፣ የተፈጨ
1 ቆርቆሮ የቲማቲም ድልህ
3—4 ቲማቲም
2 የሻይ ማንኪያ ዘይት
ዘይት ፣ ለመጥበሻ
ጨው

## እሠራር

1. እንቁላሉን መትቶ ጨውና ዘይት መጨመር ።
2. ፉርኖ ዱቄቱን ጨምሮ ቀጠን እስኪል መምታት ።
3. መጥበሻው ላይ ዘይት ጨምሮ ማሞቅ ። ዘይቱ ከሞቀ በኋላ ሊጡን እላዩ ላይ አፍስሶ በጣም ሳይበስል ማውጣት ።
4. እስፒናቹን በውኃ አብስሎ መክተፍ ።
5. በመጥበሻው ላይ ዘይት ጨምሮ ሽንኩርቱን ማቁላላት ። ከዚያም ቲማቲም ፣ ሥጋ እስፒናች ጨምሮ አንድ ላይ ማቁላላት ።
6. የቲማቲሙን ድልህ ለብቻው በዘይት ማቁላላት ።
7. በቁጥር3 የተዘጋጀውን ጥብስ ከስር አንጥፎ እላዩ ላይ በቁጥር5 የተዘጋጀውን ቁሌት መጨመር ። ቁሌቱን በጥብሱ ከድኖ የቲማቲም ድልሁን እላዩ ላይ ማፍሰስ ። ከተፈለገ በምድጃ ማብሰልና ፎርማጅ ነስንሶ ማቅረብ ።

## 349. ጣዕሚያ ።

$1\frac{1}{2}$ ኩባያ የተከካ ባቄላ ወይም ምስር
1 ትልቅ ቀይ ሽንኩርት ፣ በደቃቁ የተከተፈ
4 ፍሬ ነጭ ሽንኩርት ፣ የተፈጨ
1 የሻይ ማንኪያ ነጭ አዝሙድ ፣ ታምሶ የተወቀጠ

አሠራር

1. ሽንኩርት በቅቤ ማቁላላት ።
2. ድንች ፣ ቃሪያ ፣ የአሳማ ሥጋ ፣ ጨውና ሚጥሚጣ ከተቁላላው ሽንኩርት ጋር አደባልቆ ማብሰል ።
3. ትኩሱን ማቅረብ ።

እራት ሰው ይመግባል ።

## 364. የቆስጣና የአሳማ ሥጋ ሰላጣ ።

$1\frac{1}{2}$ ኩባያ ቆስጣ ፣ የተቀቀለ
4 ኪሎ የተከተፈ የአሳማ ሥጋ
የሎሚ ጭማቂ
ሰላጣ ቅጠል
ማዮኔዝ

አሠራር

1. ሰላጣውን አጥቦ ሣህን ላይ ማዘጋጀት ።
2. የሎሚ ጭማቂውን መጨመር ።
3. የአሳማ ሥጋውን ሰላጣው ላይ መደርደር ።
4. ቆስጣውን ከአሳማ ሥጋው ዙሪያ ማስቀመጥ ።
5. ከሰላጣ ቅመም ወይም ከማዮኔዝ ጋር ማቅረብ ።

እራት ሰው ይመግባል ።

## 365. ሥጋና ሩዝ በፎርማጆ ።

2 ኩባያ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
2 ኩባያ ሩዝ ፣ የተቀቀለ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ፎርማጆ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
ወተት ወይም መረቅ
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ



አሠራር

1. ሥጋውን ቀቅሎ መክተፍ ።
2. ትንሽ ወተት ወይም መረቅ ከሥጋው ጋር ማደባለቅ ።
3. በቅባት የታሰሰ መጋገሪያ ላይ ሩዙን ማድረግ ።
4. እሩዙ ላይ ቅቤና ፎርማጆ መጨመር ።
5. ቁንዶ በርበሬና ጨው ነስንሶ የተዘጋጀውን ሥጋ እላዩ ላይ ማድረግ።
6. ቀሪውን ቅቤና ፎርማጆ ጨምሮ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ከአሥራ አምስት እስከ ሃያ ደቂቃ ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 366. የሥጋና የአትክልት ፓይ ።

2 ኩባያ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
$1\frac{1}{2}$ የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
1 ኩባያ አተር ፣ የተቀቀለ
1 ኩባያ ካሮት ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
1 ኩባያ እንጉዳይ
2 ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
$1\frac{1}{4}$ ኩባያ ወተት ወይም መረቅ
$\frac{1}{2}$ ረሲፒ ፔስትሪ
ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ሽንኩርቱን በቅቤ አቁላልቶ ሥጋውን ጨምሮ ማብሰል ።
2. የተጣደውን ሽንኩርትና ሥጋ አውጥቶ ከዱቄት ፣ ከወተት ወይም ከመረቅ ጋር በደንብ ማደባለቅ ።
3. አተር ፣ ካሮትና እንጉዳዩን ጨምሮ ማደባለቅ ።
4. የመጋገሪያ ዕቃውን ዘይት ወይም ቅቤ መቀባት ።
5. በተራ ቁጥር 3 እና 4 የተዘጋጀውን ሥጋና አትክልት መጋገሪያ ዕቃው ላይ አድርጎ ጨውና ቁንዶ በርበሬ እላዩ ላይ መነስነስ ።
6. ፔስትሪውን እላዩ ላይ ሸፍኖ ጠርዙን በደንብ መግጠም ።
7. ሙቀቱ 425 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለሠላሳ ደቂቃ ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 367. የተሞላ ኤግፕላንት—ደበርጃን ።

1 ትልቅ ኤግፕላንት
1 እንቊላል ፣ በስሎ የተከተፈ
1 ቃሪያ ፣ የተከተፈ
2 ቲማቲም ፣ አራት ቦታ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 ትልቅ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 ኩባያ አሳማ ሥጋ
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ
የተፈጨ ዳቦ
ጨው
ውኃ ፣ ለመቀቀያ

### አሠራር

1. ኤግፕላንቱን ማጠብ ።
2. የኤግፕላንቱን ውስጣዊ ክፍል ቦርቡሮ ማውጣት ።
3. ውስጣዊ ክፍሉ የወጣለትን ኤግፕላንት ጨው የገባበት ውኃ ውስጥ መዘፍዘፍ ።
4. ከኤግፕላንቱ ውስጥ ተቦርቡሮ የወጣውን ክፍል ከሽንኩርት ፣ ከቃሪያና ከቲማቲም ጋር እያባልቆ ጨው በገባበት ውኃ መቀቀል ።
5. ውኃውን አጥልሎ ቃሪያውን ፈጭቶ ከቅቤ ፣ ከጨው ፣ ከቁንዶ በርበሬና ከአሳማ ሥጋ ጋር ማደባለቅ ።
6. ውኃ ውስጥ የተዘፈዘፈውን የኤግፕላንት ቀፎ አውጥቶ በተራ ቊጥር 6 በተዘጋጀው የአሳማ ሥጋ ድብልቅ መሙላት ።
7. የተሞላው ኤግፕላንት ላይ የተፈጨ ዳቦ ነስንሶ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
8. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሃያ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

ከአራት እስከ ስድስት ሰው ይመገባል ።



## 368. የተሞላ የፈረንጅ ቃሪያ ።

6 የፈረንጅ ቃሪያ
$1\frac{1}{4}$ ኩባያ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
$1\frac{1}{4}$ ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
$\frac{1}{2}$ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 ኩባያ ውኃ ወይም መረቅ
ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬ

### አሠራር

1. ቃሪያውን አጥቦ ፍሬውን ቦርቡሮ ማውጣት ።
2. ቃሪያውን በመጠኑ በውኃ መቀቀል ።
3. ሥጋ ፣ የተፈጨ ዳቦ ፣ ጨው ፣ ቁንድ በርበሬ ፣ ቅቤና ሽንኩርት እያባልቆ የተቦረቦረውን ቃሪያ መሙላት ።
4. የተሞላውን ቃሪያ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ውኃ ወይም መረቅ መጨመር ።
5. ሙቀቱ 375 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሠላሳ ደቂቃ ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመገባል ።

## 369. የሥጋ ሰላጣ ።

1 ኩባያ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
2 እንቊላል ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
2 ቲማቲም ፣ አራት ቦታ የተቈረጠ
ሰላጣ ቅጠል ፣ የሰላጣ ማጣፈጫ ወይም ማዮኔዝ

### አሠራር

1. ሥጋና እንቊላሉን ማደባለቅ ።
2. ሰላጣ ቅጠሉን አጥቦ ሣህን ላይ ማዘጋጀት ።
3. የተደባለቀውን ሥጋና እንቊላል ሰላጣ ቅጠሉ ላይ ማድረግ ።
4. ከሰላጣ ማጣፈጫ ወይም ከማዮኔዝ ጋር ማቅረብ ።
5. በሥጋ ፈንታ የአሳማ ሥጋ ወይም ምላስ መጠቀም ይቻላል ።

ስድስት ሰው ይመገባል ።

## 370. የተፈጨ የዶሮ ሥጋ ሾርባ ።

2 ኩባያ የዶሮ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተፈጨ
1 ኩባያ ነጭ ሶስ
1 እንቁላል አስኳል
2 የሾርባ ማንኪያ ወተት
1 የሾርባ ማንኪያ ፐርሰሜሎ

### አሠራር

1. የዶሮ ሥጋና ፐርሰሜሎውን ሶሱ ውስጥ ጨምሮ ማፍላት ።
2. እንቁላሉንና ወተቱን የፈላው የዶሮ ድብልቅ ውስጥ ጨምሮ ለሁለት ደቂቃ ማብሰል ።
3. ትኩሱን ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 371· ስካሎፕ ዱ ቺክን ።

2 ኩባያ የዶሮ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
2 ኩባያ ድንች ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
2 ኩባያ የዶሮ መረቅ
2 የሾርባ ማንኪያ የፋርኖ ዱቄት
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
የተፈጨ ዳቦ
ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬ

### አሠራር

1. መረቁን በብረት ድስት ማፍላት ።
2. ዱቄትና ቅቤውን ጨምሮ እስኪወፍር ማንተክተክ ።
3. ሽንኩርት ፣ ጨውና የዶሮ ሥጋውን በተራ ቁጥር 2 በተዘጋጀው ሶስ ውስጥ ጨምሮ ማብሰል ።
4. በተራ ቁጥር 3 የተዘጋጀውን በተጠበሰው ሁለት ዳቦ መካከል አዘጋጅቶ ጨምሮ ማቅረብ ።



## 372. ትኩስ የዶሮ ሳንድዊች ።

በስሱ ተቆረጠ የተጠበሰ ዳቦ

1 ኩባያ የዶሮ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተከፈተ
1 የሾርባ ማንኪያ የፋርኖ ዱቄት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ የዶሮ መረቅ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ወተት
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 የሻይ ማንኪያ ሽንኩርት በደቃቁ ፣ የተከተፈ
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው

### አሠራር

1. መረቁን በብረት ድስት ማፍላት ።
2. ወተት ፣ ዱቄትና ቅቤውን ጨምሮ ማንተክተክ ።
3. ሽንኩርት ፣ ጨውና የዶሮ ሥጋውን በተራ ቁጥር 2 በተዘጋጀው ሶስ ውስጥ ጨምሮ ማብሰል ።
4. በተራ ቁጥር 3 የተዘጋጀውን በተጠበሰው በየሁለት ሁለቱ ዳቦ መካከል አዘጋጅቶ ማቅረብ ።

አሠራር

1. የእሳማ ሥጋውን ያለ ቅባት መጥበስ ።
2. ፋሶሊያ ፣ ስኳር ፣ ጨው ፣ ኮምጣጤ ፣ ቁንዶ በርበሬ የእሳማ ሥጋ ጨምሮ ለስምንት ደቂቃ ወይም እስኪበስል መቀቀል ።
3. ከበሰለ በኋላ ትኩሱን ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

377. የካሮት ጥብስ ።

2 ኩባያ ካሮት ፣ ተቀቅሎ የተፈጨ
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
1 የእንቁላል አስኳል ፣የተመታ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
የተፈጨ ዳቦ
ፐርሰሜሎ
ገውዝ

አሠራር

1. ካሮት ፣ ቅቤ ፣ የእንቁላል አስኳል ፣ የተፈጨ ዳቦ ጨውና ገውዝ በጐድጓዳ ሣህን ማደባለቅ ።
2. ካሮት በሚመስል ቅርጽ አድቦልቡሎ በረዶ ቤት ውስጥ ለሁለት ሰዓት ማስቀመጥ ።
3. መጥበሻ ላይ ዘይት ጨምሮ ሲፈላ በተራ ቁጥር 2 የተዘጋጀውን ከሦስት እስከ ስምንት ደቂቃ መጥበስ ።
4. የተጠበሰውን ካሮት ወረቀት ላይ አስቀምጦ ዘይቱን እንዲመጥ ማድረግ ።
5. በፐርሰሜሎ አጊጦ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

378. የበቆሎ ኬክ ።

1 ኩባያ በቆሎ ፣ ተቀቅሎ የተፈጨ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ወተት
2 የሻይ ማንኪያ ስኳር



2 እንቁላል ፣ በደንብ የተመታ
$\frac{3}{4}$ ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
1 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው

አሠራር

1. በቆሎ ፣ ወተት ፣ ስኳርና እንቁላል በጐድጓዳ ሣህን ማደባለቅ ።
2. ዱቄት ፣ ቤኪንግ ፓውደርና ጨው አብሮ መንፋት ።
3. በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተዘጋጀውን በደንብ አደባልቆ መጋገሪያ ዕቃ ላይ መገልበጥ ።
4. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ከአሥራ አምስት እስከ ሃያ ደቂቃ ማብሰል ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

379. የእተር ጥብስ ።

2 ኩባያ እተር ፣ የተቀቀለ
1 ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
1 እንቁላል ፣ የተመታ
2 የሾርባ ማንኪያ ውኃ
የተፈጨ ዳቦ

አሠራር

1. የተቀቀለውን እተር በሹካ በመጫን ማድቀቅ ።
2. እተር ፣ ሽንኩርት ፣ ጨውና ቁንዶ በርበሬ ማደባለቅ ።
3. የእተሩን ድብልቅ በከቡ ማድቦልቦል ።
4. እንቁላሉንና ውኃውን በጐድጓዳ ሣህን መምታት ።
5. የተድቦለቦለውን እተር የተመታው እንቁላል ውስጥ ነክሮ የተፈጨ ዳቦ እላዩ ላይ መነስነስ ።
6. መጥበሻ ላይ ዘይት ጨምሮ በተራ ቁጥር 5 የተዘጋጀውን መጥበስ።
7. የእተሩን ጥብስ ወረቀት ላይ በማስቀመጥ ዘይቱን እንዲመጥ አድርጎ ማቅረብ ።

አራት ሰው ይመግባል ።

2. በመጥበሻ ላይ ዘይት ጨምሮ ማፍላት ።
3. በተራ ቁጥር 1 የተዘጋጀውን እድቦልቡሎ በፈላ ዘይት እያገላ በጡ መጥበስ ።
4. በፐርሰሜሎ አጊጦ ማቅረብ ።

አምስት ሰው ይመግባል ።

384. የአትክልት ጥብስ ።

2 ኩባያ የተደባለቀ አትክልት ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
2 ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
1 እንቁላል
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬ ፣ ነውዝ
ፐርሰሜሎ ፣ የተከተፈ

እሠራር

1. አትክልቱን ከተፈጨው ዳቦ ጋር ማደባለቅ ።
2. ጨው ፣ በርበሬ ፣ ነውዝና ፐርሰሜሎ ከአትክልትና ከተፈጨው ዳቦ ድብልቁ ጋር ማዋሐድ ።
3. ቅቤና እንቁላሉን መጨመር ፤ የመድረቅ መልክ እላዩ ላይ ካሳየ ወተት መክለስ ።
4. ተደባልቆ የተዘጋጀውን አትክልት በተፈለገው ዓይነት ቅርጽ እስተካክሎ በመጥበሻ ላይ በፈላ ዘይት መጥበስ ።
5. በፐርሰሜሎ አጊጦ ማቅረብ ።

385. የበቆሎና የድንች ጥብስ ።

1 ኩባያ ድንች ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
1 ኩባያ በቆሎ ፣ የተቀቀለ ወይም በቆርቆሮ የታሸገ
½ ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
2 እንቁላል ፣ የተመታ
3 የሻይ ማንኪያ ወተት
1 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
1 የሾርባ ማንኪያ ፐርሰሜሎ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው



እሠራር

1. ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ በጐድጓዳ ሣሀን ማደባለቅ ።
2. በመጥበሻ ላይ ዘይት አፍልቶ የአትክልቱን ድብልቅ በመጠኑ በማንኪያ እያወጡ በዘይት መጥበስ ።
3. ሲበስል አውጥቶ ወረቀት ላይ በማስቀመጥ ዘይቱን እንዲመጥ ማድረግ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

386. የአጓት ሾርባ ።

8 ኩባያ አጓት
2 እንቁላል
½ ኩባያ ስኳር
2 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ልጣጭ ፣ የተከተፈ

እሠራር

1. እንቁላሉን በወፍራሙ መምታት ።
2. በትንሽ በትንሹ ስኳር እየጨመሩ መምታት ።
3. የሎሚ ልጣጩንና አጓቱን መጨመር ።
4. በረዶ ቤት ውስጥ ለሁለት ሰዓት አቀዝቅዞ ወዲያው ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

387. የክሬም ብስኩት ።

⅔ ኩባያ ክሬም
3 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
2 እንቁላል ፣ የተመታ
⅓ ኩባያ ቅቤ
2 ኩባያ ስኳር
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
1 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
1 የሻይ ማንኪያ ቀረፋ
½ የሻይ ማንኪያ ቅርንፉድ
½ የሻይ ማንኪያ ነውዝ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው

### አሠራር

1. ቅቤውንና ስኳሩን አደባልቆ በሹካ በመጫን ማዋሐድ ።
2. እንቁላልና ቫኒላ ጨምሮ ማደባለቅ ።
3. ዱቄት ፣ ቀረፋ ፣ ቅርንፉድ ፣ ቤኪንግ ፓውደር ፣ ነውዝና ጨው በአንድ ላይ ማደባለቅ ።
4. ክሬሙንና በተራ ቁጥር 3 የተዘጋጀውን በማፈራረቅ ከቅቤና ከስኳሩ ጋር ማደባለቅ ።
5. በተዘጋጀ መጋገሪያ ዕቃ ላይ በመጠኑ በማንኪያ እያወጡ ማድረግ።
6. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአሥራ ሁለት ደቂቃ ማብሰል ።

አርባ ሁለት የክሬም ብስኩት ይወጣዋል ።

## 388. የእርጎ ኬክ ።

1 ኩባያ እርጎ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
1 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ሶዳ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
1 እንቁላል

### አሠራር

1. የፉርኖ ዱቄት ቤኪንግ ሶዳ ፣ ጨውና ስኳሩን በአንድ ላይ መንፋት ።
2. እንቁላል ፣ እርጎና ቅቤ አደባልቆ በተራ ቁጥር 1 ከተዘጋጀው ጋር ማዋሐድ ።
3. የተዘጋጀውን ድብልቅ መጋገሪያ ዕቃ ላይ በመጠኑ በማንኪያ እየቆነጠሩ መጨመር ።
4. መካከለኛ ሙቀት ባለው ምድጃ ማብሰል ።

አሥራ ስምንት የእርጎ ኬክ ይወጣዋል ።

## 389. የዝንጅብል ዳቦ ።

2$\frac{1}{3}$ ኩባያ ፉርኖ ዱቄት
1$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ዝንጅብል ፣ የተፈጨ



1 እንቁላል ፣ የተመታ
4 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 ኩባያ የተፈላ ውኃና ስኳር
1 ኩባያ ክሬም
1 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ሶዳ

### አሠራር

1. የፈላውን ስኳር ፣ ክሬምና እንቁላሉን ማደባለቅ ።
2. ዱቄት ፣ ቤኪንግ ሶዳ ፣ ዝንጅብልና ጨው በአንድ ላይ መንፋት ።
3. በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተዘጋጀውን በደንብ ማዋሐድ ።
4. ቅቤውን ጨምሮ ማደባለቅ ።
5. መጋገሪያ ዕቃውን ዘይት ወይም ቅቤ መቀባት ።
6. የተዘጋጀውን ድብልቅ መጋገሪያ ዕቃው ላይ መገልበጥ ።
7. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ከሠላሳ እስከ አርባ ደቂቃ ማብሰል ።

ከስምንት እስከ አሥር ሰው ይመግባል ።

## 390. የክሬምና የድንች ሰላጣ ።

4 ኩባያ ድንች ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ዱባ ፣ የተከተፈ
3 እንቁላል ፣ የተቀቀለ
1$\frac{1}{2}$ ኩባያ ክሬም
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ማዮኔዝ
1 የሾርባ ማንኪያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
$\frac{3}{4}$ የሻይ ማንኪያ የሰዴኖ ቅጠል
1$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ኮምጣጤ
1 የሻይ ማንኪያ ሰናፍጭ
ሰላጣ ቅጠል

### አሠራር

1. ድንች ፣ ዱባ ፣ ሽንኩርት ፣ የሰዴኖ ቅጠል ፣ ጨውና ቁንዶ በርበሬ በጐድጓዳ ሣህን ማደባለቅ ።

2. የተቀቀለውን እንቁላል አስኳሉንና ዞፉን ለይቶ ዞፉን ለብቻው መከተፍ ።
3. የተከተፈውን የእንቁላል ዞፍ ከድንችና ከዱባው ድብልቅ ጋር ማዋሐድ ።
4. የእንቁላል አስኳል ፣ ማዮኔዝ ፣ ኮምጣጤና ሰናፍጭ በተራ ቊጥር 3 ከተዘጋጀው ጋር ማደባለቅ ።
5. ለአሥራ አምስት ደቂቃ በረዶ ቤት ውስጥ አቀዝቅዞ በሰላጣ ቅጠል አጊጦ ማቅረብ ።

## 391. በክሬም የተሠራ የሰላጣ ማጣፈጫ ።

1 ኩባያ ክሬም
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሻይ ማንኪያ ስኳር
1 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
2 የሾርባ ማንኪያ ኮምጣጤ
ትንሽ ሚጥሚጣ

### አሠራር

1. ጨው ፣ ስኳርና ፣ ሚጥሚጣ ከኮምጣጤና ከሎሚ ጭማቂ ጋር ማደባለቅ ።
2. ክሬሙን ጨምሮ ማዋሐድ ።

አንድ ኩባያ ተኩብ የሰላጣ ማጣፈጫ ይወጣዋል ።

## 392. ቅመማቅመም በእርጎ ።

1 ኩባያ እርጎ
2 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
1 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ሶዳ
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ቅቤ
1 ኩባያ ስኳር
1 እንቁላል ፣ የተመታ
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቀረፋ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቅርንፉድ
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ገውዝ
ትንሽ ጨው



### አሠራር

1. ቅቤና ስኳሩን በሹካ እየተጫኑ ማደባለቅ ።
2. እንቁላልና ፣ ቫኒላውን ከቅቤና ከስኳሩ ጋር ማደባለቅ ።
3. ዱቄት ቤኪንግ ሶዳ ፣ ቀረፋ ፣ ቅርንፉድ ፣ ገውዝና ጨው በአንድ ላይ መንፋት ።
4. የተደባለቀውን ዱቄትና እርጎ በየተራ በመጨመር ከእንቁላልና ከቅቤው ጋር ማዋሐድ ።
5. ዘይት ወይም ቅቤ በተቀባ የመጋገሪያ ዕቃ ላይ ገልብጦ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

## 393. ፍሩት ኮክቴል ።

$\frac{1}{2}$ ኪሎ ፍራፍሬ—ብርቱካን ፣ ሙዝ ፣ ግሬፕ ፍሩት ፣ አናናስ
1 ኩባያ ጅንጀር ኤል
የናና ቅጠል
ስኳር

### አሠራር

1. ፍራፍሬውን አደባልቆ በረዶ ቤት ውስጥ ማቀዝቀዝ ።
2. የቀዘቀዘው ፍራፍሬ ላይ ጅንጀር ኤሉን አቀዝቅዞ መጨመር ።
3. በስኳርና በናና ቅጠል አጊጦ ማቅረብ ።

አራት ሰው ይመግባል ።

## 394. ፍሩት ሮልስ ።

2 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት ፣ የተነፋ
2 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
$\frac{3}{4}$ ኩባያ ወተት
$\frac{1}{4}$ ኩባያ የቀለጠ ቅቤ
እንጆሪ ወይንም አናናስ

አሠራር

1. ዱቄት ፥ ቤኪንግ ፓውደርና ጨው በአንድ ላይ መንፋት ።
2. ቅቤ ጨምሮ በሹካ እየተጫኑ እስከሚያያዝ ድረስ ማደባለቅ ።
3. ወተት ጨምሮ ማዋሐድ ።
4. ዱቄት ጣውላ ወይም መክተፊያ ላይ ነስንሶ ሊጡን እላዩ ላይ መዳመጥ ።
5. የተዳመጠውን ሊጥ የቀለጠ ቅቤ መቀባት ።
6. ቅባት የተቀባው ሊጥ ላይ እንጆሪ ወይም እናናስ ጨምሮ መጠቅለል ።
7. የተጠቀለለውን አትክልት በክቡ መቍረጥ ።
8. በቅባት በታሰሰ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ሙቀቱ 425 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአሥራ አምስት ደቂቃ እያገላበጡ ማብሰል ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

395. በፍም ላይ የተጠበሰ ዶሮ ።

1 ዶሮ
½ ኩባያ ቅቤ ፥ የቀለጠ
1 ትንሽ ሽንኩርት
115 ግራም እንጉዳይ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ
የተፈጨ ዳቦ
ፐርስሜሎ ፥ የተከተፈ
ትንሽ ነጭ ሽንኩርት

አሠራር

1. ዶሮውን እጥቦ ሆድ ዕቃውን ማውጣት ።
2. የታጠበውን ዶሮ ሁለት ቦታ መሰንጠቅ ።
3. የተሰነጠቀውን ዶሮ ፥ ፐርስሜሎ ፥ ሽንኩርት ፥ እንጉዳይ ፥ ነጭ ሽንኩርት ፥ ጨው ፥ ቁንዶ በርበሬና ቅቤ አደባልቆ ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ከድኖ እያገላበጡ ማብሰል ።



4. ዶሮውን ከብረት ድስት ውስጥ አውጥቶ በተፈጨ ዳቦ መለወስ ።
5. የከሰል ወይም የእንጨት ፍም ላይ ወፍራም የብረት ወንፊት አስቀምጦ ዶሮውን ብረቱ ላይ አድርጎ እያገላበጡ አጋም እስኪመስል መጥበስ ።

ሁለት ሰው ይመግባል ።

396. በፍም ላይ የተጠበሰ ዶሮና ቲማቲም ።

1 ዶሮ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
2 ቲማቲም
4 በስሱ የተቈረጠ ቤከን—የአሳማ ሥጋ
ጨው
ቁንዶ በርበሬ
ስኳር
ዳቦ ፥ የተጠበሰ

አሠራር

1. ዶሮውን እጥቦ ሆድ ዕቃውን ማውጣት ።
2. ትንሽ ውኃ አፍልቶ ዶሮውን በመጠኑ መቀቀል ።
3. የዶሮውን ብልት አውጥቶ በጥንቃቄ ሥጋውን ከአጥንቱ መለየት ።
4. ፍም ላይ ወፍራም የብረት ወንፊት አስቀምጦ ሥጋውን እላዩ ላይ አድርጎ እያገላበጡ መጥበስ ።
5. ቲማቲሙን ሁለት ቦታ ቈርጦ ከጨው ፥ ከቁንዶ በርበሬና ከስኳር ጋር ማደባለቅ ።
6. ፍሙ ላይ ባለው ወፍራም የብረት ወንፊት የቲማቲሙን ድብልቅ እያገላበጡ መጥበስ ።
7. ቤከኑን በመጥበሻ መጥበስ ።
8. የተዘጋጀውን ዶሮ ፥ ቲማቲምና ቤከን ከተጠበሰ ዳቦ ጋር ማቅረብ።

ሁለት ሰው ይመግባል ።

397. ተጠብሶ የተቀቀለ ዶሮ ።

2 ኪሎ ዶሮ
¼ ኩባያ የፋርኖ ዱቄት
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ

2 የሻይ ማንኪያ ጨው
$3\frac{1}{2}$ ኩባያ ውኃ ፣ የፈላ
ሚጥሚጣ

### አሠራር

1. ዶሮውን አጥቦ ብልቱን ማውጣት ።
2. የዶሮ ብልት ላይ ዱቄት ነስንሶ በቅቤ መጥበስ ።
3. ጨው ፣ ሚጥሚጣና ውኃ የተጠበሰው ዶሮ ላይ መጨመር ።
4. ከአንድ ተኩል እስከ ሦስት ሰዓት ከድኖ ማብሰል ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 398. ለአራት የሚሆን ዶሮ በአትክልት ።

2 ኪሎ ዶሮ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
3 ድንች ፣ የተላጠ
6 ትንንሽ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
1 ጥቅል የአበባ ጎመን ወይም ጥቅል ጎመን
12 ትንሽ ካሮት ፣ የተላጠ
ፐርሴሜሎ

### አሠራር

1. ዶሮውን አጥቦ ብልቱን ማውጣት ።
2. የተገነጠለውን ዶሮ በብረት ድስት ከሁለት እስከ ሦስት ሰዓት ከድኖ በቂ ውኃ ጨምሮ ማብሰል ።
3. ጨው ጨምሮ የበሰለውን ዶሮ ከመረቁ ውስጥ ማውጣት ።
4. ድንች ፣ ሽንኩርት ፣ የአበባ ጎመን ፣ ካሮት ዶሮው መረቅ ውስጥ ጨምሮ ማብሰል ።
5. የበሰለውን ዶሮና አትክልቱን በአንድ ሣህን ላይ አድርጎ በፐር ሰሚሎ እጊጦ ማቅረብ ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመግባል ።



## 399. ዶሮ በሩዝ ።

$1\frac{1}{2}$ ኪሎ ዶሮ
1 ኩባያ ሩዝ ፣ ያልተቀቀለ
$2\frac{1}{2}$ ኩባያ የዶሮ መረቅ
2 ፍሬ ነጭ ሽንኩርት ፣ የተፈጨ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 ትንሽ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ቲማቲም ፣ የተቀቀለ
1 የሾርባ ማንኪያ ፐርሰሜሎ ፣ የተከተፈ
1 ቃሪያ ፣ በስሱ የተቈረጠ
1 ፍንካች ነጭ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
ትንሽ ሽንኩርት ፣ በስሱ የተቈረጠ
ውኃ

### አሠራር

1. ዶሮውን አጥቦ መገንጠል ።
2. የተገነጠለውን ዶሮ፣ቀይ ሽንኩርት፣ነጭ ሽንኩርት፣ጨውና ውኃብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ ለአንድ ሰዓት ወይም እስኪበስል መቀቀል ።
3. ሩዙን በቅቤ አጋም እስኪመስል ማቁላላት ።
4. ቀይ ሽንኩርት ፣ ነጭ ሽንኩርት ፣ ቲማቲም ፐርሰሜሎ ፣ ቃሪያና የዶሮ መረቅ ከተቁላላው ሩዝ ጋር አደባልቆ እስኪበስል መቀቀል ።
5. የተዘጋጀውን ዶሮና ሩዝ አንድ ላይ ማቅረብ ።

አምስት ሰው ይመግባል ።

## 400. ዶሮ በማካሮኒ ።

$1\frac{1}{2}$ ኩባያ ማካሮኒ ፣ የተቀቀለ
2 ኩባያ የዶሮ ሥጋ ፣ የተከተፈ
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
85 ግራም ፎርማጆ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው

አሠራር

1. የተፈጨ ዳቦ ፡ የዶሮ ሾርባ ፡ የዶሮ ሥጋ ፡ ፐርሰሜሎ ፡ ጨውና እንቁላል አደባልቆ በቅባት በታሰሰ መጋገሪያ ላይ ማድረግ ።
2. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ከአርባ አምስት እስከ ስድሳ ደቂቃ ማብሰል ።
3. ትኩሱን ወይም ሲበርድ ማቅረብ ።

ከአራት እስከ አምስት ሰው ይመግባል ።

404. የዶሮና የፍራፍሬ ሰላጣ ።

3 ኩባያ የዶሮ ሥጋ ፡ ተቀቅሎ የተከተፈ
1 ብርቱካን
15 የወይን ፍሬ
1 ሙዝ
1 ፖም
1 እናናስ
1 ኩባያ ማዮኔዝ
ሰላጣ ቅጠል

አሠራር

1. ብርቱካኑን ልጦ ፍሬውን አውጥቶ መቈራረጥ ።
2. ወይኑን ሁለት ቦታ ቈርጦ ፍሬውን ማውጣት ።
3. ሙዙን ልጦ በስሱ መቍረጥ ።
4. ፖሙን አጥቦ በስሱ መቍረጥ ።
5. እናናሱን ልጦ መክተፍ ።
6. ከተራ ቍጥር 1 እስከ 5 የተዘጋጁትን ፍራፍሬ ከዶሮ ሥጋ ጋር ማደባለቅ ።
7. ሰላጣ ቅጠሉን አጥቦ ሣሀን ላይ ማድረግና የዶሮ ሥጋና የፍራፍሬ ድብልቁን ሰላጣው ላይ ጨምሮ አቀዝቅዞ ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።



405. የዓሣና የድንች ካሴሮል ።

2 ኩባያ ድንች ፡ ተቀቅሎ የተፈጨ
2 ኩባያ ዓሣ ፡ ተቀቅሎ የተከተፈ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
½ ኩባያ ፎርማጅ
ፐርሰሜሎ

አሠራር

1. ድንች ፡ ዓሣና ጨው ማደባለቅ ።
2. የተደባለቀውን ድንችና ዓሣ በቅባት የታሰሰ መጋገሪያ ዕቃ (ካሴሮል) ላይ ማድረግ ።
3. ፎርማጁውን እላዩ ላይ ነስንሶ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሠላሳ ደቂቃ ወይም እጋም እስኪመስል ማብሰል ።
4. በፐርሰሜሎ አጊጦ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

406. የዶሮና የአትክልት ካሴሮል ።

2½ ኪሎ ዶሮ
3 ካሮት ፡ ተልጦ የተከተፈ
1 ኩባያ ሰዴኖ ፡ የተከተፈ
1 ሽንኩርት ፡ የተከተፈ
1 ቃሪያ ፡ የተከተፈ
1 ኩባያ የፈላ ውኃ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1½ የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 ኩባያ ወተት
ጨው
ቁንዶ በርበሬ
የፉርኖ ዱቄት
ዘይት ፡ ለመጥበሻ

### አሠራር

1. ዶሮውን ገነጣጥሎ ማጠብ ።
2. ጨውና ቁንዶ በርበሬ ከተገነጣጠለው የዶሮ ሥጋ ጋር ማደባለቅ።
3. የዶሮው ሥጋ ላይ ዱቄት ነስንሶ በዘይት መጥበስ ።
4. የተጠበሰውን የዶሮ ሥጋ በቅባት በታሰሰ መጋገሪያ ዕቃ (ካሴሮል) ላይ ማድረግ ።
5. ካሮት ፥ ሽንኩርት ፥ ሰዴኖ ፥ ቃሪያና የፈላውን ውኃ አደባልቆ መጋገሪያ ዕቃው ላይ ጨምሮ መክደን ።
6. ሙቀቱ 275 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሦስት ሰዓት ሲያስፈልግ ውኃ እየጨመሩ ማብሰል ።
7. ቅቤውን አቅልጦ ዱቄት ፥ ጨውና ወተት ጨምሮ እስኪወፍር ማብሰል ።
8. ከምድጃ ውስጥ ከዶሮው ጋር የበሰለውን የአትክልት ድብልቅ አውጥቶ በተራ ቍጥር 7 ከተዘጋጀው ሶስ ጋር አደባልቆ ከዶሮ ሥጋው ጋር ማቅረብ ።

ከስምንት እስከ አሥር ሰው ይመግባል ።

## 407. የሃንጋሪ የዶሮ አሠራር ።

2—2½ ኪሎ ዶሮ
6 ሽንኩርት ፥ በስሱ የተቈረጠ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 የሾርባ ማንኪያ ሚጥሚጣ
3 ቲማቲም ፥ የተከተፈ
3 ቃሪያ ፥ የተከተፈ
ጨው

### አሠራር

1. ዶሮውን ገነጣጥሎ ማጠብ ።
2. ሽንኩርቱን በቅቤ አቁላልቶ ዶሮና ሚጥሚጣውን መጨመር ። ጨውና ትንሽ ውኃ ጨምሮ ለአንድ ሰዓት በመጠነኛ እሳት ላይ ማንተክተክ ።
3. ቲማቲምና ቃሪያውን ጨምሮ እንደገና ለአንድ ሰዓት ማብሰል ።

አራት ሰው ይመግባል ።



## 408. ዶሮ በአሳማ ሥጋ ።

1 ሥጋው የተገነጣጠለ ዶሮ
100 ግራም የአሳማ ሥጋ ፥ አስፈላጊ ከሆነ
½ ኩባያ ፋርኖ ዱቄት
2 የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
3 የሾርባ ማንኪያ የሰላጣ ዘይት
½ ኪሎ ተልጦ የተፈጨ ቲማቲም
1 ትንሽ ቆርቆሮ የቲማቲም ድልህ
3 ትልልቅ ፔፐሮኒ
1 የሻይ ማንኪያ አዝማሪኖ
1 ቀይ ሽንኩርት ፥ በደቃቁ የተከተፈ
8 የሾርባ ማንኪያ ነጭ ቪኖ

### አሠራር

1. ፋርኖ ዱቄት ፥ ቁንዶ በርበሬ አንድ ላይ ማደባለቅ ።
2. የተገነጣጠለውን የዶሮ ሥጋ የተቀመመው የፋርኖ ዱቄት ውስጥ እያስነኩ በአራት የጠረጴዛ ማንኪያ ቅቤ ፥ በሦስት የሾርባ ማንኪያ ዘይት ለአሥራ ሁለት ደቂቃ ማብሰል ።
3. አጋም ሲመስል ከድስቱ ውስጥ ሥጋውን አውጥቶ በቀረው ቅባት ሽንኩርት ጨምሮ ለሦስት ወይም ለአራት ደቂቃ ማቁላላት ።
4. የተጠበሰውን ዶሮ ቁሌቱ ውስጥ መጨመር ።
5. ቪኖ ፥ አዝማሪኖ ቲማቲምና ድልህ ጨምሮ ቪኖው እስቲዋሐድ እያገላበጡ ማማሰል ። እንደገና ለአርባ ደቂቃ ከድኖ ማብሰል ።
6. በመጨረሻ ፔፐሮኒ ፥ በዘይት የተጠበሰ የአሳማ ሥጋ ጨምሮ ከዶሮው ሥጋ ጋር ለአሥራ አምስት ደቂቃ አብስሎ ማውረድ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 409. በጥቅል ጎመን የተጠቀለለ ሥጋ ።

1 ኪሎ ሥጋ ፥ የተፈጨ
¼ ኪሎ ሩዝ
1 ጥቅል ጎመን

1 የሾርባ ማንኪያ የተፈጨ ዳቦ
2 እንቁላል
2 የሾርባ ማንኪያ የተፈጨ ፐርሰሜሎ
2 የሾርባ ማንኪያ ፎርማጆ
2 ፍሬ ነጭ ሽንኩርት ፡ የተፈጨ
ጨው ፡ ቁንዶ በርበሬ
ቅባት የተቀባ ወረቀት—ካርታ አልያታ
ትንሽ ዘይት ፡ ማዮኔዝ ፡ ካሮት ፡ ድንች

አሠራር

1. ቶናውን ከቆርቆሮ አውጥቶ በጐድጓዳ ሣህን ውስጥ መገልበጥ ።
2. በወተት ወይም በውኃ የራሰውን ዳቦ በእጅ ጨምቆ ከቶና ጋር መደባለቅ ።
4. የተፈጨውን ዳቦ ፡ እንቁላል ፡ ፐርሰሜሎ ፡ ፎርማጆ ፡ ነጭ ሽንኩርት ፡ ጨው ፡ ቁንዶ በርበሬ ጨምሮ በደንብ ማማሰል ።
3. ማብሰያውን ወረቀት (ካርታ አልያታ) ዘይት ቀብቶ በሁለት ከፍሎ የቶና ቅልቅሉን እሁለት ላይ ከፍሎ በእጅ የዝኩኒ ቅርጽ አውጥቶ ሁለት ጫፉን በክር አሥሮ ለግማሽ ሰዓት ያህል ጨው በገባበት የፈላ ውኃ ውስጥ ማብሰል ።
5. ከበሰለ በኋላ ውኃውን አፍስሶ ማቀዝቀዝ ፤ ከቀዘቀዘ በኋላ ወረቀቱን ልጦ በስሱ በክብ እየቈረጡ በአንድ ረጅም ሣህን ላይ አከማችቶ ቶናው ላይ ማዮኔዝ ቀብቶ በተጠበሰ ድንች ወይም ቲማቲም አጊጦ ማቅረብ ።

ሦስት ሰው ይመገባል ።

417. ዓሣ በኀመን፡ ቊጥር 1 ።

1 ኪሎ ዓሣ ፡ የተቈራረጠ
1 ኪሎ ድንች
½ ኪሎ ኀመን—ቆስጣ
½ ኪሎ ስፒናች
6 የሾርባ ማንኪያ ፐርሰሜሎ
2 ሽንኩርት ቺፖሊኒ
8 ፍንካች ነጭ ሽንኩርት
2 ኩባያ ዘይት
ጨው ፡ ቁንዶ በርበሬ



አሠራር

1. ኀመን—ቆስጣ—ስፒናች ፡ ፐርሰሜሎ ፡ ቺፖሊኒ አጥቦ መክተፍና ውኃው እስቲንጠፈጠፍ በፓስታ ማጥለያ ላይ አቆይቶ ጨው መነስነስ ።
2. ድንቹን ልጦ መክተፍ ።
3. ነጭ ሽንኩርት በደቃቁ ከትፎ ዓሣው ላይ ጨውና ቁንዶ በርበሬ ነስንሶ በሣህን ውስጥ ማቆየት ።
4. ከተከተፈው ኀመን ላይ ቀንሶ ድስት ውስጥ ማንጠፍ ። ከዓሣና ከድንቹ እንዲሁም ከነጭ ሽንኩርት ጨምሮ እላዩ ላይ ዘይት ጨምሮ ሙቀቱ 300 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአንድ ሰዓት ያህል ሳይማሰል አብስሎ ማውረድ ።

አሥር ሰው ይመገባል ።

418. የዓሣ ጥብስ ።

1 ኪሎ ለጥብስ የሚሆን ዓሣ
2 የሾርባ ማንኪያ ጨው
2 እንቁላልና ለመጥበሻ የሚሆን ዘይት
1 ኩባያ ወተት ወይም ውኃ
2 ኩባያ የተፈጨ ዳቦ ወይም የበቆሎ ከክ
2 የተቈራረጠ ሎሚ
ፐርሰሜሎ ፡ የተከተፈ
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ዓሣውን በጥንቃቄ አጥቦ እንደ አስፈላጊነቱ ቈራርጦ ማዘጋጀት ።
2. ጨውና ቁንዶ በርበሬ መነስነስ ።
3. ዓሣ ፡ ወተትና እንቁላል አንድ ላይ ደባልቆ የተፈጨውን ዳቦ ማድቦልቦል ።
4. ብዛት ያለው ዘይት በተጨመረበት መጥበሻ ላይ ለአሥር ደቂቃ መጥበስ ።
5. በሁለቱም በኩል አጋም እስኪመስል ጠብሶ በወረቀት ላይ ማድረግ።
6. ፐርሰሜሎ ነስንሶ እላዩ ላይ ሎሚ ጨምቆ ትኩሱን ማቅረብ ።

419. የሰርዲን ጥብስ ።

3 ቆርቆሮ ሰርዲን
4 ትልልቅ የበሰለ ድንች

1 እንቍላል
2 የሾርባ ማንኪያ ዘይት
ፉርኖ ዱቄት ወይም የተፈጨ ዳቦ
ለመጥበሻ የሚሆን ማርገሪን ወይም ዘይት
ቁንዶ በርበሬ ፣ ጨው

አሠራር

1. ከሰርዲኑ ዘይቱን አጠንፍፎ በሹካ እየተጫኑ ማላም ።
2. ድንቹን ፈጭቶ ሰርዲኑ ከጨውና ቁንዶ በርበሬ ጋር ማደባለቅ ።
3. እንቍላሉን መትቶ ዘይት መጨመር ።
4. ከሰርዲኑ ድብልቅ በሾርባ ማንኪያ እየቆነጠሩ እንደ አስፈላጊነቱ ቅርጽ እያወጡ በተመታው እንቍላል ነክሮና በተፈጨ ዳቦ ውስጥ ለውሶ በዘይት ወይም በማርገሪን መጥበስ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

420. ምድጃ ውስጥ የበሰለ ዓሣ ።

6 ጥቁር ዓሣ ፣ ቆዳው የተገፈፈ
2 መካከለኛ ቀይ ሽንኩርት ፣ በደቃቁ የተከተፈ
16 የወይራ ፍሬ—አሊቭ—የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ የተከተፈ ፐርሰሜሎ
4 የሾርባ ማንኪያ የሰላጣ ዘይት
2 ኩባያ የተፈጨ ቲማቲም
2 የሾርባ ማንኪያ ካፐሬስ
2 የሾርባ ማንኪያ የተከተፈ ሰዴኖ
ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ዓሣውን አጽድቶ ቅቤ የተቀባ ድስት ውስጥ ማድረግ ።
2. ሽንኩርቱን አጋም እስኪመስል ድረስ በዘይት ማቁላላት ።
3. ቲማቲምና ቁንዶ በርበሬ ጨምሮ ለኦምስት ደቂቃ ማቁላላት ።
4. የወይራ ፍሬ (አሊቭ) ፣ ፐረሰሜሎ ፣ ካፐሬስ ሰዴኖ መጨመር ።
5. ለአሥራ አምስት ደቂቃ ያህል አቁላልቶ የተዘጋጀውን ዓሣ በማንኪያ መጨመር ።



6. የሙቀቱ ኃይል 375 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሃያ አምስት ደቂቃ አብስሎ ትኩሱን ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

421. ዓሣ በኀመን ፣ ቍጥር 2 ።

1 ኪሎ የተቈራረጠ ዓሣ
1 ኪሎ ቆስጣ ወይም ስፒናች
10 የሾርባ ማንኪያ ያልተከተፈ ፐርሰሜሎ
4 ራስ እንስላል ፣ (ፎኖኪዮ) ፣ በቁመቱ የተከተፈ
1 ኪሎ ቲማቲም ፣ በኩብ የተመተረ
4 የሻይ ማንኪያ ጨው
4 የሻይ ማንኪያ በደቃቁ የተከተፈ ነጭ ሽንኩርት
2 ኩባያ ዘይት

አሠራር

1. ቆስጣውን ወይም ስፒናቹን ከሥሩ ቈርጦ ቅጠሉን አጥቦ ማዘጋጀት ።
2. ፐርሰሜሎ ፣ እንስላል ፣ ጨው ኀመኑ ውስጥ ጨምሮ ማዋሐድ ።
3. በተራ ቍጥር 1 እና 2 የተዘጋጀውን ድብልቅ ግማሹን ድስት ውስጥ ማንጠፍ ። ዓሣውን እላዩ ላይ መደረብ ። እላዩን በቀረው ኀመን ከድኖ በቲማቲም ሸፍኖ እላዩ ላይ ዘይት አፍስሶ ሙቀቱ መጠነኛ በሆነ እሳት ላይ ለአንድ ሰዓት ያህል ማብሰል ። ዓሣው መብሰሉን በሹካ ወጋ ወጋ አድርጎ በማረጋገጥ አውርዶ ቀዝቀዝ ሲል ማቅረብ ።

ከስምንት እስከ አሥር ሰው ይመግባል ።

422. ከብ ሥጋ የተሞላ እርሰቶ ።

1—2 ኪሎ ከብ የሆነ ሥጋ
3 በደንብ የበሰለና የተመተረ እንቍላል
2 ካሮት ፣ ተልጦ የተከተፈ
የተከተፈ ፐርሰሜሎ
የተከተፈ ሰዴኖ ፣ የተከተፈ ነጭ ሽንኩርት
ቁንዶ በርበሬ
ዘይት ወይም ቅቤ ፣ ለመጥበሻ

ሥራ አምስት ደቂቃ ልዩነት በመብሰል ላይ ያለው ሎፍ ውስጥ ቅቤና ውኃውን አደባልቆ መጨመር ።
4. አንድ ሰዓት ተኩል ያህል ማብሰል ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

443. ተጠቅልሎ የበሰለ ሥጋ—የሥጋ አሮስቶ ።

1 የጭቅና ሥጋ
1 እንቍላል ፣ የተመታ
1 ኩባያ ካሮት ፣ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ሰዴኖ ፣ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ቲማቲም ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
1 ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
3 የሻይ ማንኪያ ቅቤ
$1\frac{1}{2}$ ኩባያ ውኃ ፣ የሞቀ

አሠራር

1. ሥጋውን መክተፊያ ላይ በሥጋ መምቺያ በመጠኑ ቀጥቅጦ መዘርጋት ።
2. እንቍላል ፣ ካሮት ፣ ሽንኩርት ፣ ሰዴኖ ፣ ቲማቲም ፣ ጨውና የተፈጨ ዳቦ በጐድጓዳ ሣህን ውስጥ ማደባለቅ ።
3. በተራ ቍጥር 2 የተዘጋጀውን የእንቍላልና የአትክልት ድብልቅ ሥጋው ላይ አድርጎ መጠቅለልና በክር ማሰር ።
4. ቅቤውን ብረት ድስት ውስጥ ማቅለጥ ። ዱቄቱንና ቁንዶ በርበሬውን ጨምሮ አጋም እስኪመስል ማብሰል ።
5. በተራ ቍጥር 4 የተዘጋጀውን የተጠቀለለው ሥጋ ላይ መጨመር ።
6. የሞቀውን ውኃ ጨምሮ መክደን ።
7. ሙቀቱ 325 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአንድ ሰዓት ተኩል ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።



444. የሥጋና የአበባ ጎመን ሎፍ ።

1 ኪሎ የተፈጨ ሥጋ
$\frac{1}{2}$ ኪሎ የአሳማ ሥጋ ፣ የተፈጨ
1 የአበባ ጎመን ፣ የተቀቀለ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
1 የሻይ ማንኪያ ሰናፍጭ
2 እንቍላል ፣ የተመታ
1 ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{8}{4}$ ኩባያ ወተት
ቅርንፉድ ፣ ድፍን
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ
በአበባ ጎመን ፋንታ የተቀቀለ ካሮት ወይም አተር መጠቀም ይቻላል

አሠራር

1. ከአበባ ጎመኑ በስተቀር ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ በጐድጓዳ ሣህን ውስጥ ማደባለቅ ።
2. መካከሉ ላይ ክብ የቅርጽ ማውጫ ባለው ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ መሙላት ።
3. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአንድ ሰዓት ተኩል ማብሰል ።
4. ከበሰለ በኋላ ሎፉን ከመጋገሪያ ዕቃው ውስጥ አውጥቶ መካከሉ ላይ የአበባ ጎመኑን ማድረግ ።

አሥራ ሁለት ሰው ይመግባል ።

445. የእንግሊዝ ሆት ፖት ።

600 ግራም የጥጃ ሥጋ
6 ድንች ፣ ተልጦ የተከተፈ
2 ሙሉ ኩላሊት
1 ትልቅ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ

1 ኩባያ ውኃ
ጨው
ቁንዶ በርበሬ

## አሠራር

1. ግማሹን ድንች የተቀባ መጋገሪያ (ካሴሮል) ላይ ማድረግ ።
2. ሥጋውንና ሆላሊቱን ቈራርጦ ድንቹ ላይ አድርጎ ጨውና ቁንዶ በርበሬ መነስነስ ።
3. ውኃ መጨመር ።
4. ቀሪውን ድንች ሥጋው እስኪሸፈን ድረስ መጨመር ።
5. በመጨረሻ ቅቤውን መጨመር ።
6. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሁለት ሰዓት ማብሰል ።

ከአራት እስከ ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 446. የጥጃ ሥጋ ካሴሮል ።

1 ኪሎ የጥጃ ሥጋ
2 የሻይ ማንኪያ ሽንኩርት፣የተከተፈ
4 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
2 የሻይ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
$\frac{3}{4}$ ኩባያ የሥጋ መረቅ
1 ኩባያ ቲማቲም፣የተከተፈ
1 ኩባያ እንጉዳይ፣የተከተፈ
ጨው፣ ቁንዶ በርበሬ
ሰዲኖ ፣ የተከተፈ

## አሠራር

1. ሥጋውን መከተፍ ።
2. ሥጋውንና ሽንኩርቱን አጋም እስኪመስል በቅቤ ማብሰል ።
3. የበሰለውን ሥጋ መጋገሪያ ዕቃ (ካሴሮል) ላይ ማድረግ ።
4. በቀሪው ቅቤ ዱቄቱን አጋም እስኪመስል ማብሰልና መረቁን ጨምሮ እያማሰሉ እስኪወፍር ማቆየት ።
5. በተራ ቍጥር 4 የተዘጋጀውን የዱቄት ድብልቅ ሥጋው ላይ መጨመር ።



6. ቁንዶ በርበሬ፣ ጨው፣ ቲማቲምና እንጉዳይ ጨምሮ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአንድ ሰዓት ማብሰል ።
7. የተከተፈ ሰዲኖ እላዩ ላይ ነስንሶ ማቅረብ ።

እራት ሰው ይመግባል ።

## 447. ለሽርሽር የሚዘጋጅ የተጠቀለለ ሥጋ ።

1$\frac{1}{4}$ ኪሎ የጥጃ ሥጋ
6 የሾርባ ማንኪያ ሽንኩርት
6 የሾርባ ማንኪያ ቃሪያ
2 የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
2 እንቍላል
2 ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
4 እንቍላል ፣ የተቀቀለ
ፐርስሜሎ፣የተከተፈ

## አሠራር

1. ሥጋ፣ ሽንኩርትና ቃሪያ በሥጋ መፍጪያ አንድ ላይ መፍጨት ።
2. ከተቀቀለው እንቍላል በስተቀር ጨው፣ ቁንዶ በርበሬ፣ እንቍላልና የተፈጨ ዳቦ ከተፈጨው ሥጋ ጋር ማደባለቅ ።
3. የሥጋውን ድብልቅ ዱቄት የተነሰነሰበት ጣውላ ወይም መክተፊያ ላይ አድርጎ መዘርጋት ።
4. በመክተፊያው ላይ የተዘረጋው ሥጋ ላይ የተቀቀለውን እንቍላል ጨምሮ ጠቅልሎ በክር ማሰር ።
5. የተጠቀለለውን ሥጋ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራሃንይት በሆነ ምድጃ ለአርባ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።
6. ፐርስሜሎውን እላዩ ላይ ነስንሶ ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 448. የተሞላ የበግ ሥጋ ።

የበግ የታፋ ሥጋ—ስድስት ቦታ የተቈራረጠ
225 ግራም ገብስ፣የተፈተገ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ

## 451. የአሳማ ሥጋና ስፓጌቲ ።

$\frac{1}{2}$ ኪሎ የአሳማ ሥጋ፣ የተፈጨ
$\frac{1}{2}$ ኪሎ ስፓጌቲ፣ የተቀቀለ
1 ኩባያ ሽንኩርት፣ የተከተፈ
$\frac{3}{4}$ ኩባያ ቲማቲም፣ የተቀቀለ
1 ኩባያ ፎርማጆ
$\frac{1}{8}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{2}$ ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ

### አሠራር

1. ሽንኩርቱንና የአሳማ ሥጋውን አጋም እስኪመስል ማብሰል ።
2. የበሰለውን ሥጋ ከስፓጌቲ፣ ከቲማቲም፣ ከጨውና ከፎርማጆ ጋር አደባልቆ ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ላይ ማድረግ ።
3. የተፈጨ ዳቦና ቅቤ ስፓጌቲው ላይ መጨመር ።
4. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሠላሳ ደቂቃ ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 452. የአሳማ ሥጋ በፎርማጆ ።

6 በስሱ የተቈረጠ የአሳማ ሥጋ
85 ግራም ፎርማጆ
6 የተቈረጠ ዳቦ

### አሠራር

1. ዳቦው ላይ ፎርማጆውን መቀባት ።
2. የአሳማ ሥጋውን ከፎርማጆው ላይ መደረብ ።
3. መጋገሪያ ላይ አድርጎ ምድጃ ውስጥ ፎርማጆው እስኪቀልጥ የአሳማው ሥጋ እስኪበስል ድረስ አቆይቶ ማውጣት ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።



## 453. የጉድን ሥጋ—የአሳማ አሮስቶ ።

የአሳማ ሥጋ ጉድን
ጨው
ቁንዶ በርበሬ
የሚሞላ፣ ከአትክልትና ከተፈጨ ዳቦ የተዘጋጀ

### አሠራር

1. የአሳማ ሥጋው ላይ ጨውና ቁንዶ በርበሬ መጨመር ።
2. አሮስቶ መሥሪያ ዕቃ ላይ የጉድን አጥንቱን በከቡ ማስቀመጥ ።
3. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአንድ ሰዓት ማብሰል ።
4. አሮስቶ መሥሪያውን ዕቃ ከምድጃ ውስጥ አውጥቶ ጉድኖቹን መገልበጥ ።
5. የበሰለውን የጉድን አጥንት የመካከሉን ክፍት ቦታ በተዘጋጀው የአትክልትና የተፈጨ ዳቦ ድብልቅ መሙላት ።
6. የአሮስቶ መሥሪያ ዕቃውን ምድጃ ውስጥ መልሶ የጉድን አጥንቱና አትክልቱ እስኪበስል አቆይቶ ማውጣት ።

## 454. የሩዝና የሃም ስካሎፕ ።

1 ኩባያ ሩዝ፣ ያልተቀቀለ
2 በስሱ የተከተፈ ሃም
3 ኩባያ ወተት
ጨው

### አሠራር

1. ሩዙን አጥቦ ውኃውን ማጠንፈፍ ።
2. ሃሙን ስድስት ቦታ መቍረጥ ።
3. መጋገሪያ ዕቃውን ቅቤ ቀብቶ ማዘጋጀት ።
4. ቅባት የተቀባው መጋገሪያ ዕቃ ላይ ሩዙን ከሥሩ ከዚያም ሃሙን እሩዙ ላይ መደረብ ።
5. ጨውና ወተት መጨመር ።
6. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአንድ ሰዓት ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

አሠራር

1. ዓሣውን በደንብ አጥቦ በተፈጨ ዳቦ ፥ በጨውና በቁንዶ በርበሬ ውስጥ እየነከሩ በዘይት ጠብሶ ማውጣት ።
2. በቀረው ዘይት ሽንኩርቱን እስኪለሰልስ አቁላልቶ ጨው ፥ ቁንዶ በርበሬ ፥ የሎሚ ጭማቂ ከዓሣው ጋር አዋሕዶ ማቅረብ ።

ከሁለት እስከ ሦስት ሰው ይመገባል ።

480. የተሞላ ዝኩኒ—የፈረንጅ ዱባ ።

4 መካከለኛ ዝኩኒ—የፈረንጅ ዱባ
1 ትንሽ ቀይ ሽንኩርት ፥ በወፍራሙ የተከተፈ
1 ካሮት ፥ በወፍራሙ የተከተፈ
1 የላውሮ ቅጠል
1 ኩባያ የዶሮ መረቅ—ዳዶ

መሙልያ ፤

2 የሾርባ ማንኪያ ማርገሪን
1 ትልቅ ቀይ ሽንኩርት ፥ በደቃቁ የተከተፈ
1 ፍንካች ነጭ ሽንኩርት ፥ በደቃቁ የተከተፈ
1 ኩባያ የተፈጨ ሥጋ
1 ኩባያ ቲማቲም ፥ ትልጦ የተፈጨ

አሠራር

1. ዝኩኒውን በአንድ ጫፍ በኩል በቢላዋ ቈርጦ ውስጡ ያለውን በማንኪያ ጕርጕሮ አውጥቶ ቆዳውን አልፎ አልፎ በቢላዋ መላጥ።
2. በፈላ ውኃ ውስጥ ለሁለት ደቂቃ ያህል ማብሰል ።
3. ማርገሪን አቅልጦ ሽንኩርቱን መጨመር ። ነጭ ሽንኩርት ፥ ሥጋ ፥ ቲማቲም ፥ ጨምሮ ለጥቂት ደቂቃ ማቁላላት ።
4. ጨውና ቁንዶ በርበሬ ጨምሮ ሲዋሐድ ማውረድ ።
5. በተራ ቍጥር 3 እና 4 የተዘጋጀው ከቀዘቀዘ በኋላ ዝኩኒው ውስጥ መሙላት ።
6. በአንድ ሰፊ ድስት በወፍራሙ የተመተረ ሽንኩርት ፥ ካሮት ፥ መረቅ ፥ ላውሮ ጨምሮ ዝኩኒውን የሙቀቱ ኃይል 375 ድግሪ ፋራ ንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለሃያ ወይም ለሠላሳ ደቂቃ ማብሰል ።
7. ዝኩኒው ላይ ከመረቁ ጨምሮ ማቅረብ ።

አራት ሰው ይመገባል ።



481. የጥጃ ሥጋ

½ ኪሎ የጥጃ ሥጋ
100 ግራም ካፕሬስ
1 የሻይ ማንኪያ የተፈጨ ሰናፍጭ
1 ቆርቆሮ ቶኖ
5 የሾርባ ማንኪያ ማዮኔዝ
ጨው ፥ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ሥጋውን በደንብ አብስሎ በስሱ መምተር ።
2. የተመተረውን ሥጋ በአንድ ከብ ሣህን ውስጥ ማስቀመጥ ።
3. ሃምሳ ግራም ካፕሬስ እድቅቆ መትሮ ከቶኖ ጋር ማደባለቅ ። ሰናፍጭና ማዮኔዝ ሥጋውን መቀባት ።
4. የቀረውን ካፕሬስ በደቃቁ መትሮ አላዩ ላይ ነስንሶ ሲቀዘቅዝ ማቅረብ ።

ከአራት እስከ አምስት ሰው ይመገባል ።

482. በቢራ የበሰለ የሥጋ አሮስቶ ።

1 ኪሎ ሥጋ
3 ኩባያ ቢራ
½ ኩባያ ማርገሪን
2 የሻይ ማንኪያ ጨው
¼ የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. በአንድ ወፍራም ድስት ውስጥ ማርገሪን ጨምሮ ሥጋውን አጋም እስኪመስል እያገላበጡ ማብሰል ።
2. ጨውና ቁንዶ በርበሬ ጨምሮ እንደገና መጥበስ ።
3. አንድ ኩባያ ከሩብ ቢራ ጨምሮ የሙቀቱ ኃይል መጠነኛ በሆነ እሳት ላይ ለሦስት ሰዓት ማብሰል ። እንደ አስፈላጊነቱ ቢራ ጠብ እያደረጉ ማብሰል ።
4. በስሱ እየቈረጡ በሰፊ ሣህን ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመገባል ።

### 483. ድንች በአሳማ ሥጋ ።

$\frac{1}{2}$ ኪሎ ድንች ፣ ተልጦ በአራት ማዕዘን የተከተፈ
100 ግራም የአሳማ ሥጋ
6 የሾርባ ማንኪያ ማርገሪን
1 ቀይ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
5 እንቁላል ፣ በመጠኑ የተመታ
5 የሾርባ ማንኪያ ውኃ
ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬ

**አሠራር**

1. ማርገሪን በትልቅ ድስት ውስጥ ማቅለጥ ።
2. ድንችና ሽንኩርቱን መጨመር ።
3. ድንቹ እስቲበስል ቀስ እያሉ ማማሰል ።
4. የአሳማ ሥጋውን መጨመር ።
5. እንቁላል ፣ ውኃ ፣ ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬ አንድ ላይ ቀላቅሎ ድንቹና የአሳማው ሥጋ ላይ አድርጎ ከድኖ ከሰባት እስከ ስምንት ደቂቃ እንቁላሉ እስኪበስልና ትንሽ ደረቅ እስኪል አብስሎ ማውጣት ።

አራት ሰው ይመገባል ።

### 484. የጥጃ ሥጋና የማካሮኒ ሰላጣ ።

2 ኩባያ ማካሮኒ ፣ የተቀቀለ
1 ኩባያ ሰሌሪ ፣ የተከተፈ
1½ ኩባያ የጥጃ ሥጋ ፡ ተቀቅሎ የተከተፈ
1 ሎሚ ፣ በስሱ የተቈረጠ
ማዮኔዝ

**አሠራር**

1. ማካሮኒ ፣ ሰሌሪና የጥጃ ሥጋውን ማደባለቅ ።
2. በተፈለገው መጠን ማዮኔዝ ጨምሮ ማዋሐድ ።
3. የሰላጣ ሣህን ላይ አድርጎ በሎሚ አጊጦ ማቅረብ ።

አምስት ሰው ይመገባል ።



### 485. የጥጃ ሥጋ ጥብስ በማካሮኒ ።

700 ግራም የጥጃ ሥጋ ፣ የተከተፈ
1½ ኩባያ ማካሮኒ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ጨው ያለው የአሳማ ሥጋ ፣ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
1 ኩባያ ሰሌሪ ፣ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ፐርሰሜሎ ፣ የተከተፈ
2 ኩባያ ውኃ

**አሠራር**

1. የአሳማ ሥጋው እጋም እስኪመስል መጥበስ ።
2. የጥጃ ሥጋው ላይ ዱቄት ነስንሶ የአሳማ ሥጋው ሲጠበስ በወጣው ቅባት በቀስታ እጋም እስኪመስል መጥበስ ።
3. የተጠበሰውን የአሳማ ሥጋና የጥጃ ሥጋ አደባልቆ ጨውና ውኃ ጨምሮ ከድኖ ለአንድ ሰዓት ተኩል በቀስታ ማንተከተክ ።
4. ማካሮኒውንና ሰሌሪውን ጨምሮ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ወይም ማካሮኒው እስኪበስል ድረስ መቀቀል ።
5. በሣህን ላይ አድርጎ ፐርሰሜሎ እላዩ ላይ ነስንሶ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመገባል ።

### 486. ሃንጋሪያን ጉላሽ ።

$\frac{1}{2}$ ኪሎ የበሬ ሥጋ
$\frac{1}{2}$ የጥጃ ወይም የአሳማ ሥጋ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
3 ኩባያ ውኃ ፣ የፈላ
$\frac{3}{4}$ ኩባያ ክሬም
3 የሾርባ ማንኪያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ፐርሰሜሎ ፣ የተከተፈ
1 የሾርባ ማንኪያ ሚጥሚጣ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
ማካሮኒ ፣ የተቀቀለ

## 490. የልብ ጉላሽ ።

1 ኩባያ ልብ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
1 ኩባያ የእሳማ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
2½ ኩባያ ሩዝ ወይም ማካሮኒ ፣ የተቀቀለ
2 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
1 ኩባያ ሰዴኖ ፣ የተከተፈ
½ ኩባያ ካሮት ፣ የተከተፈ
½ ኩባያ ቲማቲም ፣ የተከተፈ
½ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 ኩባያ ውኃ
1¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
½ ኩባያ ክሬም

### አሠራር

1. ልብ ፣ የእሳማ ሥጋና ሽንኩርት አጋም እስኪመስል በቅቤ ማቁላላት ።
2. ውኃ ፣ ጨው ፣ ካሮትና ሰዴኖ ጨምሮ ለሃያ ደቂቃ ማብሰል ።
3. ቲማቲምና ክሬሙን መጨመር ።
4. ዱቄቱን በትንሽ ውኃ በጥብጦ ጨምሮ እያማሰሉ እስኪወፍር ማብሰል ።
5. የበሰለውን የልብ ድብልቅ ከሩዝ ወይም ከማካሮኒ ጋር ማቅረብ ።

አምስት ሰው ይመግባል ።

## 491. ጣፋጭና ጉምዛዛ ልብ ።

2 የጥጃ ልብ
2 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
6 የሾርባ ማንኪያ ኮምጣጤ
2 የሻይ ማንኪያ ስኳር
¼ የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
3 ኩባያ ውኃ
1 ትንሽ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
ማካሮኒ ፣ የተቀቀለ



### አሠራር

1. ልቡን አጥቦ እላዩ ላይ ያለውን ስስ ሽፋንና ሥር ማላቀቅ ።
2. የተላጠውን ልብ መከተፍ ።
3. ዱቄቱን ከቅቤ ጋር አደባልቆ አጋም እስኪመስል ማብሰል ።
4. የተከተፈው ልብ ላይ ጨው ፣ ኮምጣጤ ፣ ስኳርና ውኃ ጨምሮ ከበሰለው ዱቄት ጋር ማዋሐድ ።
5. ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ ለ1 ሰዓት ተኩል ክድኖ ማብሰል ።
6. ከማካሮኒ ጋር ትኩሱን ማቅረብ ።

አራት ሰው ይመግባል ።

## 492. በውኃ የበሰለ ልብ ።

3 የበግ ወይም የበሬ ልብ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 የላውሮ ቅጠል
1 ሽንኩርት ፣ በወፍራሙ የተከተፈ
½ ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
½ ኩባያ ውኃ

### አሠራር

1. ልቡን አጥቦ ስቡን አላቅቆ በንጹሕ ጨርቅ ማድረቅ ።
2. በትንሽ በትንሹ መትሮ የጨውና የፉርኖ ዱቄት ድብልቅ ውስጥ መንከር ።
3 በአንድ ትልቅ መጥበሻ ላይ ቅቤ አቅልጦ የተመተረውን ልብ አጋም እስኪመስል መጥበስ ።
4. የተጠበሰውን ልብ አውጥቶ የቀረው መረቅ ላይ ሽንኩርት ፣ ላውሮና ውኃ መጨመር ። ለግማሽ ሰዓት ያህል ተከድኖ ከበሰለ በኋላ ላውሮውን አውጥቶ መረቁን ከተጠበሰው የልብ ሥጋ ላይ አድርጎ ትኩሱን ማቅረብ ።

አራት ሰው ይመግባል ።

5. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአንድ ሰዓት ወይም ሥጋው እስኪበስል ድረስ ማቆየት ።
6. የመጋገሪያውን ዕቃ ከዳን አንሥቶ ፔስትሪውን እላዩ ላይ መደረብ።
7. አየር እንዲወጣ ፔስትሪውን አልፎ አልፎ በሹካ መብሳት ።
8. የምድጃውን ሙቀት ወደ450 ድግሪ ፋራንሃይት ከፍ አድርጎ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ወይም ፔስትሪው አጋም እስኪመስል ማብሰል ።

አራት ሰው ይመግባል ።

497. ዡላሊት በዳቦ ።

2 ዡላሊት
1 እንቁላል
1 የሾርባ ማንኪያ ውኃ
1 ብርጭቆ የተፈረፈረ ደረቅ ዳቦ
1 የቡና ስኒ ቅቤ
½ ኩባያ ዘይት
ጨው ፥ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ዡላሊቱን ለአንድ ሰዓት ያህል ጨው በገባበት ውኃ መዘፍዘፍ ።
2. ዡላሊቱን መላጥና አራት ቦታ መክፈል ።
3. እንቁላሉን ከአንድ የሾርባ ማንኪያ ውኃ ጋር መምታት ።
4. ዡላሊቱን እተመታው እንቁላል ውስጥ መጨመር ።
5. የተፈረፈረውን ዳቦ መውቀጥ ፤ ወይም መፍጨትና መንፋት ።
6. ዡላሊቱን የዳቦው ዱቄት ላይ ማንከባለል ።
7. ዘይትና ቁንዶ በርበሬ መጥበሻ ላይ ጨምሮ መጣድና የተሰናዳውን ዡላሊት መጥበስ ።
8. አጋም ሲመስል ማውጣት ።

498. የበግ ወይም የበሬ ምላስ ።

2 የበግ ምላስ—የበሬ አንድ
3 ቁንዶ በርበሬ ፥ ያልተፈጨ



6 ቀረፋ ፥ ያልተፈጨ
2 የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሾርባ ማንኪያ ኮምጣጤ

አሠራር

1. ምላሱን ፍም ላይ አስቀምጦ አምስት ደቂቃ ማቆየትና መላጥ ።
2. የተላጠውን ምላስ ንጹሕ ውኃ ላይ መጣድና እስኪበስል ድረስ መቀቀል ።
3. ቁንዶ በርበሬ ፥ ቀረፋ ፥ ጨውና ኮምጣጤ ጨምሮ ማንተክተክ ።
4. ሲበስል ማውጣት ።
5. በተፈለገው ፎርም ቈርጦና አሳምሮ ማቅረብ ።

499. ጣፋጭና ጐምዛዛ ምላስ ።

8 በስሱ የተቈረጠ ምላስ ፥ የተቀቀለ
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
2 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
¼ የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
1 ኩባያ የምላስ መረቅ
2 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
2 የሾርባ ማንኪያ ኮምጣጤ

አሠራር

1. ቅቤ ፥ ዱቄት ጨውና ቁንዶ በርበሬ በደንብ ማደባለቅ ።
2. መረቁን ጨምሮ እያማሰሉ እስኪወፍር ድረስ ማብሰል ።
3. ስኳር ፥ ኮምጣጤና ምላሱን ጨምሮ ሲፈላ ማውጣት ።

አራት ሰው ይመግባል ።

500. የጉበትና የቲማቲም ፓይ ።

¼ ኪሎ የበሬ ጉበት
2 ድንች ፥ ተቀቅሎ የተፈጨ
1 እንቁላል

## 510. ጉበት በክሬም ።

600 ግራም ጉበት
$1\frac{1}{2}$ ኩባያ ክሬም
$\frac{1}{8}$ ኩባያ ቅቤ
2 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
$1\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

### አሠራር

1. ጉበቱን በስሱ መቁረጥና እላዩ ላይ ያለውን ስስ ሽፋንና ሥራ ሥር ማላቀቅ ።
2. ቅቤ መጥበሻ ላይ አቅልጦ ጉበቱን አጋም እስኪመስል ድረስ እያገላበጡ መጥበስ ።
3. ጉበቱን አውጥቶ ዱቄት ፣ ጨውና ቁንዶ በርበሬ ከቀሪው ቅቤ ጋር ማደባለቅ ።
4. ክሬሙን ጨምሮ ለአንድ ደቂቃ ማብሰል ።
5. ጉበቱን መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ የክሬሙን ድብልቅ እላዩ ላይ መሸፈን ።
6. ሙቀቱ 300 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለአንድ ሰዓት ማብሰል።

ከአምስት እስከ ስድስት ሰው ይመገባል ።

## 511. የጉበት አሮስቶ ።

600 ግራም ጉበት
$\frac{1}{4}$ ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ቅቤ
3 ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ሚጥሚጣ
1 ኩባያ ክሬም
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ውኃ



### አሠራር

1. ዱቄቱን ጉበቱ ላይ መነስነስ ።
2. ጉበቱን በቅቤ አጋም እስኪመስል በመጥበሻ መጥበስ ።
3. ጉበቱን መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
4. በቀሪው ቅቤ ሽንኩርት ማቁላላት ።
5. ጨው ፣ ሚጥሚጣ ፣ ክሬምና ውኃ ጨምሮ ማዋሐድ ።
6. የክሬሙን ድብልቅ ጉበቱ ላይ ጨምሮ ሙቀቱ 300 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ክድኖ ለአንድ ሰዓት ተኩል ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመገባል ።

## 512. ጉበት በማካሮኒ ።

170 ግራም ማካሮኒ
600 ግራም ጉበት ፣ በስሱ የተቈረጠ
$\frac{1}{4}$ ኪሎ ፎርማጆ
4 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
$\frac{2}{4}$ ኩባያ ሰዶና ፣ የተከተፈ
1 ኩባያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
$1\frac{1}{2}$ ቃሪያ ፣ የተከተፈ
2 ኩባያ ቲማቲም ፣ የተከተፈ
የፉርኖ ዱቄት
ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬ

### አሠራር

1. ማካሮኒውን ጨው በገባበት ውኃ ቀቅሎ ማጠንፈፍ ።
2. ዱቄት ፣ ጨውና ቁንዶ በርበሬ አደባልቆ ጉበቱ ላይ መነስነስ ።
3. ጉበቱን በቅቤ አጋም እስኪመስል ድረስ እያገላበጡ መጥበስ ።
4. ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ የተጠበሰውን ጉበት ማኖር ።
5. ሰዴና ፣ ሽንኩርት ፣ ቃሪያና ቲማቲም አደባልቆ መጋገሪያ ላይ ያለውን ጉበት መሸፈን ።
6. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአንድ ሰዓት ማብሰል ። ፎርማጆውን ጨምሮ እስኪቀልጥ ድረስ ማቆየት ።
7. ከተቀቀለው ማካሮኒ ጋር ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመገባል ።

$\frac{8}{4}$ ኩባያ ክሬም
1 እንቍላል ፡ ዞፉ ብቻ
ትንሽ ቤኪንግ ሶዳ

### አሠራር

1. ሁለቱን ዓይነት ስኳር ፡ ቤኪንግ ሶዳና ክሬሙን አደባልቆ እሳት ላይ ጥዶ እያማሰሉ በደንብ እስኪዋሐድ ድረስ ማብሰል ።
2. ከእሳቱ ላይ አውጥቶ በመጠኑ እስኪቀዘቅዝ ድረስ ሳያማስሉ ማስቀመጥ ።
3. በመጠኑ የቀዘቀዘውን የክሬምና የስኳር ድብልቅ እስኪበስል ድረስ መምታት ።
4. የእንቍላሉን ዞፍ ጨምሮ እስኪወፍር ድረስ መምታት ።
5. የተዘጋጀውን ክሬም ኬኩ ላይ መቀባት ።

### 543. የቫኒላ ክሬም ፡ ቍጥር 1 ።

1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
$1\frac{1}{3}$ ኩባያ ስኳር
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ውኃ
2 የእንቍላል ዞፍ
$1\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ የበቆሎ እስታርች—ኮርን ስታርች
$\frac{1}{8}$ የሻይ ማንኪያ ጨው

### አሠራር

1. ከቫኒላው በስተቀር ከላይ የተጠቀሱትን በሙሉ ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ በኤሌክትሪክ የእንቍላል መምቻ በደንብ እስኪ ደባለቅ ድረስ መምታት ።
2. ድስቱን የፈላ ውኃ ላይ ጥዶ እያማሰሉ ከሰባት እስከ አሥር ደቂቃ በእንፋሎት ማብሰል ።
3. ከተጣደበት አውርዶ ቫኒላውን ጨምሮ ማዋሐድ ።
4. እስኪቀዘቅዝ ድረስ በእንቍላል መምቻ መምታት ።
5. ከቀዘቀዘ በኋላ ኬኩ ላይ መቀባት ።



### 544. የቫኒላ ክሬም ፡ ቍጥር 2 ።

1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
5 የሾርባ ማንኪያ ክሬም
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
3 ኩባያ ስኳር

### አሠራር

1. ቅቤ ፡ ቫኒላ ፡ ጨውና ግማሽ ኩባያ ስኳር አንድ ላይ ማደባለቅ ።
2. ክሬሙን ሞቅ አድርጎ ከቀሪው ስኳር ጋር በየተራ በመጠኑ መጨመር ። በደንብ ተዋሕዶ እስኪወፍር ድረስ መምታት ።
3. በደንብ ተደባልቆ ከበሰለ በኋላ ኬኩ ላይ መቀባት ።

### 545. የቸኮላት ክሬም ፡ ቍጥር 2 ።

3 የሾርባ ማንኪያ ቸኮላት
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
3 ኩባያ ስኳር
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ወፍራም ቡና

### አሠራር

1. ቅቤና ቫኒላውን አደባልቆ መምታት ።
2. ቸኮላትና ስኳሩን አደባልቆ መንፋት ።
3. ቸኮላቱንና ስኳሩን ከቡናው ጋር በየተራ በመጨመር ከቅቤና ከቫኒላው ጋር አደባልቆ መምታት ።
4. የተዘጋጀውን የቸኮላት ክሬም ኬክ ላይ ቀብቶ ማቅረብ ።

### 546. የአቾሎኒ ክሬም ፡ ቍጥር 1 ።

1 የሾርባ ማንኪያ አቾሎኒ ፡ ተፈልፍሎ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
1 የሾርባ ማንኪያ ማር
1 የሾርባ ማንኪያ ማርገሪን—ቅቤ

አሠራር

1. ስኳር ፣ ማርና ቅቤውን በብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ ከተደባለቀ በኋላ በመጠነኛ እሳት ላይ ጥዶ እያማሰሉ ማንተክተክ ።
2. ኦቾሎኒውን ጨምሮ ማዋሐድ ።
3. ኬክ ላይ ቀብቶ ማቅረብ ።

547. የስኳር ክሬም ።

1 ብርጭቆ ስኳር
2 የእንቁላል ዞፍ
½ ብርጭቆ ውኃ

አሠራር

1. ውኃውንና ስኳሩን ማፍላት ። ማማሰያው ብድግ ሲደረግ ስኳሩ እንደ ድር ሲያያዝ ማውጣት ።
2. የእንቁላሉ ዞፍ ውስጥ ስኳሩን ጠብ ጠብ እያደረጉ መምታት ።
3. የስኳር ክሬሙን የተሰናዳው ኬክ ላይ ቀብቶ ማቅረብ ።

548. የቅቤ ክሬም ።

1 የቡና ሲኒ ቅቤ ወይም ማርገሪን
2 ብርጭቆ የተፈጨ ስኳር
2 የእንቁላል አስኳል—ካልተፈለገ ሊቀር ይችላል
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ ወይም አንድ የሎሚ ልጣጭ ፍቅፋቂ
1 የሾርባ ማንኪያ ክሬም

አሠራር

1. ቅቤና ስኳሩን አረፋ እስኪወጣው ድረስ በደንብ ማሸት ።
2. የእንቁላሉን አስኳልና ቫኒላውን ጨምሮ ማሸት ።
3. ከወፈረ በኋላ በተሰናዳው ኬክ ላይ ክሬሙን ጨምሮ በደንብ መቀባት ።



549. የኮኮናት ክሬም ።

½ ኮኮናት
1 ኩባያ ቅቤ
1 ኩባያ ስኳር
2 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ ፣ ወይም አንድ የሎሚ ፍቅፋቂ

አሠራር

1. ቅቤውንና ስኳሩን አንድ ላይ አደባልቆ አረፋ እስኪወጣው ድረስ ማሸት ።
2. ቫኒላውን ጨምሮ በደንብ አደባልቆ ኮኮናቱን ጨምሮ ማሸት ።
3. የተሰናዳው ኬክ ላይ ቀብቶ ማቅረብ ።

550. የኦቾሎኒ ክሬም ፣ ቁጥር 2 ።

2 ኩባያ የተከተፈ ኦቾሎኒ
2 እንቁላል
1 ኩባያ ቡናማ ስኳር—ብራውን ሹገር
1 ኩባያ ውኃ
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ ወይም የሎሚ ልጣጭ ፍቅፋቂ ትንሽ ጨው

አሠራር

1. የእንቁላሉን አስኳል ከዞፉ መለየት ።
2. የእንቁላሉ ዞፍ ውስጥ ስኳር ፣ ጨውና ውኃ ጨምሮ በእንቁላል መምቻ ወይም በሹካ ደህና አድርጎ መምታት ።
3. ከፈላ ውኃ ላይ ጥዶ ለሰባት ደቂቃ ያህል መምታት ።
4. ከውኃው ላይ ማውጣትና ቫኒላውን ጨምሮ በእንጨት ማንኪያ ማሸት ።
5. የተከተፈውን ኦቾሎኒ ጨምሮ ማደባለቅ ።
6. የተሰናዳው ኬክ ላይ ቀብቶ ማቅረብ ።

551. የቫኒላ ክሬም ፣ ቁጥር 3 ።

2 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
4 የእንቁላል ዞፍ

3. የተዘጋጀውን ሊጥ ቅባት የተቀባ የኬክ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለሠላሳ ደቂቃ ማብሰል ።

565. የእንቍላል ኬክ ።

2 ኩባያ የኬክ ዱቄት ፣ የተነፋ
1 እንቍላል
2½ የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
¼ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
1 ኩባያ ስኳር
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
¾ ኩባያ ወተት

አሠራር

1. ዱቄት ፣ ቤኪንግ ፓውደርና ጨው እደባልቆ መንፋት ።
2. ቅቤውንና ስኳሩን በእንቍላል መምቻ እስኪለሰልስ ድረስ መምታት ።
3. እንቍላልና ቫኒላውን ከቅቤና ከስኳሩ ጋር ማደባለቅ ።
4. የተነፋውን ዱቄትና ወተት በመጠኑ በየተራ እየጨመሩ ከእንቍላልና ከቅቤ ድብልቅ ጋር ማዋሐድ ።
5. የተዘጋጀውን ሊጥ ቅባት የተቀባ የኬክ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ከሠላሳ እስከ ሠላሳ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

566. የስኳር ድንች ኬክ ።

1 ኩባያ ስኳር ድንች ፣ ተቀቅሎ የተፈጨ
1½ ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
2½ የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
⅓ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
2 እንቍላል ፣ በደንብ የተመታ
2¾ ኩባያ ስኳር
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሻይ ማንኪያ ቀረፋ ወይም ገውዝ
½ ኩባያ ወተት
2 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ



አሠራር

1. ዱቄትና ቤኪንግ ፓውደሩን አደባልቆ መንፋት ።
2. ቅቤና የተመታውን እንቍላል ከተፈጨው ትኩስ ስኳር ድንች ጋር ማደባለቅ ።
3. ስኳር ፣ ጨውና ቀረፋ ጨምሮ በደንብ መምታት ።
4. የተነፋውን ዱቄትና ወተት በየተራ በመጠኑ እየጨመሩ እስኪዋሐድ መምታት ።
5. የሎሚ ጭማቂ ጨምሮ ማደባለቅ ።
6. የተዘጋጀውን ሊጥ ቅባት የተቀባ የኬክ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ገልብጦ ሙቀቱ 325 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ከስድሳ እስከ ስድሳ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

567. ፕሌይን ኬክ ።

3 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
4 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 ኩባያ ስኳር
½ የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
1 የተመታ እንቍላል
1 ኩባያ ወተት
¼ ኩባያ የቀለጠ ማርገሪን

አሠራር

1. የፉርኖ ዱቄት ፣ ቤኪንግ ፓውደር ፣ ጨው ፣ ስኳር ፣ ቫኒላ አንድ ላይ ማቀላቀል ።
2. የተመታ እንቍላል ፣ ወተት ፣ ማርገሪን አንድ ላይ አደባልቆ በቍጥር 1 ከተጠቀሰው ቅልቅል ጋር ማዋሐድ ።
3. ቅባት በተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ገልብጦ ሙቀቱ 375 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ለሃያ ደቂቃ ማብሰል ።

3. እንቁላሉን ከወተትና ከስንዴ ገለባ ድብልቁ ጋር ቀላቅሎ በተራ ቁጥር 2 የተዘጋጀውን የዱቄት ድብልቅ ጨምሮ ማዋሐድ ።
4. የቀለጠውን ቅቤ ከሊጡ ጋር ማደባለቅ ።
5. የተዘጋጀውን ሊጥ በማንኪያ እያወጡ ዘይት የተቀባ ምጣድ ወይም በመጥበሻ ላይ ማብሰል ።
6. የበሰለውን ፓንኬክ ከቅቤና ከማርማላት ጋር ትኩሱን ማቅረብ ።

ሃያ አራት ፓንኬክ ይወጣዋል ።

## 592. መፊን ።

2 ኩባያ የፋርኖ ዱቄት ፥ የተነፋ
4 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ስኳር
1 እንቁላል ፥ የተመታ
1 ኩባያ ወተት
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ—የቀለጠ

### አሠራር

1. ዱቄት ፥ ቤኪንግ ፓውደር ፥ ጨውና ስኳር አደባልቆ መንፋት ።
2. እንቁላል ፥ ቅቤና ወተቱን አደባልቆ በደንብ መምታት ።
3. በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተዘጋጀውን ማደባለቅ ።
4. የተዘጋጀውን ሊጥ ቅባት የተቀባ የመፊን መጋገሪያ ዕቃ ላይ በጣም ሳይሞላ ማድረግ ።
5. ሙቀቱ 400 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለሃያ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

ከአሥራ ሁለት እስከ አሥራ አምስት መፊን ይወጣዋል ።

## 593. የሙዝ መፊን ።

1 ኩባያ የፋርኖ ዱቄት ፥ የተነፋ
1 ኩባያ የስንዴ ገለባ
2 ኩባያ በስሱ የተቈራረጠ ሙዝ
$\frac{3}{4}$ የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ሶዳ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው



2 የሾርባ ማንኪያ ማርገሪን—ቅቤ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ስኳር
1 እንቁላል ፥ የተመታ
2 የሾርባ ማንኪያ እርጎ

### አሠራር

1. ዱቄት ፥ ቤኪንግ ሶዳና ጨው አደባልቆ መንፋት ።
2. ቅቤና ስኳሩን አደባልቆ እስኪለሰልስ ድረስ መምታት ። እንቁላል ፥ እርጎና ሙዙን ጨምሮ ማዋሐድ ።
3. የስንዴውን ገለባ በተራ ቁጥር 2 ከተዘጋጀው ድብልቅ ጋር ቀላቅሎ እስኪርስ ድረስ አቆይቶ የተነፋውን የዱቄት ድብልቅ ጨምሮ መምታት ።
4. የተዘጋጀውን ሊጥ ቅባት የተቀባ የመፊን መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ሙቀቱ 375 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለሠላሳ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

ስድስት መፊን ይወጣዋል ።

## 594. የቀረፋ መፊን ።

2 ኩባያ የፋርኖ ዱቄት
3 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሻይ ማንኪያ ቀረፋ
$\frac{2}{3}$ ኩባያ ስኳር
1 እንቁላል
1 ኩባያ ወተት
2 የሾርባ ማንኪያ ማርገሪን—ቅቤ—የቀለጠ

### አሠራር

1. የመፊን መጋገሪያ ዕቃውን (ኩባያ) ቅባት መቀባት ። በእያንዳንዱ ኩባያ ውስጥ ግማሽ የሻይ ማንኪያ ቅቤ ፥ አንድ የሻይ ማንኪያ ስኳር መጨመር ።
2. ዱቄት ፥ ቤኪንግ ፓውደር ፥ ጨውና ቀረፋ አደባልቆ መንፋት ።

3. እንቍላል ፡ ወተት ፡ ቀሪውን ቅቤና ስኳር አደባልቆ በተራ ቍጥር 2 ከተዘጋጀው የዱቄት ድብልቅ ጋር ማዋሐድ ።
4. የተዘጋጀውን ሊጥ ቅቤና ስኳር ያለበት የመፊን መጋገሪያ ኩባያ ውስጥ ጨምሮ ሙቀቱ 250 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለሃያ ደቂቃ ማብሰል ።

እሥራ ስምንት የቀረፉ መፊን ይወጣዋል ።

595. የማር መፊን ።

2 ኩባያ የፋርኖ ዱቄት ፡ የተነፋ
½ ኩባያ ማር
3 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
½ የሻይ ማንኪያ ገውዝ
½ ኩባያ ዘቢብ
2 ኩባያ የስንዴ ገለባ
1 እንቍላል ፡ የተመታ
¼ ኩባያ ስኳር
1¼ ኩባያ ወተት
¼ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ—የቀለጠ

እሠራር

1. ዱቄት ፡ ቤኪንግ ፓውደር ፡ ጨውና ገውዝ አደባልቆ መንፋት ።
2. እንቍላሉን ለብቻው መምታት ።
3. የተመታውን እንቍላል ፡ ከማር ፡ ከስኳር ፡ ከወተትና ከቅቤ ጋር ቀላቅሎ ከዱቄቱ ድብልቅ ጋር ማዋሐድና የስንዴውን ገለባ ጨምሮ እስኪርስ ድረስ ትንሽ አቆይቶ ዘቢብ ጨምሮ ማዋሐድ ።
4. ሊጡን ቅባት የተቀባ የመፊን መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
5. ሙቀቱ 425 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለሃያ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

ከአሥራ ስድስት እስከ አሥራ ስምንት የማር መፊን ይወጣዋል ።

596. የእንግሊዝ መፊን ።

4 ኩባያ የፋርኖ ዱቄት
2 የሻይ ማንኪያ እርሾ—ይስት
1 እንቍላል ፡ የተመታ



3 የሾርባ ማንኪያ ማርገሪን—ቅቤ
1¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
2 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
1 ኩባያ ወተት ፡ የሞቀ
¼ ኩባያ ውኃ

እሠራር

1. ቅቤ ፡ ጨውና ፡ ስኳር ከወተት ጋር ማደባለቅ ።
2. እርሾው ውስጥ ውኃ ጨምሮ ማሟሟት ።
3. የሟሟውን እርሾ ፡ እንቍላልና ሁለት ኩባያ ዱቄት በተራ ቍጥር 1 ከተዘጋጀው የወተት ድብልቅ ጋር አዋሕዶ ቀሪውን ዱቄት ጨምሮ ማቡካት ።
4. የተዘጋጀውን ሊጥ እንዲቦካ ሸፍኖ ለአንድ ሰዓት ያህል ማቆየት ።
5. የቦካውን ሊጥ ትንሽ ዱቄት በተነሰነሰበት ጣውላ ላይ በስሱ ዳምጦ አሥራ ሁለት ቦታ ቈርጦ በድጋሚ ኩፍ እንዲል ለአንድ ሰዓት ማቆየት ።
6. የተቈረጠውን ሊጥ ባልተቀባ ምጣድ ወይም በወፍራሙ መጥበሻ ላይ አጋም እስኪመስል ድረስ እያገላበጡ መጥበስ ።
አሥራ ሁለት መፊን ይወጣዋል ።

597. ቾኮላት ኬክ ።

3 ኩባያ የፋርኖ ዱቄት
¾ ኩባያ ካካዎ
1 ኩባያ ማርገሪን
1 ኩባያ ስኳር
6 እንቍላል
3½ የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
1½ ኩባያ አልሞንድ—ናት—የተፈጨ
1 ኩባያ ወተት
3 የሻይ ማንኪያ ራም—ቸሪ ብራንዲ

እሠራር

1. ማርገሪን ፡ ስኳር አንድ ላይ አደባልቆ በደንብ ኩፍ እስኪል ድረስ መምታት ።

2. የእንቍላሉን አስኳልና ዞፍ መለየት ።
3. የእንቍላሉን አስኳል ከማርገሪንና ከስኳር ጋር ቀላቅሎ መምታት ።
4. የፉርኖ ዱቄትና ቤኪንግ ፓውደሩን ቀላቅሎ ከማርገሪንና ከስኳሩ ድብልቅ ጋር አዋሕዶ ከእንቍላል አስኳሉ ጥቂት በጥቂት እየጨመሩ ማማሰል ፤ አልሞንድና (ናት) ወተት ጨምሮ በደንብ እስኪለሰልስ ድረስ ማዋሐድ ።
5. ሊጡን ከሁለት ላይ ከፍሎ አንዱ ክፍል ውስጥ የራም ወይም ቸሪ ብራንዲ መጨመር ። ሁለተኛው ክፍል ውስጥ ካካዎ ጨምሮ እንደገና እላዩ ላይ ወተት እያንጠባጠቡ ማማሰል ።
6. የእንቍላሉን ዞፍ ለብቻው መትቶ ለሁለት ከተከፈለው ሊጥ ጋር ማዋሐድ ።
7. ራም ወይም ቸሪ ብራንዲ ከገባበትና ካካዎ ከተጨመረበት ሊጥ አንድ አንድ የሾርባ ማንኪያ እየጨለፉ ሁለቱም ክፍል እስኪ ያልቅ ድረስ ቅባት በተቀባ ድስት ውስጥ መጨመር ። ከዚያም ሙቀት ከ325—350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ አንድ ሰዓት ከሩብ ማብሰል ።

ከስምንት እስከ አሥር ሰው ይመግባል ።

## 598. የበቆሎ ዱቄት ኬክ ።

8 የሾርባ ማንኪያ የበቆሎ ዱቄት
1 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
4 እንቍላል ፣ የተለያየ
8 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
1 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
3 ጠብታ ቫኒላ ፈሳሽ
የሚነስነስ ስኳር ፣ የተፈጨ

### አሠራር

1. በጐድጓዳ ሣሀን ውስጥ የእንቍላል አስኳል ፣ ስኳር ፣ የሎሚ ጭማቂ በአንድ ላይ ደባልቆ መምታት ።
2. የእንቍላሉን ዞፍ አረፋ እስኪወጣው ድረስ መምታት ።
3. ቫኒላ ከአስኳሉ ጋር ማደባለቅ ።
4. የበቆሎ ዱቄትና ቤኪንግ ፓውደር አንድ ላይ ደባልቆ ትንሽ በትንሽ እስቲያልቅ ድረስ ከእንቍላል ቅልቅልና ከዞፉ ጋር እየቀላቀሉ ማማሰል ።
5. መጋገሪያውን ዕቃ ቅባት ቀብቶ ሊጡን እላዩ ላይ መገልበጥ ።



6. ሙቀቱ 375 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለሃያ ደቂቃ ወይም ለአርባ ደቂቃ አብስሎ ማውጣት ። እላዩ ላይ ስኳር ነስንሶ ትኩሱን ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 599. የእንጆሪ ኬክ ።

2 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት ፣ የተነፋ
$1\frac{1}{2}$ ኩባያ እንጆሪ ፣ የታጠበ
3 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት ፣ የተነፋ
2 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
6 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
$\frac{3}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ማርገሪን
1 እንቍላል ፣ የተመታ
$\frac{1}{8}$ ኩባያ ወተት
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ስኳር

### አሠራር

1. ሁለት ኩባያ ዱቄት ፣ ቤኪንግ ፓውደር ፣ ስድስት የሾርባ ማንኪያ ስኳር ፣ ጨውና ማርገሪን አንድ ላይ ማደባለቅ ።
2. እንቍላልና ወተቱን በተራ ቍጥር 1 ከተዘጋጀው የዱቄትና የማርገሪን ድብልቅ ጋር በደንብ ማዋሐድ ።
3. ቅባት የተቀባ የኬክ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ እላዩ ላይ እንጆሪውን በሚያምር ሁኔታ ማስቀመጥ ።
4. ቅቤ ፣ ሩብ ኩባያ ስኳርና ሦስት የሾርባ ማንኪያ ዱቄት አደባልቆ እንጆሪው ላይ መነስነስ ።
5. የተዘጋጀውን ኬክ ሙቀቱ 400 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ከሃያ አምስት እስከ ሠላሳ ደቂቃ ማብሰል ።

## 600. የብርቱካን ኬክ ።

2 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
1 ትልቅ ብርቱካን
1 ኩባያ ወይን ፣ ፍሬ የሌለው
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ማርገሪን

$1\frac{1}{2}$ ኩባያ ስኳር
2 የተመታ እንቁላል
$\frac{1}{4}$ ማንኪያ ጨው
1 የሻይ ማንኪያ ሶዳ—ባይካርቦኔት
1 ኩባያ እርጎ

## አሠራር

1. ብርቱካኑን ሁለት ቦታ ከፍሎ መጭመቅ ፤ ቅርፊቱንና የውስጥ ሥጋውን መለየት ።
2. የውስጥ ሥጋውንና ቅርፊቱን አድቅቆ መምተር ። የተጨመቀውን ወይን መቀላቀል ።
3. የብርቱካኑ ጭማቂ ውስጥ ግማሽ ኩባያ ስኳር ጨምሮ እስኪሟሟ ድረስ ማቆየት ።
4. ማርገሪኑንና የተረፈውን ስኳር አንድ ላይ ደባልቆ መትቶ እንቁላል መጨመር ።
5. የፉርኖ ዱቄት ፥ ጨው ፥ እርጎ ፥ ሶዳ አንድ ላይ አድርጎ የተመታው ማርገሪንና ስኳር ውስጥ ጨምሮ ማማሰል ።
6. ብርቱካኑንና ወይኑን መጨመር ።
7. ሁሉንም አንድ ላይ በደንብ ለውሶ ማርገሪን በተቀባ መጋገሪያ ላይ ገልብጦ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአርባ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።
8. በስሎ ከወጣ በኋላ በትኩሱ እንዳለ የብርቱካኑን ጭማቂና ስኳር እላዩ ላይ መቀባት ። የብርቱካኑ ጭማቂ ኬኩ ውስጥ ሰርጎ ከገባና ከቀዘቀዘ በኋላ ማቅረብ ።

## 601. የማርገሪን ኬክ ።

3 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
1 ኩባያ ቅቤ—ማርገሪን
$2\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
4 እንቁላል
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ ወይም የሎሚ ልጣጭ ፍቅፋቂ
2 ኩባያ የተፈጨ ስኳር
$\frac{1}{4}$ ወይም $\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 ኩባያ ወተት



## አሠራር

1. ቅቤው ኩፍ እስቲል ድረስ መምታት ። ቫኒላና የተፈጨ ስኳር ጨምሮ መምታት ።
2. የእንቁላሉን አስኳል አንድ በአንድ እየጨመሩ በደንብ ኩፍ እስኪል ድረስ መምታት ።
3. የፉርኖ ዱቄት ፥ ጨው ፥ እርሾ አንድ ላይ ማደባለቅ ።
4. አንድ ጊዜ ከፉርኖ ዱቄቱ አንድ ጊዜ ከወተቱ እየጨመሩ ማማሰል ።
5. የእንቁላሉን ዞፍ ለብቻው መትቶ መጨመር ።
6. ቅባት በተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ገልብጦ ሙቀቱ 365 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ማብሰል ።

## 602. የእንቁላል ኬክ ፥ ቁጥር 2 ።

5 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
$2\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ እርሾ (ይስት)
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ውኃ ፥ ለብ ያለ
$\frac{1}{4}$ ማርገሪን ቅቤ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ስኳር
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
2 እንቁላል ፥ የተመታ
1 ኩባያ ወተት ፥ ሞቅ ያለ
1 የሻይ ማንኪያ የሎሚ ልጣጭ ፍቅፋቂ
1 የእንቁላል አስኳል
2 የሾርባ ማንኪያ የተፈጨ ስኳር

## አሠራር

1. እርሾውን ለብ ያለ ውኃ ውስጥ ጨምሮ ከአምስት እስከ አሥር ደቂቃ ድረስ ኩፍ እንዲል ማቆየት ።
2. ቅቤ ፥ ግማሽ ኩባያ ስኳርና ጨው ከወተት ጋር አደባልቆ ኩፍ ካለው እርሾ ጋር ማዋሐድ ።
3. ሁለት እንቁላል ፥ የሎሚ ልጣጭና ዱቄት በተራ ቁጥር 2 ከተዘጋጀው ድብልቅ ጋር ቀላቅሎ ማቡካት ።
4. የተቦካውን ሊጥ ትንሽ ዱቄት የተነሰነሰበት ጣውላ ላይ አድርጎ በደንብ ማሸት ።
5. የታሸውን ሊጥ በዘይት የተቀባ ጐድጓዳ ሣህን ውስጥ ጨምሮ ከድኖ ኩፍ እስኪል ድረስ ማስቀመጥ ።
6. ኩፍ ያለውን ሊጥ በመጠኑ አሽቶ ሁለት እኩል ቦታ ላይ መክፈል ።
7. ቀሪውን ግማሽ ሊጥ ሁለት የተቀባ የኬክ መጋገሪያ ዕቃ ውስጥ

4. የተዘጋጀውን ሊጥ ቅባት የተቀባ የኬክ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ጨምሮ አናናሱን በሚያምር መልክ እላዩ ላይ መደርደር ።
5. ስኳር ፣ ዱቄትና ሦስት የሾርባ ማንኪያ ቅቤውን አደባልቆ በሹካ በደንብ መትቶ አናናሱ ላይ መጨመር ።
6. ሙቀቱ 400 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ከሃያ አምስት እስከ ሠላሳ ደቂቃ ማብሰል ።

አንድ ኬክ ይወጣዋል ።

606. አፕል ኬክ ።

6 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
6 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
9 ወይም አሥር ፖም
2 ሎሚ ልጣጭ ፍቅፋቂ
4 እንቁላል
1½ ኩባያ የቀለጠ ማርማላት
2 ሎሚ ጭማቂ
½ ኩባያ የተፈጨ ስኳር
1 ኩባያ ማርገሪን
ትንሽ ወተት

አሠራር

1. ማርገሪን ፣ ስኳር የሎሚ ልጣጭ ፍቅፋቂና የሎሚ ጭማቂ አንድ ላይ አደባልቆ በጣም ኩፍ እስኪል መምታት ።
2. እንቁላሉን ጨምሮ በመጠኑ መምታት ።
3. የፉርኖ ዱቄትና ቤኪንግ ፓውደሩን አንድ ላይ ቀይጦ በተራ ቁጥር 2 ከተጠቀሰው ድብልቅ ጋር አቀላቅሎ አንድ ጊዜ ከፉርኖ ዱቄቱ አንድ ጊዜ ደግሞ ከወተቱ እየጨመሩ ማዋሐድ ።
4. ቅባት በተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ገልብጦ ፖሙን—አፕል—ልጦ በቁመት ቈርጦ ከሊጡ ላይ መሰካት ። በእጅ እየተጫኑ ስኳር ነስንሶ ሙቀቱ 375 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለሠላሳ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።
5. አጋም ሲመስል ማርማላት ቀብቶ ለትንሽ ደቂቃዎች በምድጃ ውስጥ አቆይቶ ማውጣት ።



607. የስኳር ኬክ ።

3 ኩባያ የኬክ ዱቄት ፣ የተነፋ
3 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
2 ኩባያ ስኳር
2 ኩባያ የፈላ ውኃ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
4 እንቁላል ፣ ዞፉና አስኳሉ የተለየ
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ

አሠራር

1. አንድ ኩባያ ስኳር ለክቶ በመጥበሻ ላይ ማቅለጥ ። አጋም እስኪመስል ድረስ እያማሰሉ እሳቱ ላይ ማቆየት ።
2. ስኳሩን ከእሳቱ ላይ አውጥቶ የፈላውን ውኃ ጨምሮ እያማሰሉ ስኳሩን ማሟሟት ።
3. ዱቄት ፣ ቤኪንግ ፓውደር ፣ ጨው አደባልቆ መምታት ።
4. ቅቤውንና ቀሪውን አንድ ኩባያ ስኳር አደባልቆ መምታት ።
5. የእንቁላሉን አስኳል ከቅቤውና ከስኳሩ ጋር በየተራ እየጨመሩ መምታት ። ቫኒላውን ጨምሮ ማደባለቅ ።
6. የቀለጠውን ስኳርና ዱቄቱን በየተራ በመጨመር ከእንቁላሉና ከቅቤው ድብልቅ ጋር ጨምሮ መምታት ።
7. የእንቁላሉን ዞፍ እስኪወፍር ድረስ መትቶ ከተዘጋጀው ሊጥ ጋር አዋሕዶ የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
8. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ከሠላሳ እስከ ሠላሳ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

608. የአቿሎኒ ኬክ ።

4 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት ፣ የተነፋ
½ አቿሎኒ ፣ ተፈልፍሎ የተከረተፈ
1½ ማርገሪን—ቅቤ
¼ ኩባያ ስኳር
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው
4 እንቁላል ፣ አስኳል
1 የሻይ ማንኪያ የሎሚ ልጣጭ ፣ የተከተፈ
1 የእንቁላል ዞፍ

½ የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
3 የሻይ ማንኪያ አሞኒያ ፓውደር — ከፋርማሲ የሚገኝ
1 የሻይ ማንኪያ ባይካርቦኔት
½ ሊትር ወተት
2 መለኪያ ኮኛክ

እሠራር

1. ስኳሩንና ማርገሪኑን አንድ ላይ መትቶ እንላቍል ጨምሮ ኩፍ እስኪል ድረስ መምታት ።
2. የፋርኖ ዱቄት ፡ ቤኪንግ ፓውደርና ቫኒላ አንድ ላይ ማደባለቅ ።
3. አሞኒያና ባይካርቦኔት በሦስት የሾርባ ማንኪያ ወተት መበጥበጥ ።
4. ከማርገሪን ጋር የተመታ እንቍላል ጨምሮ የፋርኖ ዱቄቱ በትንሽ በትንሹ እየጨመሩ ማቡካት ። ቀጥሎ ወተትና ኮኛክ ጨምሮ ማቡካት ።
5. ዱቄት በተነሰነሰበት ጠረጴዛ ላይ አድርጎ በድቡልቡል እንጨት ዳምጦ በብስኩት መቍረጫ መቍረጥ ።
6. ቅባት በተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ምድጃ ውስጥ አጋም እስኪመስል ድረስ ማብሰል ።

635. ደረቅ ብስኩት ፡ ቍጥር 2 ።

½ ኪሎ የፋርኖ ዱቄት
1 ኩባያ ማርገሪን
1¼ ኩባያ ስኳር
2 ወይም 3 እንቍላል
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ ወይም የአንድ ሎሚ ልጣጭ ፍቅፋቂ
1 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሻይ ማንኪያ የተፈጨ ቀረፋ

እሠራር

1. ማርገሪን ኩፍ እስኪል ድረስ መምታት ።
2. ስኳር ጨምሮ በደንብ ማሸት ።
3. እንቍላልና ቫኒላ ጨምሮ ማማሰል ።
4. የፋርኖ ዱቄት ፡ ቀረፋ ፡ ቤኪንግ ፓውደርና ጨው አንድ ላይ ደባልቆ ከእንቍላልና ከቅቤ ቅልቅሉ በትንሽ በትንሹ እየጨመሩ ማቡካት ።



5. ዱቄት በተነሰነሰበት ጠረጴዛ ላይ በስሱ ዳምጦ ፡ በብስኩት መቍረጫ ቈርጦ ፡ ቅባት በተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ የእንቍላሉን አስኳል ቀብቶ ለአሥር ደቂቃ ምድጃ ውስጥ ማብሰል ።

636. ቢራቢሮ ብስኩት ።

4 እንቍላል
3 ኩባያ የፋርኖ ዱቄት
2 የሾርባ ማንኪያ የተፈጨ ስኳር
2 የሾርባ ማንኪያ ቀረንፋድ
ዘይት ፡ ለመጥበሻ

እሠራር

1. እንቍላሉን መትቶ ትንሽ ትንሽ የፋርኖ ዱቄት እየጨመሩ ሊጡ ጠንከር እስኪል ማቡካት ።
2. ጠረጴዛ ላይ በስሱ ዳምጦ መዘርጋት ።
3. በቢላዋ እየቈረጡ የፋልፋሊና ቅርጽ በማውጣት በትኩስ ዘይት ላይ አጋም እስኪመስል እየጠበሱ ወረቀት ላይ ማውጣት ።
4. የተጠበሰውን ብስኩት ሣህን ሥር ማንጠፍ ። ቀጥሎ ስኳርና ቀረንፋድ መነስነስ ፤ እንደገና እላዩ ላይ ብስኩት ደርቦ ስኳርና ቀረንፋድ እየነሰነሱ ማዘጋጀት ።

637. ብስኩት በማር ።

2½ ኩባያ ፋርኖ ዱቄት
1 ኩባያ ማር
62 ግራም ቅቤ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
2 እንቍላል
½ ኩባያ ወተት
½ ኩባያ ስኳር
3 ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር

### አሠራር

1. የፋርኖ ዱቄት ፣ ቤኪንግ ፓውደር አንድ ላይ ማደባለቅ ።
2. ቅቤውን በጐድጓዳ ሣህን ውስጥ ጨምሮ ለብቻው መምታት ። እንቁላሉን ጨምሮ በኃይል መትቶ ስኳር አስገብቶ እስኪሟሟ ድረስ መምታት ። ወተት ጨምሮ አማስሎ የፋርኖ ዱቄት ጨምሮ በደንብ ማሸት ።
3. ከታሸ በኋላ ጠረጴዛ ላይ በስሱ ዳምጦ በአራት ማዕዘን መቍረጥ። በማንኪያ ክብ አድርጎ አዘጋጅቶ ምድጃ ውስጥ ማስገባት ። ከበሰለ በኋላ አውጥቶ ማር እላዩ ላይ መቀባት ።
4. ካስፈለገ ስኳር ፈጭቶ እላዩ ላይ መነስነስ ።

### 638. ዶናት ።

4 ኩባያ የፋርኖ ዱቄት ፣ የተነፋ
1 ኩባያ ስኳር
2 የሾርባ ማንኪያ ማርጋሪን—ቅቤ—የቀለጠ
2 እንቁላል
4 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቀረፋ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ገውዝ
1 ኩባያ ወተት
ዘይት ፣ ለመጥበሻ

### አሠራር

1. የእንቁላሉ ዞፍ ለብቻ ከተመታ በኋላ እስኳሉን በመጠኑ በመጨመር እስኪዋሐድ ድረስ መምታት ። የቀለጠውን ቅቤ ጨምሮ ማደባለቅ ።
2. ዱቄት ፣ ቤኪንግ ፓውደር ፣ ጨው ፣ ቀረፋና ገውዝ አደባልቆ መንፋት ።
3. የተነፋውን የዱቄት ድብልቅና ወተት በመጠኑ በየተራ በመጨመር በተራ ቍጥር 1 ከተዘጋጀው ድብልቅ ጋር አዋሕዶ ማቡካት ።
4. ሊጡን ትንሽ ዱቄት በተነሰነሰበት ጣውላ ላይ በስሱ ዳምጦ በዶናት መቍረጫ ቈርጦ በመጥበሻ ላይ በፈላ ዘይት ውስጥ እያገላበጡ በመጠኑ አጋም እስኪመስል ድረስ መጥበስ ።



5. የተጠበሰውን ዶናት ወረቀት ላይ አኑሮ ዘይቱን እንዲመጥ ማድረግ ።
6. ዶናቱን የቸኮላት ፍሮስቲንግ ቀብቶ ማቅረብ ።

ሃያ አራት ዶናት ይወጣዋል ።

### 639. ተቦክቶ የተጋገረ ዶናት ።

5 ኩባያ የፋርኖ ዱቄት ፣ የተነፋ
$1\frac{1}{4}$ ኩባያ ወተት ፣ የሞቀ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ማርጋሪን—ቅቤ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
2 የሻይ ማንኪያ እርሾ—ይስት
3 እንቁላል
$\frac{3}{4}$ ኩባያ ስኳር
$1\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቀረፋ
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ገውዝ
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ
ዘይት ፣ ለመጥበሻ

### አሠራር

1. ቅቤና ጨውን ከወተቱ ጋር ማደባለቅ ።
2. እርሾውን በተራ ቍጥር 1 ከተዘጋጀው የወተት ድብልቅ ውስጥ ጨምሮ ለአምስት ደቂቃ ሸፍኖ ማቆየት ።
3. ሁለት ኩባያ ተኩል ዱቄት ከእርሾው ድብልቅ ጋር ተዋሕዶ ከተመታ በኋላ ኩፍ እስኪል ድረስ ሸፍኖ ማቆየት ።
4. እንቁላል ፣ ስኳር ፣ ቀረፋ ፣ ገውዝና ቁንዶ በርበሬ ኩፍ ካለው ሊጥ ጋር ማደባለቅ ።
5. ቀሪውን ዱቄት ጨምሮ በደንብ አቡክቶ ኩፍ እስኪል ድረስ ሸፍኖ ማቆየት ።
6. ኩፍ ያለውን ሊጥ ትንሽ ዱቄት የተነሰነሰበት ጣውላ ላይ በስሱ ዳምጦ በዶናት መቍረጫ መቍረጥ ።
7. የተቈረጠውን ሊጥ፣ በመጥበሻው ላይ በፈላ ዘይት ውስጥ እያገላበጡ በመጠኑ አጋም እስኪመስል ድረስ መጥበስ ።
8. የተጠበሰውን ዶናት ወረቀት ላይ አኑሮ ዘይቱን እንዲመጥ ማድረግ ።

ሠላሳ ስድስት ዶናት ይወጣዋል ።

640. ፍሬንች ዶናት ።

$7\frac{1}{2}$ ኩባያ የፉርኖ ዱቄት ፣ የተነፋ
1 ኩባያ ውኃ ፣ የፈላ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ስኳር
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
3 የሻይ ማንኪያ እርሾ—ይስት
1 ኩባያ ወተት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ውኃ ፣ ለብ ያለ
2 እንቁላል ፣ የተመታ
ዘይት ፣ ለመጥበሻ

### አሠራር

1. ቅቤ ፣ ስኳርና ጨው ከግማሽ ኩባያ የፈላ ውኃ ጋር ማደባለቅ ፤ ወተቱን ጨምሮ ማብረድ ።
2. እርሾውን ግማሽ ኩባያ ውኃ ውስጥ ጨምሮ ማሟሟት ።
3. የሟሟውን እርሾ በተራ ቁጥር 1 ከተዘጋጀው ድብልቅ ጋር ቀይጦ ከተመታው እንቁላልና በአራት ኩባያ ዱቄት ጋር ማዋሐድ።
4. ቀሪውን ዱቄት ጨምሮ ማቡካት ።
5. ሊጡን ቅባት የተቀባ ጐድጓዳ ሣህን ውስጥ ጨምሮ ከድኖ በረዶ ቤት ውስጥ አስገብቶ ማቀዝቀዝ ።
6. የቀዘቀዘውን ሊጥ ትንሽ ዱቄት በተነሰነሰበት ጣውላ ላይ በስሱ ዳምጦ በብስኩት ቅርጽ ማውጫ መቁረጥ ።
7. የተቈረጠውን ሊጥ በመጥበሻ ላይ በፈላ ዘይት ውስጥ በመጠኑ አጋም እስኪመስል ድረስ መጥበስ ።
8. የተጠበሰውን ዶናት ወረቀት ላይ አኑሮ ዘይቱን እንዲመጥ ማድረግ ።

ስድሳ ዶናት ይወጣዋል ።

## ኩኪስ

641. ፋውንዴሽን ድሮፕ ኩኪስ ።
2 ኩባያ የኬክ ዱቄት
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
$\frac{3}{4}$ ኩባያ ስኳር



1 እንቁላል ፣ የተመታ
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ወተት
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ

### አሠራር

1. ስኳር በመጠኑ ቅቤው ውስጥ ጨምሮ በእንቁላል መምቻ ወይም በሹካ በመጫን እስኪለሰልስ ድረስ ማደባለቅ ።
2. እንቁላሉን ጨምሮ ማዋሐድ ።
3. ዱቄት ፣ ጨውና ቤኪንግ ፓውደር አደባልቆ መንፋት ።
4. ዱቄቱን ቫኒላና ወተቱን በየተራ በመጨመር ከእንቁላልና ከቅቤው ድብልቅ ጋር በደንብ እየመቱ ማዋሐድ ።
5. ሊጡን በማንኪያ እየቆነጠሩ የተቀባ የኩኪስ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
6. ሙቀቱ 375 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ከአሥር እስከ አሥራ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

ሃምሳ ኩኪስ ይወጣዋል ።

642. የቸኮላት ድሮፕ ኩኪስ ።

4 ኩባያ የኬክ ዱቄት
1 ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
$1\frac{1}{3}$ ኩባያ ቡናማ ስኳር—ብራውን ሹገር
2 እንቁላል
1 ኩባያ ወተት
$2\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
3 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
$\frac{3}{4}$ ኩባያ ቸኮላት
1 ኩባያ ኦቾሎኒ ፣ ተፈልፍሎ የተከተፈ

### አሠራር

1. ቅቤና ስኳሩን ማደባለቅ ።
2. እንቁላሉን ከቡናማው ስኳር ጋር አደባልቆ በደንብ መምታት ።

$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ የሎሚ ልጣጭ ፍቅፋቂ
3 የሾርባ ማንኪያ የብርቱካን ጭማቂ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ አቿሎኒ ፣ የተፈለፈለ
ትንሽ ስኳር
ትንሽ ጨው

አሠራር

1. ቅቤውንና ስኳሩን አደባልቆ እስኪለሰልስ ድረስ መምታት ።
2. የእንቁላል አስኳል ጨምሮ መምታት ።
3. የተፈጨውን አቿሎኒ ፣ ጨው ፣ የሎሚ ልጣጭ ፍቅፋቂና ዱቄቱን አደባልቆ ከብርቱካን ጭማቂው ጋር በየተራ በመጠኑ በመጨመር ከእንቁላልና ከቅቤው ድብልቅ ጋር እስኪዋሐድ ድረስ መምታት ።
4. የተፈለፈለውን አቿሎኒ ጨምሮ መቀየጥ ።
5. ከሊጡ በማንኪያ እየቆነጠሩ ቅባት የተቀባ የኩኪስ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማስቀመጥ ።
6. ሙቀቱ 400 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ከአሥር እስከ አሥራ ሁለት ደቂቃ አብስሎ ትኩሱ ኩኪስ ላይ ስኳር መነስነስ ።

አርባ ኩኪስ ይወጣዋል ።

646. የአቿሎኒ ቅቤ ኩኪስ ።

1 ኩባያ የኬክ ፣ ዱቄት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ አቿሎኒ ፣ የተፈጨ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ቅቤ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ስኳር
1 እንቁላል ፣ ዞፉና አስኳሉ የተለየ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
2 የሾርባ ማንኪያ የብርቱካን ልጣጭ ፍቅፋቂ
1 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ልጣጭ ፍቅፋቂ

አሠራር

1. ቅቤና ስኳሩን አደባልቆ እስኪለሰልስ ድረስ መምታት ።
2. የእንቁላሉን አስኳልና ቫኒላውን ጨምሮ ማደባለቅ ።



3. ዱቄትና ጨው አደባልቆ መንፋት ።
4 ዱቄት ፣ የሎሚ ጭማቂ ፣ የብርቱካን ልጣጭ ፍቅፋቂና የሎሚ ልጣጭ ፍቅፋቂ ማደባለቅ ።
5. የዱቄቱን ድብልቅ ከእንቁላልና ከቅቤ ድብልቁ ጋር በደንብ አዋሕዶ በረዶ ቤት ውስጥ አስገብቶ ማቀዝቀዝ ።
6. የቀዘቀዘውን ሊጥ በትንሹ አድቦልቡሎ በመጠኑ የተመታ የእንቁላል ዞፍ ውስጥ ነከሮ አቿሎኒውን እላዩ ላይ መነስነስ ።
7. የተድቦለቦለውን ሊጥ ቅባት የተቀባ የኩኪስ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለሃያ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

አርባ ኩኪስ ይወጣዋል ።

647. የአቿሎኒ ኩኪስ ፣ ቁጥር 1 ።

$1\frac{1}{3}$ ኩባያ የኬክ ዱቄት
1 ኩባያ አቿሎኒ ፣ ተፈልፍሎ የተከረተፈ
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
$1\frac{1}{3}$ ኩባያ ቡናማ ስኳር—ብሪውን ሹገር
2 እንቁላል ፣ የተመታ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር

አሠራር

1. ቅቤውንና $\frac{1}{3}$ ኩባያ ስኳር አደባልቆ እስኪለሰልስ ድረስ መምታት።
2. እንቁላሉን በደንብ መምታት ። ቀሪውን ስኳር ጨምሮ እስኪዋሐድ ድረስ መምታት ።
3. የቅቤውንና የእንቁላሉን ድብልቅ ማዋሐድ ።
4. ዱቄት ፣ ጨውና ቤኪንግ ፓውደር አደባልቆ መንፋት ።
5. የተነፋው ዱቄትና አቿሎኒ ከቅቤና ከእንቁላል ድብልቁ ጋር ተቀይጦ ከተመታ በኋላ በረዶ ቤት ውስጥ አስገብቶ ማቀዝቀዝ ።
6. የቀዘቀዘውን ሊጥ በማንኪያ እየቆነጠሩ ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
7. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ከስምንት እስከ አሥር ደቂቃ ማብሰል ።

ስድሳ ኩኪስ ይወጣዋል ።

7. የእንቁላል ዞፍ ቀብቶ ሙቀቱ 400 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

ስባ ስምንት ኩኪስ ይወጣዋል ።

657. የተፈጨ ዳቦ ኩኪስ ።

$2\frac{1}{2}$ ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
1 ኩባያ የኬክ ዱቄት
$\frac{2}{3}$ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
1 ኩባያ ቡናማ ስኳር—ብራውን ሹገር
2 እንቁላል ፤ በደንብ የተመታ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ሞላሰስ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ሶዳ
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ቅርንፉድ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቀረፋ
1 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
ዱቄት ፤ ወተት

አሠራር

1. ቅቤውንና ስኳሩን እስኪለሰልስ ድረስ መምታት ።
2. የተመታ እንላቁልና ሞላሰሱን ማደባለቅ ።
3. የተፈጨውን ዳቦ ፤ ዱቄት ፤ ሶዳ ፤ ቅርንፉድ ፤ ቀረፋና ቤኪንግ ፓውደር አደባልቆ መንፋት ።
4. የተፈጨ ዳቦና የዱቄት ድብልቁን ከእንቁላልና ከቅቤ ጋር በደንብ ማዋሐድ ። ሊጡ የሚቀጥን ከሆነ ዱቄት ጨምሮ ማወፈር ።
5. ሊጡን በረዶ ቤት ውስጥ አቀዝቅዞ ከዚያም በስሱ ዳምጦ በስስ መቁረጫ በተፈለገው ቅርጽ መቁረጥ ።
6. የተዳመጠውን ሊጥ ወተት ቀብቶ የኩኪስ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
7. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

አርባ ስምንት ኩኪስ ይወጣዋል ።

658. የኮምጣጣ ክሬም ኩኪስ ።

$2\frac{1}{4}$ ኩባያ የኬክ ዱቄት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ኮምጣጣ ክሬም
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ



$\frac{2}{3}$ ኩባያ ቡናማ ስኳር—ብራውን ሹገር
1 እንቁላል ፤ የተመታ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
$1\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ሶዳ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ገውዝ
ቡናማ ስኳር—ብራውን ሹገር

አሠራር

1. ቅቤና ስኳር አደባልቆ እስኪለሰልስ ድረስ መምታት ።
2. እንቁላሉን ለብቻ መትቶ ከክሬሙ ጋር መቀየጥ ።
3. ዱቄት ፤ ጨው ፤ ቤኪንግ ፓውደር ፤ ሶዳና ገውዝ አንድ ላይ መንፋት ።
4. የዱቄቱን ድብልቅ ፤ እንቁላልና ክሬሙን በየተራ በመጠኑ በመጨመር ከቅቤና ከስኳሩ ጋር አዋሕዶ በረዶ ቤት ውስጥ አስገብቶ ማቀዝቀዝ ።
5. የቀዘቀዘውን ሊጥ በስሱ ዳምጦ በተፈለገው ቅርጽ በኩኪስ መቁረጫ መቁረጥ ።
6. የተቈረጠውን ሊጥ የኩኪስ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ቡናማ ስኳር እላዩ ላይ መነስነስ ።
7. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

አርባ ስምንት ኩኪስ ይወጣዋል ።

659. የሎሚና የስፒናች ኩኪስ ።

$3\frac{2}{3}$ ኩባያ የኬክ ዱቄት
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
1 ኩባያ ስኳር
5 የእንቁላል አስኳል ወይም 2 የእንቁላል ዞፍ
3 የሾርባ ማንኪያ ወተት
$1\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
$2\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ሶዳ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
ወተት
እንቁላል

662. የማርና የብርቱካን ኩኪስ ።

3 ኩባያ የኬክ ዱቄት
$\frac{3}{4}$ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ስኳር
1 እንቁላል ፣ የተመታ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ማር
$1\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ዝንጅብል
2 የሾርባ ማንኪያ የብርቱካን ጭማቂ

አሠራር

1. ቅቤውንና ስኳሩን አደባልቆ እስኪለሰልስ ድረስ መምታት ።
2. እንቁላል ፣ ማርና ዝንጅብል ከቅቤውና ከስኳሩ ጋር አደባልቆ መምታት ። የብርቱካን ጭማቂውን ጨምሮ ማዋሐድ ።
3. ዱቄቱን ነፍቶ በመጠኑ በመጨመር በደንብ እስኪዋሐድ ድረስ መምታት ።
4. የተዘጋጀውን ሊጥ በረዶ ቤት ውስጥ አስገብቶ ማቀዝቀዝ ።
5. የቀዘቀዘውን ሊጥ በስሱ ዳምጦ በተፈለገው ዓይነት ቅርጽ ቆርጦ የኩኪስ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
6. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ከስምንት እስከ አሥር ደቂቃ ማብሰል ።

አንድ መቶ ሃያ ኩኪስ ይወጣዋል ።

663. የቀረፋ ኩኪስ ።

2 ኩባያ የኬክ ዱቄት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
1 ኩባያ ስኳር
1 እንቁላል ፣ የተመታ
2 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
$\frac{1}{4}$ የሻዬ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{2}$ ኩባያ አቾሎኒ ፣ የተፈለፈለ
1 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ቀረፋ



አሠራር

1. ቅቤውንና ስኳሩን አደባልቆ እስኪለሰልስ መምታት ።
2. ዱቄት ፣ ቤኪንግ ፓውደርና ጨውን አደባልቆ መንፋት ።
3. የተመታውን እንቁላል የተነፋው ዱቄት ውስጥ በመጠኑ በመጨመር ከቅቤውና ከስኳሩ ጋር በደንብ አዋሕዶ በረዶ ቤት ውስጥ አስገብቶ ማቀዝቀዝ ።
4. የቀዘቀዘውን ሊጥ በስሱ ዳምጦ በተፈለገው ዓይነት ቅርጽ በኩኪስ መቁረጫ ቆርጦ ካስፈለገ የእንቁላል ዞፍ እላዩ ላይ መቀባት።
5. የተቈረጠውን ሊጥ ኩኪሱ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ በእያንዳንዱ ሊጥ መካከል አቾሎኒውን ስክቶ እላዩ ላይ ቀረፋ መነስነስ ።
6. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአሥር ደቂቃ ማብሰል ።

ሰባ ስድስት ኩኪስ ይወጣዋል ።

664. አምስት በአንድ ኩኪስ ።

6 ኩባያ የኬክ ዱቄት
4 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
$1\frac{1}{2}$ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
3 ኩባያ ቡናማ ስኳር—ብራውን ሹገር
2 እንቁላል ፣ በደንብ የተመታ
2 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው

አሠራር

1. ቅቤውንና ስኳሩን አደባልቆ እስኪለሰልስ መምታት ።
2. የተመታውን እንቁላልና ቫኒላ ከቅቤውና ከስኳሩ ጋር ማደባለቅ።
3. ጨው ፣ ቤኪንግ ፓውደር ፣ ዱቄት ቀይጦ ከተነፋ በኋላ ከእንቁላሉና ከቅቤው ድብልቅ ጋር እቡክቶ ማዋሐድ።
4. የተዘጋጀውን ሊጥ አምስት ቦታ ክፍሎ እያንዳንዱን በቁመቱ በወፍራሙ አድቦልቡሎ በረዶ ቤት ውስጥ አስገብቶ ማቀዝቀዝ ።
5. የቀዘቀዘውን ሊጥ በስሱ ቆርጦ የኩኪስ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
6. ሙቀቱ 375 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ማብሰል ።

ሦስት መቶ ኩኪስ ይወጣዋል ።

1 ኩባያ ኮምጣጣ ክሬም
1 የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሻይ ማንኪያ ቀረፋ
$\frac{3}{4}$ የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ሶዳ

አሠራር

1. ስኳሩን ከክሬሙ ጋር አደባልቆ እያማሰሉ ማሟሟት ።
2. ዱቄት ፥ ጨው ቀረፋና ሶዳ አደባልቆ ከተነፉ በኋላ ከስኳርና ከክሬሙ ጋር ማዋሐድ ።
3. ቸኮላቱን አቅልጦ ከተዘጋጀው ሊጥ ጋር በደንብ ማደባለቅ ።
4. ሊጡን በማንኪያ እየቆነጠሩ የተቀባ የኩኪስ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
5. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለሃያ ደቂቃ ማብሰል ።

ሰባ ሁለት ኩኪስ ይወጣዋል ።

672. የገና ኩኪስ ።

$2\frac{1}{2}$ ኩባያ የኬክ ዱቄት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ወተት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
1 ኩባያ ስኳር
1 እንቁላል
2 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
1 የእንቁላል ዘፍ

አሠራር

1. ቅቤውን ብቻ እስኪለሰልስ ድረስ መምታት ።
2. ስኳርና እንቁላሉን ከተመታው ቅቤ ጋር በደንብ ማደባለቅ ።
3. ቤኪንግ ፓውደር ፥ ዱቄትና ጨው አደባልቆ መንፋት ።
4. የተነፋውን የዱቄት ድብልቅና ወተቱን በየተራ መጥኖ በመጨመር በተራ ቁጥር 2 ከተዘጋጀው የቅቤ ድብልቅ ጋር ማዋሐድ ። ቫኒላውን ጨምሮ ማደባለቅ ።



5. የተዘጋጀውን ሊጥ በረዶ ቤት ውስጥ አስገብቶ ከቀዘቀዘ በኋላ ዱቄት የተነሰነሰበት ጣውላ ወይም መክተፊያ ላይ በስሱ ጠፍጥፎ በተፈለገው ዓይነት ቅርጽ መቊረጥ ።
6. የተቈረጠውን ሊጥ ቅባት የተቀባ የኩኪስ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ የእንቊላሉን ዘፍ መቀባት ።
7. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ከአሥር እስከ አሥራ ሁለት ደቂቃ ማብሰል ።

አንድ መቶ ኩኪስ ይወጣዋል ።

673. የዘቢብ ኩኪስ ።

$2\frac{1}{2}$ ኩባያ የኬክ ዱቄት
1 ኩባያ ዘቢብ ፥ የታጠበ
$\frac{3}{4}$ ኩባያ ማርገሪን—ቅቤ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቀረፋ
$\frac{3}{4}$ ኩባያ ስኳር
1 የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
1 የሻይ ማንኪያ የሎሚ ልጣጭ ፍቅፋቂ
1 ኩባያ አቾሎኒ ተፈልፍሎ ፥ የተከረተፈ
2 እንቁላል ፥ በደንብ የተመታ
6 የሾርባ ማንኪያ ወተት

አሠራር

1. ቅቤውን ብቻ እስኪለሰልስ ድረስ መምታት ።
2. ዱቄት ፥ ጨው ፥ ቀረፋ ፥ ስኳርና ቤኪንግ ፓውደር አደባልቆ መንፋት ።
3. የተነፋውን የዱቄት ድብልቅ ከተመታው ቅቤ ጋር በእንቁላል መምቻ በደንብ እስኪያያዝ ድረስ መምታት ።
4. የሎሚ ልጣጭ ፥ አቾሎኒ ፥ ዘቢብ ፥ እንቁላልና ወተት አደባልቆ በተራ ቁጥር 3 ከተዘጋጀው ሊጥ ጋር ማዋሐድ ።
5. ቅባት የተቀባ የኩኪስ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ሊጡን በማንኪያ እየቆነጠሩ ማድረግ ።
6. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

ሰማንያ አራት ኩኪስ ይወጣዋል ።

## ሳንድዊች

የሳንድዊች ሙሊት ፤

674. ፎርማጆና ቤከን የሳንድዊች ሙሊት ።

½ ኩባያ ፎርማጆ
¼ ኩባያ ቤከን ፣ ተከትፎ የተጠበሰ
½ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
3 የሾርባ ማንኪያ ማዮኔዝ

አሠራር

ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ አደባልቆ ለሳንድዊች ሙሊት መጠቀም ።

675. ፎርማጆና አቾሎኒ የሳንድዊች ሙሊት ።

1 ኩባያ ፎርማጆ
¼ ኩባያ ጨው ያለው አቾሎኒ
2 የሾርባ ማንኪያ ማዮኔዝ

አሠራር

ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ አደባልቆ ለሳንድዊች ሙሊት መጠቀም ።

676. ፎርማጆና ዘቢብ የሳንድዊች ሙሊት ።

85 ግራም ፎርማጆ
½ ኩባያ ዘቢብ
1 ኩባያ ውኃ
2 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
ትንሽ ጨው

1. ዘቢቡን አጥቦ አንድ ኩባያ ውኃ ውስጥ ጨምሮ ለአሥር ደቂቃ በዝግታ ማብሰል ።
2. ስኳሩን ከበሰለው ዘቢብ ጋር አደባልቆ ማቀዝቀዝ ።
3. ፎርማጆውንና ጨውን ከዘቢቡና ከስኳሩ ጋር ማዋሐድ ።
4. በዳቦ ሳንዷዊች ሠርቶ ማቅረብ ።

አንድ ኩባያ ተኩል የሳንድዊች ሙሊት ይወጣዋል ።



677. የቤከን የሳንድዊች ሙሊት ።

7 በስሱ የተቈረጠ ቤከን ፣ የተከተፈ
1 ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
¼ ኩባያ ማዮኔዝ

አሠራር

ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ አደባልቆ በተቈረጠ ሁለት ዳቦ መካከል አስገብቶ ሳንድዊች መሥራት ።

678. የበሬ ሥጋ የሳንድዊች ሙሊት ።

1½ ኩባያ የሥጋ አሮስቶ
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
2 የሻይ ማንኪያ የበርበሬ ሶስ
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ

አሠራር

ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ አደባልቆ የተቈረጠ ሁለት ዳቦ መካከል አስገብቶ ሳንድዊች መሥራት ።

679. የአሳማ ሥጋ የሳንድዊች ሙሊት ።

1 ኩባያ የአሳማ ሥጋ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
½ የሾርባ ማንኪያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
½ የሻይ ማንኪያ ሰናፍጭ
2 የሾርባ ማንኪያ ማዮኔዝ

አሠራር

ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ አደባልቆ በተቈረጠ ሁለት ዳቦ መካከል አስገብቶ ሳንድዊች መሥራት ።

680. የአሳማ ሥጋና የፎርማጆ የሳንድዊች ሙሊት ።

$\frac{1}{2}$ ኩባያ የአሳማ ሥጋ ፣ ተፈጭቶ የተቀቀለ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ፎርማጆ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
ማዮኔዝ

አሠራር

ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ አደባልቆ በተቈረጠ ሁለት ዳቦ መካከል አስገብቶ ሳንድዊች መሥራት ።

681. የበግ ሥጋ የሳንድዊች ሙሊት ።

1$\frac{1}{4}$ ኩባያ የበግ ሥጋ ፣ በስሱ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ቁንዶ በርበሬ
$\frac{1}{2}$ የሾርባ ማንኪያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
1 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ

አሠራር

ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ አደባልቆ በተቈረጠ ሁለት ዳቦ መካከል አስገብቶ ሳንድዊች መሥራት ።

682. የጉበትና የቤከን የሳንድዊች ሙሊት ።

$\frac{1}{2}$ ኩባያ ቤከን ፣ ተከትፎ የተቀቀለ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ የተፈጨ ጉበት ፣ የተቀቀለ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ክሬም
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ
ትንሽ ሚጥሚጣ

አሠራር

ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ አደባልቆ በተቈረጠ ሁለት ዳቦ መካከል አስገብቶ ሳንድዊች መሥራት ።



683. የጉበትና የዘቢብ የሳንድዊች ሙሊት ።

$\frac{3}{4}$ ኩባያ ጉበት ፣ ተከትፎ የተቀቀለ
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ዘቢብ
2 የሾርባ ማንኪያ ማዮኔዝ
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ሰናፍጭ
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ሽንኩርት ፣ የተከተፈ
3 የሾርባ ማንኪያ የበርበሬ ሶስ
ትንሽ ጨው
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ አደባልቆ የተቈረጠ ሁለት ዳቦ መካከል አስገብቶ ሳንድዊች መሥራት ።

684. የጥጃ ሥጋና የካሮት የሳንድዊች ሙሊት ።

$\frac{1}{2}$ ኩባያ የጥጃ ሥጋ ፣ ተከትፎ የተቀቀለ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ካሮት ፣ ተልጦ የተከተፈ
1 የሻይ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
3 የሾርባ ማንኪያ ማዮኔዝ
ትንሽ ጨው
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ አደባልቆ በተቈረጠ ሁለት ዳቦ መካከል አስገብቶ ሳንድዊች መሥራት ።

685. የምላስ የሳንድዊች ሙሊት ።

1$\frac{1}{2}$ ኩባያ ምላስ ፣ ተቀቅሎ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ራድሽ ፣ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ማዮኔዝ
ትንሽ ሚጥሚጣ

## 693. የተጠበሰ ሥጋ ሳንድዊች ።

አሮስቶ ፥ በስሱ የተቈረጠ
12 የተቈረጠ ዳቦ ፥ ወይም 6 ትናንሽ ዳቦ
½ ኩባያ ካችአፕ
½ ኩባያ ውኃ
1 ፍንካች ነጭ ሽንኩርት ፥ የተከተፈ
1 የሻይ ማንኪያ በርበሬ
¼ ኩባያ ስኳር
1 የሻይ ማንኪያ ሰናፍጭ

### አሠራር

1. ካችአፕ ፥ ውኃ ፥ ነጭ ሽንኩርት ፥ በርበሬ ፥ ስኳርና ሰናፍጭ አደባልቆ እሳት ላይ ጥዶ ለአሥር ደቂቃ ማብሰል ።
2. ሥጋውን በተራ ቊጥር 1 ከተዘጋጀው ድብልቅ ጋር ቀይጦ በደንብ እስኪፈላ ድረስ እሳቱ ላይ ማቆየት ።
3. የተዘጋጀውን ሥጋና ሶስ ግማሹን ዳቦ ላይ አፍስሶ በቀሪው ዳቦ መሸፈን ።
4. የተዘጋጀውን ሳንድዊች በሦስት ማዕዘን ቈርጦ ማቅረብ ።

እሥራ ሁለት ሳንድዊች ይወጣዋል ።

## 694. እንቊላል ተነክሮ የተጠበሰ ሳንድዊች ።

ዳቦ
2 እንቊላል ፥ በመጠኑ የተመታ
1 ኩባያ ወተት
½ ኩባያ ዱቄት
½ የሻይ ማንኪያ ጨው
ትንሽ ቊንዶ በርበሬ
ዘይት ፥ ወይም ቅቤ ፥ ለመጥበሻ

### አሠራር

1. ዳቦውን በተፈለገው ዓይነት የሳንድዊች ሙሊት መቀባት ወይም መሙላት ።
2. እንቊላል ፥ ዱቄት ፥ ጨው ፥ ቊንዶ በርበሬና ወተት ማደባለቅ ።



3. ሳንድዊቹን የእንቊላል ድብልቁ ውስጥ ነክሮ መጥበሻ ላይ በፈላ ዘይት ወይም ቅቤ መጥበስ ።

## 695. የሰርዲን ሳንድዊች ።

6 የተቈረጠ ዳቦ
2 ቆርቆሮ 90 ግራም ሰርዲን
2 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
2 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
1 ኩባያ ወተት
2 የሾርባ ማንኪያ የቲማቲም ካችአፕ
½ ኩባያ ፎርማጆ
ትንሽ ጨው ፥ ትንሽ ሚጥሚጣ

### አሠራር

1. ቅቤውን አቅልጦ ዱቄትና ወተቱን ጨምሮ ማደባለቅ ።
2. ጨው ፥ ካችአፕና ሚጥሚጣውን ከወተት ድብልቁ ጋር አዋሕዶ እያማሰሉ እስኪወፍር ድረስ ማብሰል ። ፎርማጆውን ማደባለቅ።
3. ሰርዲኑን የተቈረጠው ዳቦ ላይ አድርጎ ምድጃ ውስጥ መጨመር ። ከሞቀ በኋላ አውጥቶ የተዘጋጀውን ሶስ እላዩ ላይ አፍስሶ ትኩሱን ማቅረብ ።

ስድስት ሳንድዊች ይወጣዋል ።

## 696. የዶሮ ሳንድዊች ።

8 የተቈረጠ ዳቦ ፥ ቅቤ ተቀብቶ የተጠበሰ
8 የተቈረጠ የዶሮ ሥጋ ፥ የተቀቀለ
8 የተቈረጠ ቲማቲም
1 ኩባያ ፎርማጆ
ጨው

### አሠራር

1. የተቈረጠውን ዳቦ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
2. በዳቦው ላይ የዶሮ ሥጋ ጨው ከዚያም ቲማቲሙን ጨምሮ ፎርማጆውን እላዩ ላይ መነስነስ ።

3. የተዘጋጀውን ሳንድዊች በምድጃ ውስጥ ፎርማጆው እስኪቀልጥ ድረስ ማቆየት ።

ስምንት ሳንድዊች ይወጣዋል ።

697. ዲ ሉክስ የዶሮ ሳንድዊች ።

2 ኩባያ የዶሮ ሥጋ ፥ ተቀቅሎ የተከተፈ
12 የተቈረጠ ዳቦ ፥ የተጠበሰ
2 ኩባያ ሃም—የአሳማ ሥጋ—የተከተፈ
3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
1 ኩባያ ክሬም ሶስ
2 የእንቊላል አስኳል
$\frac{1}{4}$ ኪሎ ፎርማጆ
ቲማቲምና የወይራ ፍሬ ፥ ለማስጌጫ
ጨው ፥ ቁንዶ በርበሬ

አሠራር

1. ሃሙን ከቅቤው ጋር አደባልቆ ለአንድ ደቂቃ መጥበስ ።
2. የዶሮ ሥጋውንና ክሬሙን ጨምሮ ለሦስት ደቂቃ ማብሰል ።
3. ክሬም ሶስ ፥ ጨውና ቁንዶ በርበሬውን ጨምሮ ለሁለት ደቂቃ ማብሰል ።
4. የእንቊላሉን አስኳል ጨምሮ እያማሰሉ እስኪወፍር ማብሰል።
5. የተዘጋጀውን የዶሮ ፥ የሃምና የእንቊላል ድብልቅ የተቈረጠው ግማሽ ዳቦ ላይ ጨምሮ በቀሪው ዳቦ መሸፈን ።
6. ከተሸፈነው ዳቦ ላይ ፎርማጆውን አድርጎ ምድጃ ውስጥ አስገብቶ ፎርማጆው እስኪቀልጥ ድረስ ማቆየት ።
7. የተዘጋጀውን ሳንድዊች በስሱ በተቈረጠ ቲማቲምና የወይራ ፍሬ አስጊጦ ትኵሱን ማቅረብ ።

ስድስት ሳንድዊች ይወጣዋል ።

698. በስሱ የተቈረጠ የዶሮ ሥጋ ሳንድዊች ።

8 የተቈረጠ ዳቦ
4 በስሱ የተቈረጠ የዶሮ ሥጋ ፥ የተቀቀለ
ቅቤ ፥ ማዮኔዝ ፥ ሰላጣ



አሠራር

1. የተቈረጠውን ዳቦ ቅቤ መቀባት ።
2. የተቈረጠው አራቱ ዳቦ ላይ የዶሮ ሥጋ አድርጎ ማዮኔዙን መቀባት ። ሰላጣውን በማዮኔዙ ላይ ደርቦ በቀሪው ዳቦ መሸፈን ።
3. ሳንድዊቹ እንደ ተዘጋጀ ወዲያው ማቅረብ ።

አራት ሳንድዊች ይወጣዋል ።

699. የምላስ ሳንድዊች ።

8 የተቈረጠ ዳቦ ፥ ነጭ
8 የተቈረጠ የስንዴ ዳቦ
$1\frac{1}{2}$ ኩባያ ምላስ ፥ ተቀቅሎ የተከተፈ
2 የሾርባ ማንኪያ ፐርስሜሎ ፥ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ሽንኩርት ፥ የተከተፈ
1 ቃሪያ ፥ የተከተፈ
$\frac{1}{3}$ ኩባያ ማዮኔዝ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ቅቤ
ሰላጣ

አሠራር

1. ምላስ ፥ ፐርስሜሎ ፥ ሽንኩርት ፥ ቃሪያና ማዮኔዝ አደባልቆ ነጩ ዳቦ ላይ መቀባት ።
2. የስንዴውን ዳቦ ቅቤ ቀብቶ የተቀባው ነጭ ዳቦ ላይ መደረብ ።
3. ሳንድዊቹን በሰላጣ አጊጦ ማቅረብ ።

ስምንት ሳንድዊች ይወጣዋል ።

700. የሃምና የቲማቲም ሳንድዊች ።

16 የተቈረጠ ዳቦ
1 ኩባያ ሃም ፥ ተቀቅሎ የተከተፈ
8 የተቈረጠ ቲማቲም
1 ፍንካች ነጭ ሽንኩርት
1 የሻይ ማንኪያ ፐርስሜሎ ፥ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ቅቤ
1 የሻይ ማንኪያ ሽንኩርት

½ የሻይ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
ትንሽ ቁንዶ በርበሬ
ትንሽ ሚጥሚጣ

አሠራር

1. ለማደባለቂያ የሚያገለግለውን ጐድጓዳ ሣህን ነጭ ሽንኩርት መቀባት ።
2. ሃም ፣ ፐርስሜሎ ፣ ቁንዶ በርበሬ ፣ ሚጥሚጣ ፣ የሎሚ ጭማቂ ፣ ሽንኩርትና ቅቤ ጐድጓዳ ሣህን ውስጥ ጨምሮ ማደባለቅ ።
3. በተራ ቍጥር 2 የተዘጋጀውን የሃም ድብልቅ ስምንቱን ዳቦ ቀብቶ ቲማቲሙ እላዩ ላይ ከተደረገ በኋላ በቀሪው ስምንት ዳቦ ሸፍኖ ማቅረብ ።

ስምንት ሳንድዊች ይወጣዋል ።

701. የተጠበሰ የአሳማ ሥጋ ሳንድዊች ።

8 የተቈረጠ ዳቦ
የተቈረጠ የአሳማ ሥጋ ፣ የተጠበሰ
ቅቤ ፣ የቃሪያ ሶስ ፣ ጨው ቁንዶ በርበሬ ፣ ሰላጣ

አሠራር

1. የተቈረጠውን ዳቦ ቅቤና የቃሪያ ሶስ በየተራ መቀባት ።
2. የተቈራረጠው አራት ዳቦ ላይ የአሳማ ሥጋ ፣ ጨው ፣ ቁንዶ በርበሬና ሰላጣ አድርጎ በቀሪው አራት ዳቦ መሸፈን ።
3. የተዘጋጀውን ሳንድዊች በሦስት ማዕዘን ቅርጽ ቈርጦ ማቅረብ ።

አራት ሳንድዊች ይወጣዋል ።

702. የሳንድዊች ሎፍ ።

1 ዳቦ
255 ግራም ክሬም ቺዝ
ቅቤ
ማዮኔዝ



ቲማቲም ፣ በስሱ የተቈረጠ
ከሃም—ከአሳማ ሥጋ—የተዘጋጀ የሳንድዊች ሙሊት
ሰላጣ ፣ ወተት ፣ፐርስሜሎ

አሠራር

1. ዳቦውን በስሱ አራት ቦታ መቍረጥ ።
2. የተቈረጠውን ዳቦ ቅቤ መቀባት ።
3. አንዱን የተቈረጠ ዳቦ ዝርግ ሣህን ላይ አድርጎ ማዮኔዝ መቀባት ። ከላዩ ላይ ደግሞ አንድ የተቈረጠ ቲማቲም ማድረግ ።
4. ሌላ የተቈረጠ ዳቦ ላይ ማዮኔዝ ቀብቶ ቲማቲም እላዩ ላይ ከተደረበ በኋላ ከሃም የተዘጋጀውን የሳንድዊች ሙሊት ዳቦው ላይ መቀባት ።
5. የተቈረጠውን ሦስተኛ ዳቦ በተራ ቍጥር 4 ከተዘጋጀው ሳንድዊች ላይ ደርቦ ማዮኔዝ ከተቀባ በኋላ ሰላጣውን ከላይ ማድረግ ።
6. ቀሪውን ዳቦ ሰላጣው ላይ መደረብ ። ሳንድዊቹ እንዲያያዝ ወደ ታች ጫን ማድረግ ።
7. ክሬሙን ቺዝና ወተቱን አደባልቆ በደንብ እስኪዋሐድ ድረስ ከተመታ በኋላ ሳንድዊቹ ላይ መቀባት ።
8. የተዘጋጀውን ሳንድዊች በረዶ ቤት ውስጥ ለአንድ ሰዓት ያህል ማቀዝቀዝ ።
9. ሳንድዊቹን ስምንት ቦታ ቈርጦ በፐርስሜሎ አጊጦ ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመገባል ።

703. የሥጋ ሳንድዊች ።

ለስላሳ ወይም ደረቅ ዳቦ
1½ ኩባያ ሥጋ ፣ በምድጃ ተጠብሶ የተከተፈ
1½ የሻይ ማንኪያ ጨው
½ የሻይ ማንኪያ በቃሪያ የተሠራ የቲማቲም ሱጎ
1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
ሰላጣ ወይም የሰዲኖ ቅጠል

አሠራር

1. ሥጋ ፣ ጨው ፣ ሱጎና ቅቤ ማደባለቅ ።
2. ለስላሳ ወይም የደረቀ ዳቦ ላይ የሥጋውን ድብልቅ ማድረግ ።

3. ከላዩ ሌላ ዳቦ ሸፍኖ በአራት ወይም በሦስት ማዕዘን መቍረጥ ።
4. በሰላጣ ወይም በሰዲኖ ቅጠል አጊጦ ማቅረብ ።

## ማርማላት ፣ ክረሜላ ፣ አይስክሬምና ፑዲንግ ።

### 704. የካሮት ማርማላት ።

$\frac{1}{2}$ ኪሎ ካሮት ፣ በደቃቁ የተከተፈ
$\frac{1}{2}$ ኪሎ ፖም ፣ በደቃቁ የተከተፈ
1 ኩባያ ኮክ ፣ በደቃቁ የተከተፈ
1 ሎሚ ፣ ጭማቂው
3 ኩባያ ስኳር

**አሠራር**

1. ካሮት ፣ ፖም ፣ ኮክ ፣ የሎሚ ጭማቂና ስኳር አደባልቆ ብረት ድስት ውስጥ እያማሰሉ በደንብ ማፍላት ።
2. ፈልቶ አረፋውን ሲከት በማንኪያ ትንሽ ሣህን ላይ ጠብ አድርጎ ሲቀዘቅዝ መርጋቱን ማረጋገጥ ።
3. ሲቀዘቅዝ መርጋቱ ከተረጋገጠ በኋላ ትኩሱን አውጥቶ ታጥቦ በተቀቀለ የማርማላት ጠርሙስ ውስጥ ጨምሮ ወዲያው መክደን ።
4. ከቀዘቀዘ በኋላ መጠቀም ።

አንድ ሊትር ተኩል ማርማላት ይወጣዋል ።

### 705. የብርቱካን ማርማላት ፣ ቍጥር 1 ።

6 ብርቱካን
2 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
ውኃ
ስኳር

**አሠራር**

1. ብርቱካኑ ታጥቦ ከተላጠ በኋላ ፍሬውን ማውጣት ።
2. የተላጠውን ብርቱካን በጣም አድቅቆ መክተፍ ።
3. ከብርቱካኑ ልጣጭ በደቃቁ ከትፎ ሦስት የሾርባ ማንኪያ ያህል ሣህን ውስጥ መጨመር ።



4. የተከተፈውን ብርቱካን በኩባያ ለክቶ ከተዘጋጀው የብርቱካን ልጣጭ ጋር ማደባለቅ ።
5. ለአንድ ኩባያ የተከተፈ ብርቱካን ሁለት ኩባያ ውኃ ጨምሮ ለአሥራ ሁለት ሰዓት ወይም ለአንድ ሌሊት ማቆየት ።
6. ተዘፍዝፎ ያደረውን ብርቱካን ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ እስኪለሰልስ ድረስ ማንተክተክ ።
7. የተቀቀለው ብርቱካን በኩባያ ከተለካ በኋላ ለአንድ ኩባያ ብርቱካን አንድ ኩባያ ስኳር ጨምሮ ለሃያ ደቂቃ ወይም እስኪ ወፍር ድረስ መቀቀል ።
8. የተዘጋጀውን ማርማላት ለአምስት ደቂቃ አቀዝቅዞ ማማሰል ።
9. ታጥቦ በተቀቀለ የማርማላት ጠርሙስ ውስጥ ጨምሮ ወዲያው መክደን ።
10. ሲቀዘቅዝ መጠቀም ።

አንድ ጠርሙስ ማርማላት ይወጣዋል ።

### 706. የብርቱካንና የግሬፕ ፍሩት ማርማላት ።

2 ብርቱካን
1 ግሬፕ ፍሩት
1 ሎሚ
ማር ፣ ጨው
ስኳር

**አሠራር**

1. ብርቱካኑንና ግሬፕ ፍሩቱን አጥቦ መላጥ ።
2. ልጣጩን ከትፎ አንድ ሊትር ውኃ ጨምሮ ለአምስት ደቂቃ ቀቅሎ ውኃውን አጥልሎ ማፍሰስ ፤ አሠራሩን ሁለት ጊዜ መድገም ።
3. የተላጠውን ብርቱካንና ግሬፕ ፍሩት ፍሬውን አውጥቶ ከትፎ ከልጣጩ ጋር ማደባለቅ ።
4. የተደባለቀውን ብርቱካንና ግሬፕ ፍሩት በኩባያ ለክቶ ለአንድ ኩባያ ድብልቅ ሦስት ኩባያ ውኃ ጨምሮ ለአርባ ደቂቃ መቀቀል ።
5. የተቀቀለውን ብርቱካንና ግሬፕ ፍሩት በኩባያ ለክቶ ለአንድ ኩባያ የብርቱካንና የግሬፕ ፍሩት ድብልቅ ሁለት ሦስተኛ ($\frac{2}{3}$) ኩባያ ማርና አንድ ሦስተኛ ($\frac{1}{3}$) ኩባያ ስኳር እንደዚሁም የሎሚ ጭማቂና ትንሽ ጨው ጨምሮ ለሃያ አምስት ደቂቃ ወይም ሲቀ ዘቅዝ ለመርጋት መቻሉን ትንሽ ሣህን ላይ ጠብ አድርጎ ካረጋ ገጡ በኋላ ማውጣት ።

6. የተዘጋጀውን ማርማላት ታጥቦ የተቀቀለ የማርማላት ጠርሙስ ውስጥ ትኩሱን ጨምሮ ወዲያው መክደን ።
7. ሲቀዘቅዝ መጠቀም ።

አንድ ጠርሙስ ማርማላት ይወጣዋል ።

707. የኮክ ማርማላት ።

$3\frac{1}{2}$ ኪሎ የበሰለ ኮክ
3 ብርቱካን
2 ሎሚ
$2\frac{1}{2}$ ኪሎ ስኳር

አሠራር

1. ኮኩን አጥቦ ፍሬውን ማውጣት ።
2. ፍሬው የወጣለትን ኮክ መፍጨት ።
3. ብርቱካኑንና ሎሚውን አጥቦ ከውስጡ ፍሬውን ብቻ አውጥቶ ከነልጣጩ መፍጨት ።
4. የተፈጨውን ኮክ ፣ ብርቱካን ፣ ሎሚና ስኳር ብረት ድስት ውስጥ ጨምሮ መቀቀል ።
5. ከተዘጋጀው ማርማላት ትንሽ ሣህን ላይ በማንኪያ ጠብ አድርጎ ሲቀዘቅዝ መርጋቱን ማረጋገጥ ።
6. ሲቀዘቅዝ መርጋቱ ከተረጋገጠ በኋላ ታጥቦ የተቀቀለ የማርማላት ጠርሙስ ውስጥ ጨምሮ ወዲያው መክደን ።
7. ከቀዘቀዘ በኋላ መጠቀም ።

ሦስት ጠርሙስ ማርማላት ይወጣዋል ።

708. የአናናስና የኮክ ማርማላት ።

$1\frac{3}{4}$ ኩባያ አናናስ ፣ ተልጦ የተከተፈ
1 ኪሎ ኮክ
12 ብርቱካን
1 ግሬፕ ፍሩት
$\frac{3}{4}$ ኩባያ የሎሚ ጭማቂ
ስኳር



አሠራር

1. ኮኩን አጥቦ ፍሬውን ከውስጡ ማውጣት ።
2. ፍሬው የወጣለትን ኮክ መክተፍ ።
3. አናናሱን ልጦ መክተፍ ።
4. ብርቱካኑንና ግሬፕ ፍሩቱን ልጦ ፍሬውን አውጥቶ መክተፍ ።
5. ኮክ ፣ አናናስ ፣ ብርቱካን ግሬፕ ፍሩቱንና የሎሚ ጭማቂውን አደባልቆ በኩባያ ከተለካ በኋላ በዚያው ልክ ስኳር ጨምሮ መቀቀል ።
6. ማርማላቱን በመጠኑ እስኪወፍር ድረስ እያማሰሉ መቀቀል ።
7. የተዘጋጀውን ማርማላት ታጥቦ የተቀቀለ የማርማላት ጠርሙስ ውስጥ ጨምሮ ወዲያው መክደን ።
8. ከቀዘቀዘ በኋላ መጠቀም ።

አራት ጠርሙስ ማርማላት ይወጣዋል ።

709. የብርቱካን ማርማላት ፣ ቁጥር 2 ።

4 መካከለኛ ብርቱካን
1 መካከለኛ ሎሚ
$1\frac{1}{2}$ ትልቅ ብርጭቆ ውኃ
6 ትልቅ ብርጭቆ ስኳር
$\frac{1}{2}$ ጠርሙስ ፍሩት ፓኬቲን
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ሶዳ

አሠራር

1. ብርቱካኑንና ሎሚውን ልጦ ቅርፊቱ ውስጥ የሚገኘውን ነጩን ልባስ አስወግዶ ልጣጩን አድቅቆ መክተፍ ።
2. ውኃውን ለክቶ በሚቀቀልበት ዕቃ ውስጥ ጨምሮ ሶዳውንና የተከተፈውን የሎሚና የብርቱካን ልጣጭ ለአሥር ደቂቃ ማብሰል ።
3. የበሰለውን ድብልቅ ጐድጓዳ ሣህን ላይ ገልብጦ እስኪዋሐድ ድረስ በእንጨት ማንኪያ በደንብ ማሸት ።
4. ወደ ተቀቀለበት ዕቃ ውስጥ ገልብጦ ለሃያ ደቂቃ ማብሰል ።
5. ስኳሩን ጨምሮ ለአምስት ደቂቃ እንተክትኮ ከእሳት ላይ ማውረድ ።
6. ፍሩት ፖኬቲን መጨመርና ለአምስት ደቂቃ በእንጨት ማንኪያ መምታት ።

7. የሚቀመጥበትን ዕቃ በሙቅ ውኃ በደንብ ማጠብና ማድረቅ ።
8. የበሰለውን ማርማላት ዕቃ ውስጥ ጨምሮ ቀዝቃዛ ቦታ ማስቀመጥ።
9. ሲቀዘቅዝ መጠቀም ።

710. የትርንጐ ማርማላት ።

8 ብርጭቆ ውኃ
8 ብርጭቆ ስኳር
1 ትልቅ ትርንጐ

አሠራር

1. ትርንጐውን በልክ በልኩ ሳይደቅ መክተፍ ።
2. ትርንጐውን ከውኃና ከስኳር ጋር ቀላቅሎ ማብሰል ።
3. ሙክክ ብሎ እስኪበስል ድረስ እሳት ማስመታት ።
4. ማርማላቱ የሚቀመጥበትን ዕቃ በሙቅ ውኃ አጥቦ ማድረቅ ።
5. የበሰለውን ማርማላት በዕቃው ገልብጦ ቀዝቃዛ ቦታ ማስቀመጥ።
6. ሲቀዘቅዝ መጠቀም ።

711. የእስትሮበሪ ማርማላት ።

3 ብርጭቆ እስትሮበሪ
1 መካከለኛ ብርቱካን
1 መካከለኛ ሎሚ
1 ብርጭቆ ውኃ
1 ብርጭቆ ስኳር
1 ፓኬት የተወቀጠ ፍሩት ፓንች
  ትንሽ ሶዳ

አሠራር

1. ብርቱካኑንና ሎሚውን መላጥ ። ቆዳው ውስጥ ያለውን ነጭ ልባስ ማውጣትና ልጣጩን አድቅቆ መክተፍ ።
2. ብረት ድስት ውስጥ ውኃ ፣ ሶዳና የተከተፈውን ልጣጭ ጨምሮ ለሃያ አምስት ደቂቃ እያማሰሉ ማብሰል ።



3. እስትሮበሪውን መክተፍና ሦስት ብርጭቆ ለከቶ እንደገና ጥዶ እሳቱን በደንብ ማንደድ ። ፍሩት ፓንች ጨምሮ እስኪለደልድ ድረስ ማማሰል ።
4. ስኳሩን ጨምሮ ለደቂቃ ያህል አማስሎ ከእሳት ላይ ማውረድ ።
5. የሚቀመጥበትን ዕቃ በደንብ አጥቦ መገልበጥ ።
6. ሲቀዘቅዝ መጠቀም ።

## ክረሜላ

712. የቸኮላት ክረሜላ ።

4 የሾርባ ማንኪያ ኮኮናት
2 ፍንጃል ነጭ ስኳር
2 የቡና ስኒ ወተት
1 የሻይ ማንኪያ ጨው

**አሠራር**

1. ከላይ የተጠቀሱትን መቀላቀሎች አንድ ላይ አፍልቶ እስኪወፍር ድረስ ማብሰልና በሚፈለገው ቅርጽ እያዘጋጁ ማስቀመጥ ።

713. የኦቾሎኒ ክረሜላ ።

16 እንቁላል
2 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
1 የሻይ ማንኪያ የተፈጨ ገውዝ
2 ብርጭቆ የተፈጨ ስኳር

**አሠራር**

1. እንቁላሉን ከአስኳሉ ለይቶ ዞፋን አረፋ እስኪወጣው መምታት ።
2. የተፈጨውን ስኳር ጨምሮ መምታት ።
3. ቫኒላና ገውዙን መጨመር ።
4. ወረቀት (ዋክስፔፐር) ቅቤ ቀብቶ ድብልቁን በማንኪያ እየጨለፉ ወረቀቱ ላይ አድርጎ እመጋገሪያው ላይ ማስቀመጥ ።
5. በተዘጋጀው ምድጃ ውስጥ ማብሰልና በሚፈለገው ቅርጽ እያዘጋጁ ማስቀመጥ ።

714. የብርቱካን ማርማላትና የዳቦ ፑዲንግ ።

$1\frac{1}{2}$ ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
$1\frac{1}{3}$ ኩባያ ወተት ፣ የሞቀ
$1\frac{1}{2}$ ስኳር



1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
2 እንቁላል ፣ የተመታ
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
1 ኩባያ የብርቱካን ማርማላት
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ገውዝ
ክሬም

**አሠራር**

1. የተፈጨውን ዳቦ ወተቱ ውስጥ መንከር ።
2. ዳቦው ወተቱን እንዲመጠው ትንሽ ማቆየት ።
3. ስኳር ፣ ቅቤ ፣ እንቁላል ፣ ቫኒላ ፣ የብርቱካን ማርማላት ፣ ገውዝ ጨምሮ ማደባለቅ ።
4. ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ገልብጦ የፈላ ውኃ በተሞላ ዕቃ ላይ ማስቀመጥ ።
5. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአርባ አምስት ደቂቃ በእንፋሎት ማብሰል ።
6. ትኩሱን ከክሬም ጋር ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመገባል ።

715. የብርቱካን ማርማላት ጥቅል ።

5 ኩባያ የፉርኖ ዱቄት
$2\frac{1}{2}$ ኩባያ ወተት
4 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
4 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
$1\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
2 የሻይ ማንኪያ እርሾ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ውኃ ፣ ለብ ያለ
የቀለጠ ቅቤ
የብርቱካን ማርማላት

**አሠራር**

1. ወተቱን ሞቅ አድርጎ ቅቤ ፣ ጨውና ስኳር ጨምሮ ቅቤው እስኪቀልጥ ድረስ ማማሰል ።
2. እርሾውን ለብ ባለ ውኃ ማሟሟት ።

$1\frac{1}{2}$ ኩባያ ወተት
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ክሬም
ጨው

አሠራር

1. ግማሽ ኩባያ ስኳር በወፍራም መጥበሻ ላይ ማቅለጥ ።
2. የካስታርድ መሥሪያ ኩባያ ውስጡን በቀለጠው ስኳር መቀባት ።
3. ቀሪውን ሩብ ኩባያ ስኳር ፣ እንቁላል ፣ ጨው ፣ ቫኒላ ፣ ወተትና ክሬሙን አደባልቆ ስኳር የተቀባው የካስታርድ ኩባያ ውስጥ መጨመር ።
4. የተሞላውን የካስታርድ ኩባያ የፈላ ውኃ ላይ ጥዶ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ከሠላሳ እስከ ሠላሳ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።
5. አቀዝቅዞ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

722. ጣፋጭ ሱፍሌ ።

3 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ ፣ የቀለጠ
4 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 ኩባያ ወተት
4 እንቁላል ፣ አስኳሉና ዞፉ የተለየ
4 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ

አሠራር

1. ቅቤ ፣ ዱቄትና ጨው ማደባለቅ ።
2. ወተቱን ጨምሮ እያማሰሉ ማሞቅ ።
3. የእንቁላሉን አስኳልና ስኳር አደባልቆ በደንብ መምታት ።
4. የተመታውን የእንቁላል አስኳልና ስኳር ከዱቄትና ከወተት ድብልቁ ጋር ማዋሐድ ። ሲቀዘቅዝ ቫኒላውን መጨመር ።
5. የእንቁላሉን ዞፍ እስኪወፍር ድረስ መትቶና ከፍ ብሎ ከተዘጋጀው ድብልቅ ጋር ቀይጦ ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ የፈላ ውኃ ላይ ጥዶ ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ከሃምሳ እስከ ስድሳ ደቂቃ በእንፋሎት ማብሰል ።
6. ትኩሱን ማቅረብ ።



ስድስት ሰው ይመግባል ።

723. የቸኮላት ፑዲንግ ።

28 ግራም ቸኮላት
6 የሾርባ ማንኪያ አቾሎኒ
$\frac{1}{2}$ ሊትር ወተት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ስኳር
3 የሾርባ ማንኪያ የበቆሎ ስታርች
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
1 የሻይ ማንኪያ ቅቤ

አሠራር

1. ቸኮላቱን በግማሽ ኩባያ ወተት ማሟሟት ።
2. ቀሪውን ወተት አሙቆ ከሟሟው ቸኮላት ጋር ማደባለቅ ።
3. ስኳር ፣ የበቆሎ ስታርችና ጨው ከፈላው የወተትና የቸኮላት ድብልቅ ጋር አዋሕዶ በእሳት ላይ ጥዶ እያማሰሉ እስኪወፍር ድረስ ማብሰል ።
4. ቫኒላና ቅቤውን ጨምሮ ማቅረቢያ ዕቃ ላይ ገልብጦ በረዶ ቤት ውስጥ አስገብቶ ማቀዝቀዝ ።
5. አቼሎኒውን እላዩ ላይ ነስንሶ ማቅረብ ።

አምስት ሰው ይመግባል ።

724. የሩዝ ፑዲንግ ።

$\frac{1}{2}$ ኩባያ ሩዝ
1 ሊትር ወተት
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቀረፋ ወይም ገውዝ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ስኳር
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ዘቢብ ወይም 2 እንቁላል

አሠራር

1. ሩዙን አጥቦ ማጠንፈፍ ።
2. ወተት ፣ ቀረፋ ፣ ስኳርና ጨው ከሩዝ ጋር አደባልቆ ቅባት የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ ማድረግ ።
3. ሙቀቱ 275 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ የመጀመሪያውን አንድ ሰዓት አልፎ አልፎ ማማሰል ።
4. ተጨማሪ አንድ ሰዓት ተኩል ከቆየ በኋላ ዘቢብ ወይም እንቍላል ጨምሮ ከግማሽ ሰዓት በኋላ ከምድጃው ውስጥ ማውጣት ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

725. በተርስኮች ፑዲንግ ።

1 የሾርባ ማንኪያ ቅቤ
2 ኩባያ ስኳር
$1\frac{2}{4}$ ኩባያ ወተት ፣ የሞቀ
3 የሾርባ ማንኪያ የበቆሎ ስታርች
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ቀዝቃዛ ወተት
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
2 የእንቍላል ዞፍ ፣ በወፍራሙ የተመታ
በደንብ የተመታ ክሬም ወይም የእንጆሪ ፍሬ

አሠራር

1. ቅቤውን አቅልጦ ስኳሩን ጨምሮ እያማሰሉ ስኳሩ እስኪጧጧ ድረስ እሳቱ ላይ ማቆየት ።
2. የሞቀውን ወተት ጨምሮ እስኪፈላና እስኪዋሐድ ድረስ እያማሰሉ ማቆየት ።
3. የበቆሎውን ስታርችና ጨው ከቀዝቃዛ ወተት ጋር አደባልቆ ከፈላው የወተት ድብልቅ ጋር አዋሕዶ እስኪወፍር ድረስ እያማሰሉ እሳቱ ላይ ማቆየት ።
4. በመጠኑ ሲቀዘቅዝ ከተመታው የእንቍላል ዞፍ ጋር አዋሕዶ ትናንሽ ማቅረቢያ ዕቃዎች ላይ ጨምሮ በረዶ ቤት ውስጥ ማቀዝቀዝ ።
5. በክሬም ወይም በእንጆሪ አጊጦ ማቅረብ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።



726. የቸኮላት ቀዝቃዛ ኬክ ።

1 ትንሽ ስፖንጅ ኬክ
113 ግራም ቸኮላት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ወተት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ስኳር
4 እንቍላል ፣ አስኳሉና ዞፉ የተለየ
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 ኩባያ በወፍራሙ የተመታ ክሬም
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ስኳር

አሠራር

1. ትንሽ የሎፍ መጋገሪያ ዕቃ ላይ የአሉሚኒየም ወረቀት መሸፈን ።
2. ከወረቀቱ ላይ በስሱ የተቈረጠ ስፖንጅ ኬክ ማኖር ።
3. ቸኮላቱን የፈላ ውኃ ላይ አቅልጦ ወተቱን ጨምሮ እያማሰሉ ማደባለቅ ።
4. ግማሽ ኩባያ ስኳርና የእንቍላል አስኳል ጨምሮ እያማሰሉ ማዋሐድ ።
5. ከተጣደበት አውርዶ ከተመታው የእንቍላል ዞፍ ጋር ማደባለቅ ።
6. ግማሽ የሻይ ማንኪያ ቫኒላና ጨው ጨምሮ ከተደባለቀ በኋላ ግማሹን የሎፍ መጋገሪያ ዕቃ ውስጥ ያለው ስፖንጅ ኬክ ላይ መጨመር ። ከዚያም ስፖንጅ ኬኩን ሸፍኖ ቀሪውን የቸኮላት ድብልቅ ደግሞ እላዩ ላይ መጨመር ። በስፖንጅ ኬክ ሸፍኖ በረዶ ቤት ውስጥ ለአሥራ ሁለት ሰዓት ማቀዝቀዝ ።
7. የቀዘቀዘውን ኬክ ማቅረቢያ ሣህን ላይ መገልበጥ ።
8. የተመታውን ክሬም ፣ ግማሽ የሻይ ማንኪያ ቫኒላና ሩብ ኩባያ ስኳር አደባልቆ የቀዘቀዘው ኬክ ላይ ጨምሮ ማቅረብ ።

አሥራ ሁለት ሰው ይመግባል ።

727. የተምር ፑዲንግ ።

$1\frac{1}{2}$ ኩባያ ተምር ፣ የተከተፈ
2 ኩባያ የተፈጨ ዳቦ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቤኪንግ ፓውደር
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ጨው

½ ኩባያ አቾሎኒ ፣ ተፈልፍሎ የተከረተፈ
2 እንቁላል
½ ኩባያ ስኳር
½ ኩባያ ውኃ

አሠራር

1. የተፈጨ ዳቦ ፣ ቤኪንግ ፓውደር ፣ ጨው ፣ ተምርና አቾሎኒውን ማደባለቅ ።
2. እንቁላል ፣ ስኳርና ውኃውን አደባልቆ በተራ ቍጥር 1 ከተዘጋጀው የተምር ድብልቅ ጋር ማዋሐድ ።
3. ቅባት የተቀባ ቅርጽ ማውጫ ያለው ዕቃ ላይ ጨምሮ በፈላ ውኃ ላይ ለአርባ አምስት ደቂቃ በእንፋሎት ማብሰል ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

728. የብርቱካን ፑሩ ።

2 ኩባያ የብርቱካን ጭማቂ
1 የሻይ ማንኪያ የበቆሎ ስታርች
2 የሾርባ ማንኪያ ቀዝቃዛ ውኃ
½ ኩባያ ስኳር
1 የሻይ ማንኪያ የብርቱካን ልጣጭ ፣ የተከተፈ

አሠራር

1. የብርቱካን ጭማቂውን ብረት ድስት ውስጥ ማፍላት ።
2. የበቆሎውን ስታርች በቀዝቃዛ ውኃ በጥብጦ ከፈላው የብርቱካን ጭማቂ ጋር ማደባለቅ ።
3. በደንብ እስኪዋሐድ ድረስ ማብሰል ።
4. ስኳርና የብርቱካን ልጣጩን ጨምሮ ስኳሩ እስኪሟሟ ድረስ ማማሰል ።
5. የፑሩ ማቅረቢያ ኩባያ ውስጥ ጨምሮ አቀዝቅዞ መጠቀም ።

አራት ሰው ይመግባል ።



729. አፕል—ፖም—ሜሪንጉይ ፑዲንግ ።

12 አፕል
3 እንቁላል ፣ ዞፉና አስኳሉ የተለየ
በስሱ ተቈርጦ የደረቀ ዳቦ
የፈላ ወተት
ስኳር
ገውዝ

አሠራር

1. መጋገሪያ ዕቃ ውስጥ የደረቀውን ዳቦ አስተካክሎ ከሥርም ከጐንም ማስቀመጥ ።
2. የፈላውን ወተት ዳቦው ላይ መጨመር ።
3. ከአፕሉ ውስጥ በጥንቃቄ ፍሬውንና እንጨቱን አውጥቶ ድፍኑን መቀቀል ፤ ስኳርና ገውዙን ጨምሮ ማዋሐድ ።
4. የእንቁላሉን አስኳል በስኳር መምታት ።
5. የተመታውን አስኳል ከአፕሉ ጋር አደባልቆ ዳቦው ላይ መጨመር ።
6. የእንቁላሉ ዞፍ በወፍራሙ ከተመታ በኋላ አስኳሉና አፕሉ ላይ መደረብ ።
7. ሙቀቱ 325 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ማብሰል ።

730. በውኃ የበሰለ ብርቱካን ።

8 ትልቅ ብርቱካን ፣ ፍሬ የሌለው
½ ኩባያ ስኳር
8 የሻይ ማንኪያ ቅቤ

አሠራር

1. ብርቱካኑን አጥቦ ቆዳውን መላጥ ።
2. የተላጠውን ብርቱካን በውኃ ለሠላሳ ደቂቃ ቀቅሎ ማጠንፈፍ ።
3. የተቀቀለውን ብርቱካን ከጫፍ በኩል ቈርጦ መሃሉን ከፍቶ ስኳርና ቅቤውን እያንዳንዱ ብርቱካን ውስጥ መጨመር ።
4. ብርቱካኑን ቅቢ የተቀባ መጋገሪያ ዕቃ ላይ አድርጎ ውኃ ጨምሮ መክደን ።
5. ሙቀቱ 350 ድግሪ ፋራንሃይት በሆነ ምድጃ ውስጥ ለሁለት ሰዓት ማብሰል ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 735. የሩዝ ሃለዋ ።

2 ኩባያ የተቀቀለ ሩዝ
3 ኩባያ ወተት
6 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
2 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ

### አሠራር

1. ከላይ የተጠቀሱትን መቀላቅሎች በሙሉ አንድ ላይ መቀየጥ ።
2. ድብልቁን ቅርጽ ባለው ዕቃ ላይ ገልብጦ ማቀዝቀዣ ውስጥ ማስቀመጥ ።
3. በመቀዝቀዝ ላይ እንዳለ ደጋግሞ ማማሰል ።
4. በደንብ ከቀዘቀዘ በኋላ ሳህን ላይ መገልበጥ ።
5. ከብስኩት ጋር ወይም ከምግብ በኋላ ማቅረብ ።

## 736. የሩዝ ፑዲንግ ።

1 እንቁላል
2 ኩባያ ወተት
½ ኩባያ የተቀቀለ ሩዝ
2 የሾርባ ማንኪያ ስኳር
2 የሾርባ ማንኪያ የደረቀ ዳቦ ፍርፍር
ጨው

### አሠራር

1. እንቁላሉን መምታት ።
2. ወተት ፥ ሩዝና የዳቦ ፍርፋሪውን አደባልቆ ለአሥር ደቂቃ ማቆየት ።
3. እንቁላሉንና ስኳሩን አንድ ላይ በእንጨት ማንኪያ አሽቶ ጨው መጨመር ።
4. መጋገሪያውን ዕቃ ቅባት መቀባት ።
5. የታሸውን እንቁላል ከወተቱና ከሩዙ ጋር ማደባለቅ ።
6. የተሰናዳውን ሊጥ እመጋገሪያ ዕቃ ላይ ገልብጦ እተዘጋጀው ምድጃ ውስጥ ለአንድ ሰዓት ማቆየት ።



## 737. የከረሜላ ፑዲንግ ።

2 ኩባያ ስኳር
3 የሾርባ ማንኪያ ውኃ
6 ኩባያ ክሬም
1½ የሾርባ ማንኪያ የቀለጠ ስኳር ፥ ድስቱን ለመቀብያ
6 እንቁላል
1 የሾርባ ማንኪያ ቫኒላ

### አሠራር

1. ሁለት ጭልፋ ስኳር ጥዶ ስኳሩ እስኪቀልጥ ድረስ ማማሰል ።
2. ከብ ቅርጽ ያለው ማብሰያ ድስት ውስጡን የቀለጠውን አንድ የሾርባ ማንኪያ ተኩል ስኳር በደንብ መቀባት ።
3. በሌላ ጐድጓዳ ሳህን ስኳር ፥ ቫኒላ ፥ ክሬም እንቁላል መምታት ።
4. ድብልቁን በአንድነት የስኳር ፈሳሽ በተቀባ ክብ ቅርጽ ባለው ማብሰያ ድስት ውስጥ መገልበጥ ።
5. የማብሰያውን ድስት የፈላ ውኃ በያዘ ዕቃ ላይ ጥዶ 150 ድግሪ ፋራን ሃይት ሙቀት ባለው ምድጃ ላይ በጥንቃቄ በእንፋሎት ማብሰል ።
6. ከቀዘቀዘ በኋላ ሳህን ላይ ገልብጦ ማቅረብ ።

## 738. ድብልቅ ፍራፍሬ—ማቾዶንያ ።

1 ትልቅ ፓፓያ
½ ኪሎ ብርቱካን
½ ኪሎ ሙዝ
1 ትልቅ ሎሚ
½ ኩባያ ስኳር
½ ኩባያ ቸሪ ብራንዲ ወይም 1 ኩባያ ቀይ ግራናቲና

### አሠራር

1. ፍራፍሬዎችን አጥርቶ ማጠብ ።
2. ፓፓያውን ሁለት ላይ ሰንጥቆ ፍሬውን አውጥቶ የውስጡን ሥጋ በወፍራሙ መምተር ።
3. ብርቱካኑን አራት ቦታ ላይ ከፍሎ ፥ ፍሬውን አውጥቶ ሥጋውን ከቁርበቱ ለይቶ ከፓፓያው ጋር ማደባለቅ ።

2 የእንቁላል አስኳል
2 ኩባያ ወፍራም ክሬም
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
1 የሾርባ ማንኪያ ቫኒላ

አሠራር

1. ዱቄቱንና ስኳሩን ማደባለቅ ።
2. የዱቄትና ስኳር ድብልቅ ውስጥ ወተት ጨምሮ ብረት ድስት ውስጥ አድርጎ የፈላ ውኃ ላይ ለስምንት ደቂቃ እያማሰሉ በእንፋሎት ማብሰል ።
3. እንቁላሉን ጨምሮ ለሁለት ደቂቃ ማብሰል ።
4. ሲቀዘቅዝ ክሬም ፣ ጨውና ቫኒላ ጨምሮ የአይስክሬም ዕቃ ውስጥ አድርጎ በረዶ ቤት ውስጥ ማቀዝቀዝ ።
5. ሲቀዘቅዝ አውጥቶ ማቅረብ ።

አንድ ሊትር ተሩብ አይስክሬም ይወጣዋል ።

743. የሙዝ አይስክሬም ።

1 ኩባያ የተፈጨ ሙዝ ፣ በደንብ የበሰለ
2 የሻይ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ጨው
$\frac{1}{8}$ ኩባያ ወተት
2 እንቁላል ፣ አስኳሉና ዞፉ የተለየ
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ስኳር
1 ኩባያ ወፍራም ክሬም
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
አቾሎኒ

አሠራር

1. የተፈጨ ሙዝ፣ የሎሚ ጭማቂ፣ ጨውና ወተት በደንብ ማዋሐድ።
2. ከእንቁላሉ ዞፍ ጋር ስኳር እያደባለቁ እስኪወፍር ድረስ መምታት ።
3. አስኳሉንና ክሬሙን ለየብቻ እስኪወፍር ድረስ መምታት ።



4. ከሙዝ ድብልቅ ፣ ከእንቁላሉ አስኳል ፣ ከእንቁላሉ ዞፍ ጋር ክሬምና ቫኒላ እያደባለቁ ማቀዝቀዣ ውስጥ በሚቀመጥ ዕቃ ውስጥ ጨምሮ ማቀዝቀዝ ።
5. የቀዘቀዘው አይስክሬም ላይ ኦቾሎኒ ነስንሶ ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

744. የቫኒላ አይስክሬም ።

$1\frac{1}{2}$ የሾርባ ማንኪያ ቫኒላ
6 ኩባያ ክሬም
6 የእንቁላል አስኳል
$1\frac{1}{2}$ ኩባያ ስኳር

አሠራር

1. የእንቁላል አስኳል ፣ ስኳርና ቫኒላ በጐድጓዳ ሣህን ውስጥ ከተመታ በኋላ ቀስ በቀስ ለብ ያለ ክሬም መጨመር ።
2. ቅይጡን የያዘውን ጐድጓዳ ሣህን በግማሽ ድስት ውኃ ውስጥ አስቀምጦ ድስቱን እሳት ላይ መጣድ ። ቅይጡ እስኪወፍር ድረስ ያለማቋረጥ ማማሰል ።

745. የቸኮላት አይስክሬም ፣ ቁጥር 1 ።

85 ግራም ቸኮላት
2 ኩባያ ወተት
$1\frac{1}{8}$ ኩባያ ስኳር
4 የሾርባ ማንኪያ የፉርኖ ዱቄት
2 እንቁላል ፣ በመጠኑ የተመታ
4 ኩባያ ክሬም
2 የሾርባ ማንኪያ ቫኒላ
ትንሽ ጨው

አሠራር

1. ቸኮላቱንና ወተቱን በብረት ድስት ውስጥ ማደባለቅ ።
2. በሌላ ብረት ድስት ውስጥ ውኃ አፍልቶ የተደባለቀውን ቸኮላትና ወተት ውኃው ላይ ጥዶ ቸኮላቱ እስኪሟሟ ድረስ ማሞቅ ።

749. የማር አይስክሬም ።

2 እንቁላል ፣ ዞፉና አስኳሉ የተለየ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ማር
2 ኩባያ ክሬም
1 የሻይ ማንኪያ ቫኒላ

አሠራር

1. አስኳሉን እስኪወፍር ድረስ መምታት ።
2. ማሩን ቀስ በቀስ ጨምሮ ማደባለቅ ።
3. ክሬምና ቫኒላውን ጨምሮ በደንብ አዋሕዶ ማቀዝቀዝ ።
4. የእንቁላሉን ዞፍ እስኪወፍር ድረስ መትቶ ከቀዘቀዘ የማር አይስ ክሬም ጋር አደባልቆ በረዶ ቤት ውስጥ እንዲቀዘቅዝ ማድረግ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

750. የቸኮላት አይስክሬም ፣ ቁጥር 2 ።

28 ግራም ቸኮላት
$\frac{2}{3}$ ኩባያ ውኃ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
1 ኩባያ ወፍራም ክሬም ፣ የተመታ
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ወተት

አሠራር

1. የሞቀ ውኃ ላይ ቸኮላቱን ማቅለጥ ።
2. ወተቱን ጨምሮ ለአምስት ደቂቃ ማፍላት ።
3. ውኃውን ጨምሮ ማዋሐድ ፤ በረዶ ቤት ሊቀመጥ በሚችል ዕቃ ውስጥ ጨምሮ ማቀዝቀዝ ።
4. ቫኒላውንና ክሬሙን አደባልቆ በደንብ መትቶ ከቀዘቀዘው የቸኮላት ድብልቅ ጋር አዋሕዶ እንደገና በረዶ ቤት ውስጥ አስገብቶ ማቀዝቀዝ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።



751. የቸኮላት አይስክሬም ፣ ቁጥር 3 ።

56 ግራም ቸኮላት
$\frac{2}{3}$ ኩባያ ወተት
1 እንቁላል
$\frac{1}{4}$ ኩባያ ስኳር
$\frac{1}{4}$ የሻይ ማንኪያ ቫኒላ

አሠራር

1. ወተቱን በረዶ ቤት ውስጥ ማቀዝቀዝ ።
2. የቀዘቀዘውን ወተት በእንቁላል መምቻ በደንብ መምታት ።
3. እንቁላል ፣ ስኳር ፣ ጨው ፣ ቸኮላትና ቫኒላ ከተመታው ወተት ጋር ማደባለቅ ።
4. በረዶ ቤት ሊቀመጥ የሚችል ዕቃ ውስጥ ገልብጦ ማቀዝቀዝ ።

ሦስት ሰው ይመግባል ።

752. የቡና አይስክሬም ።

8 ኩባያ ወተት
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ስኳር
$\frac{1}{2}$ ኩባያ ወፍራም ቡና ፣ የቀዘቀዘ
$\frac{1}{2}$ የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
1 ኩባያ ወፍራም ክሬም ፣ የተመታ

አሠራር

1. ወተትና ስኳሩን ማደባለቅ ።
2. ቡናና ቫኒላውን ጨምሮ በደንብ ማዋሐድ ።
3. በረዶ ቤት የሚቀመጥ ዕቃ ውስጥ ጨምሮ ማቀዝቀዝ ።
4. በረዶ መሥራት ሲጀምር ከዕቃው ውስጥ አውጥቶ እስኪለሰልስ ድረስ በእንቁላል መምቻ መትቶ ከክሬሙ ጋር አደባልቆ እንደገና በረዶ ቤት ውስጥ ማቀዝቀዝ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።

## 753. የማርና የኦቾሎኒ ካስታርድ አይስክሬም ።

4 የእንቍላል አስኳል ፣ በደንብ የተመታ
2 ኩባያ የፈላ ውኃ
1 ኩባያ ማር
2 ኩባያ ወተት
½ ኩባያ ኦቾሎኒ ፣ ተፈልፍሎ የተከረተፈ
ትንሽ ጨው

### አሠራር

1. ወተቱን በረዶ ቤት ሊቀመጥ በሚችል ዕቃ ውስጥ ጨምሮ ማቀዝቀዝ ።
2. የእንቍላሉን አስኳል ከጨው ጋር አደባልቆ መምታት ።
3. የፈላውን ውኃ ከአስኳሉ ጋር በዝግታ ጨምሮ ያለማቋረጥ ማማሰል ። የፈላ ውኃ ላይ አስቀምጦ ለሁለት ደቂቃ በእንፋሎት ማብሰል ።
4. የአስኳሉ ድብልቅ ከቀዘቀዘ በኋላ ከማሩ ጋር ማዋሐድ ።
5. በረዶ መሥራት የጀመረውን ወተት ከበረዶ ቤት ውስጥ አውጥቶ በእንቍላል መምቻ መምታት ።
6. የአስኳሉን ድብልቅና የተመታውን ቀዝቃዛ ወተት ቀይጦ የካስታርድ ዕቃ ውስጥ ጨምሮ ማቀዝቀዝ ።
7. የቀዘቀዘው አይስክሬም ላይ ማር ጨምሮ እላዩ ላይ ኦቾሎኒ ነስንሶ ማቅረብ ።

ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 754. ኒውዮርክ አይስክሬም ።

1¼ ኩባያ ወፍራም ክሬም
2 ኩባያ ወተት
1 የሾርባ ማንኪያ የበቆሎ ስታርች
2 የሾርባ ማንኪያ ቀዝቃዛ ወተት
2 እንቍላል ፣ አስኳሉና ዞፉ የተለየ
½ ኩባያ ስኳር
½ ኩባያ የበቆሎ ሲረፕ—ኮርን ሲረፕ
½ የሻይ ማንኪያ ቫኒላ
¼ የሻይ ማንኪያ ጨው



### አሠራር

1. ወተቱን የፈላ ውኃ ላይ አስቀምጦ ማሞቅ ።
2. በሁለት የሾርባ ማንኪያ ወተት ስታርቹን አደባልቆ የሞቀው ወተት ውስጥ ጨምሮ እስኪወፍር ድረስ እያማሰሉ ማብሰል ።
3. አስኳል ፣ ስኳር ፣ ጨውና ኮርን ሲረፕ በደንብ ማደባለቅ ።
4. በተራ ቍጥር 2 የተዘጋጀውን የወተትና የስታርች ድብልቅ በተራ ቍጥር 3 ከተዘጋጀው አስኳል ጋር አዋሕዶ ለሁለት ደቂቃ በፈላ ውኃ ላይ ጥዶ በእንፋሎት ማብሰል ።
5. ቫኒላውን ጨምሮ በረዶ ቤት ውስጥ ማቀዝቀዝ ።
6. በረዶ መሥራት ሲጀምር አውጥቶ በእንቍላል መምቻ መምታት ።
7. የእንቍላሉን ዞፍና ክሬሙን ለየብቻ መትቶ ቀዝቅዞ ከተመታው የወተትና የአስኳል ድብልቅ ጋር አዋሕዶ የአይስክሬም ዕቃ ውስጥ ጨምሮ በረዶ ቤት ውስጥ ማቀዝቀዝ ።

ከስድስት እስከ ስምንት ሰው ይመግባል ።

## 755. የእንቍላል አይስክሬም ።

1 ኩባያ ወፍራም ክሬም ፣ የተመታ
2 እንቍላል ፣ አስኳልና ዞፉ የተለየ
½ ኩባያ ስኳር
2 የሾርባ ማንኪያ ብራንዲ
2 የሾርባ ማንኪያ ራም
1 ኩባያ ወተት ፣ የሞቀ

### አሠራር

1. የእንቍላሉ አስኳል ውስጥ በመጠኑ ስኳር ጨምሮ እስኪወፍር ድረስ መምታት ።
2. ብራንዲ ፣ ራምና ወተቱ ተጨምሮ ከተደባለቀ በኋላ በረዶ ቤት ውስጥ ማቀዝቀዝ ።
3. የእንቍላሉ ዞፍና ክሬሙ ለየብቻ በደንብ ከተመታ በኋላ ከቀዘቀዘው የእንቍላል አስኳል ድብልቅ ጋር አዋሕዶ አይስክሬም ዕቃ ውስጥ ጨምሮ በረዶ ቤት አስገብቶ ማቀዝቀዝ ።

ስድስት ሰው ይመግባል ።




16. የሥጋ መፍጫ
17. መከተፊያ
18. ባለ እጀታ ቢላዋ
19. መጥበሻዎች
20. ዱቄት መለወሻና ጎገር መሥሪያ ድስት
21. ወተት ማፍያ
22. የምግብ ማቀላቀያና ማደባለቂያ ሳህኖች
23. የሥጋ መምቻ
24. ባለ ሳንቲ ሜትር መለኪያ
25. የፍራፍሬ መጭመቂያ
26. የአትክልት መፍጫ
27. የሥጋና የቢስኩት መምችያ
28. የሎሚ ፥ የብርቱካንና የካሮት መፈቅፈቂያ
29. የፓስታ ላጫና የፔስትሪ መሥሪያ






30. ፈሳሽ ማንቆርቆሪያ
31. ዳቦና ሥጋ መቁረጫ ቢላዎች
32. የወጥና የገንፎ ማማሰያ
33. የድንች መላጫ ፥ የፍራፍሬ መክተፊያና ቅርጽ ማውጫዎች
34. ዳቦና ኬክ መሥሪያ
35. የኬክና የፒዛ መሥሪያ
36. ወንፊት ፥ ማጥለያ
37. የብስኩት ጌጣጌጥ ማውጫዎች

19. ገውዝ (ናትሚግ)--ኖች ሞስካታ ፤ በርበሬ መቀመሚያ ፣ እን ዲሁም ለአበሻና ፈረንጅ ምግብ ማጣፈጫ ቅመም ።

20. ራም ፤ ጥሩ ጣዕም ያለው የመጠጥ ዓይነት ። ኬክ ማጣፈጫ ይሆናል ።

21. ድራይ ይስት (ድራይ ሂስት) ፤ ሌቪቶ የዳቦና የአምባሻ እርሾ ።

22. አሬራ ፤ ቅቤው የወጣለት ወተት ።

23. አጓት ፤ ቅቤው የወጣለት ወተት ፤ ፈልቶ አይቡ ከወጣ በኋላ የሚቀረው ፈሳሽ ።

24. አዋዜ ፤ ተቀምሞ የተፈጨ በርበሬ ፤ ለጥሬና ለጥብስ ሥጋ መባያ የሚሆን ።

25. አይብ ፤ ቅቤው የወጣለትን ወተት በማፍላት የሚገኝ ነጭ ጓጓላ መሳይ ቅባት (ኮቴጅ ቺዝ) ።

26. ፑዲንግ ፤ የምግብ ዓይነት ።

27. አኘሪኮት ፤ ፍሬ ።